

በቀና ልብ - በመልካም እጆች ስር

ገጽ 16

የሴቶች የተሃድሶ እና የክህሎት ማበልጸጊያ ስልጠና ማዕከል ግንባታ



ገጽ 14


# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

82ኛ ዓመት ቁጥር 210 መጋቢት 30 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10:00

ቅዳሜ

ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!







ፎቶ፡- ዳኜ አበራ

## «የክልል ልዩ ኃይልን መልሶ የማደራጀት ስራ ከትጥቅ ማስፈታት ጋር አይገናኝም»

*- የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት*

**ሞገስ ተስፋ**

አዲስ አበባ፡- በሁሉም ክልሎች የተጀመረው የክልል ልዩ ኃይሎችን መልሶ የማደራጀት ስራ ከትጥቅ ማስፈታት ጋር በምንም መልኩ እንደማይገናኝ የመንግሥት ኮሙዩኒኬሽን አገልግሎት አስታወቀ። 92 የውጭ አገር ዜጐች በሕገ ወጥ የማዕድን ንግድ ሥራ ሲንቀሳቀሱ በቁጥጥር ስር ውለው አስፈላጊው ምርመራ እየተደረገባቸው መሆኑንም ገልጿል።

የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት ሚኒስትር ዴኤታ ሰላማዊት ካሳ ትናንት አገራዊ የሰላም፣ የፀጥታና የልማት እንቅስቃሴን አስመልክቶ ለመገናኛ ብዙሃን በሰጡት መግለጫ እንዳስታወቁት፤ ልዩ ኃይሎችን መልሶ የማደራጀት ስራ በሁሉም ክልሎች ተጀምሯል።

መንግሥት ጠንካራ የመከላከያ ሠራዊት ለመገንባት ባለፉት ዓመታት በጥናት ላይ ተመርኩዞ ስራ ሲሰራ ቆይቷል ያሉት ሚኒስትር ዴኤታዋ፤ ጥናቱን ተከትሎ ባስቀመጠው አቅጣጫ መሰረት የክልል ልዩ ኃይሎች በተለያዩ መዋቅሮች እንዲደራጁ የሚያስችል ተግባራዊ እርምጃ ተጀምሯል። አንዱ ጥናትም የክልል ልዩ ሃይሎችን መልሶ በማደራጀት የመከላከያ ሠራዊትን እንዲያጠናክሩ ማድረግ ነው ብለዋል።

ሚኒስትር ዴኤታዋ በመግለጫው፤ በሁሉም ክልሎች በየደረጃው ባሉ

«የክልል ልዩ ኃይልን ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



ፎቶ፡- አዩብ ተፈሪ

## «ተመራማሪዎች በተለያዩ ቋንቋዎች ምርምሮችን በማሳተም የውሸት ትርክቶችን ማስተካከል አለባቸው»

*- ዶክተር ኢንጂነር ሀብታሙ ኢተፋ የውሃና ኢነርጂ ሚኒስትር*

**ሞገስ ጸጋዬ**

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ ተመራማሪዎች በተለያዩ የውጭ ቋንቋዎች ምርምሮችን በማሳተም በኢትዮጵያ በውሃ ሀብት አጠቃቀም ዙሪያ ያሉ የውሸት ትርክቶችን ማስተካከል እንዳለባቸው የውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር አስታወቀ።

«ተመራማሪዎች በተለያዩ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

## ቢሮው የመዲናዋን የቱሪዝም ሀብት ለማስተዋወቅ ከኢፕድ ጋር ለመስራት ስምምነት ተፈራረመ

**ሳሙኤል ወንደሰን**

አዲስ አበባ፡- የአዲስ አበባ ባህል፣ ኪነ ጥበብና ቱሪዝም ቢሮ ከተማዋ ያላትን የቱሪዝም ሀብት ለማስተዋወቅ ከኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ጋር በጋራ ለመስራት የሚያስችለውን የመግባቢያ ሰነድ ተፈራረመ።

የአዲስ አበባ ከተማ ባህል፣ ኪነ -ጥበብና ቱሪዝም ቢሮ ኃላፊ ዶክተር ሂሩት ካሰው በስምምነቱ ወቅት እንደተናገሩት፤ የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በሀገር ውስጥና በውጭ ቋንቋዎች በሚያሳትማቸው ጋዜጦችና መጽሄቶች መልካም አስተሳሰብ የሚቀርጹና የሚገነቡ የባህል፣ የኪነ -ጥበብና የቱሪዝም ስፍራዎችን ለህብረተሰቡ በወቅቱ ተደራሽ የሚያደርግ ተቋም ነው።

አዲስ አበባ በባህል፣ በኪነ -ጥበብና በቱሪዝም ያላትን ሀብት ለሀገር ውስጥና ለውጭ ሀገር ቱሪስቶች ለማስተዋወቅ ከኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ጋር መሥራት ጉልህ

ቢሮው የመዲናዋን ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



## ለድርቅ ተጎጂዎች የአስቸኳይ ጊዜ ምላሽ ከማጠናከር ጎን ለጎን የዘላቂ መፍትሔ ፍኖተ ካርታ ይዘጋጃል

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- ለድርቅ ተጎጂዎች እየተደረገ ያለውን የአስቸኳይ ጊዜ ምላሽ ከማጠናከር ጎን ለጎን የዘላቂ መፍትሔ ፍኖተ ካርታ እንደሚዘጋጅ ብሔራዊ የአደጋ ሥጋት አመራር ምክር ቤት ሰብሳቢ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ደመቀ መኮንን ገለጹ።

የአደጋ ሥጋት አመራር ምክር ቤት ትናንትና ባካሄደው መደበኛ ስብሰባ የድርቅ አደጋዎች ምላሽ የአራት ወራት

ለድርቅ ተጎጂዎች ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል




# ዩኒቨርሲቲው የህንጻ ፕሮጀክቶች ላይ የአዋጭነት ጥናት እንዲያከናውን ቋሚ ኮሚቴው አሳሰበ

## - ዩኒቨርሲቲው በክዋኔ ኦዲት በርካታ ጉድለቶች እንደታዩበት ተገልጿል

**ዳግማዊት አበበ**

አዲስ አበባ፡- በሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ እየተገነቡ ያሉ የህንጻ ፕሮጀክቶች የአዋጭነት ጥናት እንዲከናወንባቸው የኢፌዴሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የመንግሥት ወጪ አስተዳደርና ቁጥጥር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አሳሰቧል።

የሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲዎች የህንጻዎች ግንባታ ፕሮጀክት አፈጻጸም ውጤታማነትን በተመለከተ ባቀረቡት የ2013 እና 2014 ዓ.ም የስራ ክንዋኔ ሪፖርት ላይ፤ በኢፌዴሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የመንግሥት ወጪ አስተዳደር እና ቁጥጥር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ አቶ ክርስቲያን ታደለ በሰጡት አስተያየት፤ በዩኒቨርሲቲው የሚገነቡ ማናቸውም የህንጻ ፕሮጀክቶች የአዋጭነት ጥናት እና የቅድመ ትግበራ ግምገማ ሊደረግላቸው ይገባል።

የኦዲት ሪፖርቱ እንደሚያመለክተው በዩኒቨርሲቲው እየተገነቡ ያሉ የህንጻ ፕሮጀክቶች ላይ የአዋጭነት ጥናት እና ቅድመ ትግበራ ግምገማ አልተደረገላቸውም ያሉት ሰብሳቢው፤ ይህም ባለመከናወኑ በርካታ ችግሮች አጋጥመዋል ሲሉ ገልጸዋል።

ለአብነትም በወሊሶ ካምፓስ ላይ የመዋኛ ገንዳ ከተቆፈረ በኋላ ቦታው ደረጃውን የጠበቀ አለመሆኑ ታውቆ እንዲቋረጥ መደረጉን አንስተው፤ በተመሳሳይ የአካዳሚ ህንጻ አዳራሽ የፍሳሽ ቆሻሻ ማጠራቀሚያ መቆፈር ከተጀመረ በኋላ ስራው እንዲቋረጥ ተደርጎ ከነባር ቆሻሻ ማጠራቀሚያው ጋር መገናኘቱን አክለዋል።

በተጨማሪም የህንጻ ፕሮጀክቱ በተፈጥሮ ውሃ ተሞልቶ በመገኘቱ ጥቅም አለመስጠቱ እና አንዳንድ የፍሳሽ መገናኛዎች ከላብራቶሪዎች ጋር የሚገናኙ በመሆናቸው እንዲቋረጡ መደረጋቸውን እንደማሳያ ተናግረዋል።

ፕሮጀክቶቹ በውል በተቀመጠላቸው ጊዜ ተጠናቀው ለማህበረሰቡ አገልግሎት አለመስጠታቸው እና ስራዎች ከተጀመሩ በኋላ እንዲቋረጡ መደረጉ የመንግሥት ሀብት ያለ አግባብ ብክነት ማስከተሉን የኦዲት ሪፖርቱ



እንደሚያመላክት አብራርተዋል።

ተገቢ የሆነ የአዋጭነት ጥናት እና ትግበራ ግምገማ ቢሰራ እነዚህ ችግሮች አይፈጠሩም ነበር ያሉት አቶ ክርስቲያን፤ ማንኛውም ህንጻ ግንባታ ሲገነባ የአዋጭነት ጥናት መቅረብ ይኖርበታል ሲሉ ተናግረዋል።

የአዋጭነት ጥናቱ ቀድሞ ተጠንቶ ህንጻው ቢጠናቀቅ የሚወጡ ተጨማሪ ወጪዎችን እንደሚያድን ጠቅሰውም፤ ጤናማ የሆነ የዩኒቨርሲቲ የመማር ማስተማር ሂደት ለማስቀጠልም ምቹ ሁኔታን እንደሚፈጥር ጠቁመዋል።

የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ ዩኒቨርሲቲው በአሥር ቀናት ውስጥ የተስተካከለ የኦዲት ማሻሻያ መርሃ ግብር እንዲልክ እና በየሦስት ወሩም የአፈጻጸም ሪፖርት እንዲያቀርብ አቅጣጫ አስቀምጠዋል።

የፌዴራል ዋና ኦዲት መስሪያ ቤት ዋና ኦዲተር ወይዘሮ መሰረት ዳምጤ በበኩላቸው፤ በሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ የ2013 እና 2014 በጀት ዓመት የክዋኔ ኦዲት በሚገመገምበት ወቅት በርካታ ጉድለቶች መገኘታቸውን ሪፖርቱ ያመለክታል ብለዋል።

የአዋጭነት ጥናት ሳይቀርብ በጀት መፈቀድ የለበትም ያሉት ወይዘሮ መሰረት፤ ጉዳዩን አስመልክቶ የሚመለከታቸው ተቋማት በትኩረት ሊሠሩ እንደሚገባ አሳስበዋል።

የሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት ፕሮፌሰር ፍቅሬ ደሳለኝ በበኩላቸው፤ ይህ የክዋኔ ኦዲት በተቋሙ አዲስ በመሆኑ ብዙ ትምህርት እንደወሰዱ ገልጸው፤ በቀጣይም እነዚህን ክፍተቶች ለመቅረፍ እንሰራለን ብለዋል።

# ከ400 ሺህ በላይ ሕገወጦች ላይ ሕጋዊ ርምጃ ተወሰደ

**ታደሠ ብናልፈው**

አዲስ አበባ፡- በዘጠኝ ወራት በመዲናዋ ደንብን በተላለፉና ሕገ ወጥ ድርጊት በፈጸሙ ከ400 ሺህ በላይ ሕገወጦች ላይ ርምጃ መወሰዱን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የደንብ ማስከበር ባለሥልጣን አስታወቀ።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ደንብ ማስከበር ባለሥልጣን «በተጠናከር የህብረተሰብ ተሳትፎ የደንብ መተላለፎችንና ተያያዥ ሕገ ወጥ ድርጊቶችን እንቀንሳለን» በሚል ንቅናቄ ከክፍለ ከተሞችና ከወረዳዎች ከተውጣጡ የህብረተሰብ ክፍሎች በዘጠኝ ወር ሪፖርቱ ላይ ውይይት አካሂዷል።

በውይይቱ ላይ የባለሥልጣኑ የአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤት የሰላም፣ የፍትህና የመልካም አስተዳደር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ አቶ ሙሉነህ ደሳለኝ ባደረጉት መክፈቻ ንግግር፤ በመዲናዋ የመሬት ወረራ፣ ሕገ ወጥ ግንባታና ንግድ የመሳሰሉ የደንብ መተላለፎችና ሌሎች ውስብስብ ችግሮች አሉ። እነዚህን በማስወገድ በከተማዋ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ማህበራዊ እድገት ለማምጣት ከማህበረሰቡ ጋር በቅንጀት መስራት አስፈላጊ ነው ብለዋል።

ሕገ- ወጥ ግንባታ፣ የመሬት ወረራና ንግድ ከተማዋን የሚያውኩ ወንጀሎች መሆናቸውን



አቶ ሙሉነህ ደሳለኝ

የገለጹት አቶ ሙሉነህ፤ እነዚህን ተግባራት ለመከላከል ባለሥልጣኑ ለሚያደርገው እንቅስቃሴ ቋሚ ኮሚቴያቸው አስፈላጊውን ድጋፍ እንደሚያደርግ ገልጸዋል።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የደንብ ማስከበር ባለሥልጣን ዋና ስራ አስኪያጅ ሻለቃ ዘሪሁን ተፈራ በውይይቱ ላይ እንደተናገሩት፤ ማህብረሰቡን የሰላም ባለቤት ለማድረግ መጠነ ሰፊ ስራዎች ተሰርተዋል። ደንብና ሥርዓትን የማስከበር ሂደቱ ተጠናክሮ ይቀጥላል።

የባለሥልጣኑን የዘጠኝ ወር የስራ አፈፃጸም ሪፖርት ያቀረቡት የባለሥልጣኑ የጽህፈት ቤት ኃላፊ አቶ ተስፋሁን አሉላ፤ በመዲናዋ ከ400 ሺህ በላይ የሚሆኑ ደንብ የመተላለፍ ተግባራት በመፈፀማቸው ሕጋዊ እርምጃ እንደተወሰደባቸው ገልጸው፤ ደንብን በማስከበር ሂደት የተገኘ ከ22 ሚሊዮን ብር በላይ ለመንግሥት ገቢ ተደርጓል ሲሉ ገልጸዋል።

በጎዳና ንግድ ከ56 ሺህ በላይ፤ በመሬት ወረራ ወንጀል አንድ ሺህ የሚጠጉ፣ በእንስሳት እርድ ከ900 በላይ፣ በደረቅ ቆሻሻ ከ700 በላይ እና በሌሎች የደንብ ጥሰቶችን በፈጸሙ ሕገ ወጦች ላይ እርምጃ እንደተወሰደ ጠቁመዋል።

እንደ አቶ ተስፋሁን ገለጻ፤ ባለሥልጣን መስሪያ ቤቱ ከተቋቋመ ጊዜ ጀምሮ ደንብን የማስከበር ኃላፊነቱን እየተወጣ ይገኛል፤ የመሬት ወረራን፣ ሕገ ወጥ ግንባታንና ንግድን የመከላከል ስራ መሰራቱን በመግለጽ ይህም ተጠናክሮ ይቀጥላል ብለዋል።

ቁጥጥሩን ለማጠናከር ከ100 በላይ ለሚሆኑ ሰዎች የመረጃ ጥናትና አሰባሰብ ሥልጠና በመስጠት ወደ ስራ መሰማራታቸውን ገልጸው፤ በመዲናዋ ያለውን የደንብ ጥሰት ከመከላከል አኳያ መጠነ ሰፊ ስራዎች ተሰርተዋል ብለዋል።

አቶ ተስፋሁን አክለውም በመዲናዋ የሚታየውን የደንብ ጥሰትና ተያያዥ ሕገ-ወጥ ድርጊትን ለመከላከል ለማህበረሰቡ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራ ተጠናክሮ ይቀጥላል ብለዋል።




# ሩዝ ለመጀመሪያ ጊዜ በኤሌክትሮኒክስ መድረክ ለገበያ ቀረበ

**ማርቆስ በላይ**

አዲስ አበባ፡- ለመጀመሪያ ጊዜ የሩዝ ምርትን በኤሌክትሮኒክስ የግብይት መድረክ ማገበያየቱን የኢትዮጵያ ምርት ገበያ አስታወቀ።

የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በላከው መግለጫ እንዳስታወቀው፤ ምርት ገበያው በተያዘው ዓመት ወደ ገብይት ሥርዓቱ ከአካተታቸው የግብርና ምርቶች መካከል አንዱ ሩዝ ነው። በዚህም መሰረት ከትናንት በስቲያ ጀምሮ የሩዝ ምርት በኤሌክትሮኒክ የግብይት መድረክ ተገበያይቷል።

በቡሬ ቅርንጫፍ ደረጃ ሦስት ሩዝ በኩንታል ስድስት ሺህ 400 ብር መገበያየቱን ያተተው መግለጫው፤ በዕለቱም 60 ኩንታል ሩዝ በ383 ሺህ 232 ብር መገበያየቱ አብራርቷል።

ሩዝ ወደ ዘመናዊ ግብይት ሥርዓት በመግባቱ የአምራቾች ተጠቃሚነት የሚያሳድግ ነው ያለው መግለጫው፤ በተለይም ለአምራቾችና ለነጋዴዎች የገበያ መረጃን በበቂ ሁኔታ ለማሰራጨት የሚረዳ እንደሆነ ጠቅሷል። በዚህም አገሪቱ ወደ ውጭ የምትልከውን የምርት መጠን ለማሳደግና አምራችና ላኪውን በማገናኘት የተሳለጠ ግብይት መፍጠር የሚያስችል መሆኑን አመላክቷል።

ከመጋቢት 28 ቀን አንስቶ የሩዝ የገበያ መረጃ ለሕዝብ መቅረብ መቻሉን የገለጸው መግለጫው፤ አርሶ አደሩ ምርቱን በተሻለ ዋጋ ለመሸጥ የመደራደር አቅሙን የሚያሳድግ ነው። በዚህም አቅርቦቱን ለማስቀጠል የሚረዳ መሆኑን አመላክቷል።

በኢትዮጵያ ሩዝ የሚሊኒየሙ ሰብል በመባል የሚታወቅ መሆኑን በመጥቀስ የገቢና የወጪ ምርት ከሆኑት አንዱ መሆኑ ተገልጿል።

ሩዝ በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች በስፋት የሚመረት ሲሆን የ2008 ዓ.ም የምርት መጠኑ ከአንድ ነጥብ 32 ሚሊዮን ቶን እንደነበረ ታውቋል፤ በ2012 ዓ.ም ደግሞ ዓመታዊ መጠኑ ወደ ሁለት ሚሊዮን ቶን ሊያድግ መቻሉም ተመላክቷል።

በሩዝ አምራችነት ሽፋን፤ በትናንሽ ማሳዎች ላይ በአርሶ አደሮች 60 በመቶ የሚሸፈን መሆኑን ያተተው መግለጫው፤ በመንግሥት ሁለት በመቶና በግል አልሚዎች 38 በመቶ ድርሻ የሚይዙ መሆናቸውን አብራርቷል።

ምርት ገበያ የዘመናዊ ግብይት ሥርዓቱን አጠናክሮ በመቀጠል በ2015 በጀት ዓመት አምስት የምርት አይነቶችን ወደ ግብይት ሥርዓቱ አስገብቷል። በዚህም ሩዝ፤ ስንዴ፤ ኮረሪማ፤ እጣን፤ ግብጦና ባቄላ ናቸው።



አቶ አህመድ እድሪስ

# በኦሮሚያ ክልል ከ186 ቢሊዮን ብር በላይ የኢንቨስትመንት ፈቃድ ተሰጠ

**መዓዛ ማሞ**

አዲስ አበባ፡- የኦሮሚያ ክልል 186 ነጥብ 4 ቢሊዮን ብር ላስመዘገቡ 3 ሺህ 601 ባለሀብቶች የኢንቨስትመንት ፍቃድ መስጠቱን የኦሮሚያ ክልል ኢንቨስትመንት እና ኢንዱስትሪ ቢሮ ገለጸ።

የኦሮሚያ ክልል ኢንቨስትመንት እና ኢንዱስትሪ ቢሮ ኃላፊ አቶ አህመድ እድሪስ ሰሞኑን ለጋዜጠኞች በሰጡት መግለጫ እንዳሉት፤ ክልሉ 186 ነጥብ አራት ቢሊዮን ብር በላይ ላስመዘገቡ ባለሀብቶች የኢንቨስትመንት ፍቃድ ሰጥቷል። ፍቃዱ የተሰጣቸው ባለሀብቶች የኢንቨስትመንት መስፈርቱን አሟልተው የቀረቡ የሀገር ውስጥና የውጭ ባለሀብቶች፣ ዲያስፖራዎች፣ ወደ መካከለኛ ኢንተርፕራይዝ የተሸጋገሩ ወጣት ባለሀብቶች እና ሀብት ያላቸው አርሶ አደሮች እንዲሁም አርብቶ አደሮች ናቸው።

የባለሀብቶቹ የኢንቨስትመንት ጥያቄ ለክልሉ ኢንቨስትመንት ቦርድ ቀርቦ መጋቢት 22 ቀን ውሳኔ ማግኘቱን የገለጹት አቶ አህመድ፤ ቦርዱ ውሳኔ የሰጠባቸው አዲስ የግል ባለሀብቶች 1 ሺህ 680 ሲሆኑ ከነዚህ ውስጥ የማስፋፊያ ጥያቄ ያቀረቡ 92፣ አርሶ አደር እና አርብቶ አደር የሆኑ 1 ሺህ 502፣ የሕብረት ስራ ማህበራት 47፣ ጥቃቅን እና አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ 280 ናቸው።

ፍቃድ የተሰጣቸው ባለሀብቶች የሚሰማሩባቸው ዘርፎች የግብርና ምርቶችን በማቀነባበር፣ ማኑፋክቸሪንግ፣ እርሻ እና የአገልግሎት ዘርፎች ሲሆኑ ባለሀብቶቹ በሙሉ አቅም ወደ ስራ ሲገቡ ለ 679 ሺህ 730 ወጣቶች ቋሚ እና ጊዜያዊ የስራ እድል እንደሚፈጥሩ ኃላፊው ገልጸዋል።

ለባለሀብቶቹ በከተማ እና በገጠር 30 ሺህ 782 ሄክታር መሬት ለኢንቨስትመንት የቀረበ መሆኑን ጠቁመው፤ ለመሬቱ የመጀመሪያ የመሬት ኪራይ እና ሊዝ 3 ነጥብ 3 ቢሊዮን ብር ክፍያ እንደሚከፍሉ ተናግረዋል። ይህ የመንግሥትን የማስፈጸም አቅም ከፍ በማድረግ መሰረተ ልማትና ማህበራዊ ልማት ለመስራት እንደሚያግዝ ጠቁመዋል።

ባለሀብቶቹ ሙሉ ለሙሉ ወደ ስራ ሲገቡም 26 ነጥብ 3 ቢሊዮን ብር ክፍያ እንደሚፈጽሙም ገልጸዋል።

ለባለሀብቶቹ የሚሰጣቸው መሬት ሳይት ፕላን ተዘጋጅቶ የቀረበበት በከተማ ለኢንዱስትሪ ተብሎ የተዘጋጁ፣ በገጠር ለእርሻ ተብሎ የተዘጋጀው መሬት ከደን ነጻ መሆኑን ከደን እና አካባቢ ጥበቃ የተረጋገጠ እንደሆነ ኃላፊው አስታውቀዋል።

እንደ አቶ አህመድ ገለጻ፤ እነዚህ ባለሀብቶች ፍቃድ ከመሰጠቱ በፊት አስፈላጊ ቅድመ ሁኔታ እንዳሟሉ በሚገባ በመገምገም በጥብቅ ዲሲፕሊን ያለፉ ናቸው። ባለሀብቶቹ ልምድ ያላቸው፣ ሰርተው ውጤት ያመጡ፣ በቂ ገንዘብ ያላቸው ፣ መሬት ወስደው አጥረው የማያስቀምጡ እና መሬት ከወሰዱ በኋላ ወደ ስራ ገብተው የስራ እድል መፍጠር የሚችሉ መሆናቸውንና ለአገራችን የኢንዱስትሪ ዘርፍ መሰረት ሊጥሉ የሚችሉ ትልልቅ ባለሀብቶች እንደሆኑ ጠቁመዋል።

ፍቃድ ወስደው ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ላይ የሚሰማሩት ባለሀብቶች በ45 ቀን ውስጥ ከቢሮው ጋር ውል በመግባት መሬት በተቀበሉ በአራት ወራት ውስጥ ወደ ስራ መግባት እንደሚጠበቅባቸው የጠቆሙት አቶ አህመድ ፤ በተሰጣቸው ጊዜ ውስጥ ወደ ስራ ካልገቡ ውሳኔው እንደገና እንደሚታይ ገልጸዋል።

ቢሮው መሬት መስጠት ብቻ ሳይሆን ለባለሀብቶቹ አስፈላጊውን ሁሉ ድጋፍ በማድረግ ወደ ስራ ከገቡ በኋላ ማነቆዎች እንዳይገጥሟቸው ድጋፍ እንደሚያደርግላቸውም አብራርተዋል።

የኦሮሚያ ክልል ለኢንቨስትመንት ምቹ መሆኑን የጠቆሙት ኃላፊው ፤ በክልሉ ማንኛውንም ባለሀብት ዘርና ቀለም ሳይለይ የሚስተናገድ በመሆኑ ባለሀብቶች ወደ ክልሉ በመምጣት ኢንቨስት እንዲያደርጉ ጥሪ አቅርበዋል።

# የባንኩ ከወለድ ነፃ አገልግሎት የፋይናንስ አካታችነትን አሳድጓል

## - ንግድ ባንክ ለሲቢኢ ኑር ደንበኞቹ የኢፍጣር መርሃ-ግብር አካሄደ

**አማን ረሺድ**

አዲስ አበባ፡- የባንኩ ከወለድ ነፃ አገልግሎት የፋይናስን አካታችነትን በማሳደግ ረገድ ጉልህ ሚና መጫወቱን የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ፕሬዚዳንት አቶ አቤ ሳኖ ተናገሩ።

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የረመዷን ጾምን ምክንያት አድርጎ ለሲቢኢ ኑር ከወለድ ነፃ ደንበኞቹ “ልዩ የአብሮነት የኢፍጣር መርሃ ግብር” አካሂዷል።

የባንኩ ፕሬዚዳንት አቶ አቤ ሳኖ በመርሃ ግብር ላይ እንደገለጹት፤ ባንኩ እ.ኤ.አ 2013 ጀምሮ የሸሪዓ መርህን መሠረት ያደረገ ከወለድ ነፃ የባንክ አገልግሎት ሲሰጥ ቆይቷል።

ባንኩ አገልግሎቱን በመስጠቱ ከወለድ ነፃ የባንክ አገልግሎት ፈላጊዎችን ያካተተ የፋይናንስ ሥርዓትን ተግባራዊ እንዲያደርግ አስችሎታል ብለዋል።

ከወለድ ነፃ የፋይናንስ አገልግሎቱን በማቅረቡ ከባንክ አገልግሎት ርቀው የነበሩ ወገኖችን መድረስ መቻሉን የገለጹት አቶ አቤ፤ በቀጣይም የፋይናንስ አካታችነትን የሚያሳድጉ ተግባራትን አጠናክሮ እንደሚቀጥል አስታውቀዋል።



አቶ አቤ ሳኖ

የኢፍጣር መርሃ-ግብሩ ከወለድ ነጻ የፋይናንስ ደንበኞቹ ጋር ያለውን ግንኙነት ለማሳደግ እንደሚረዳ ጠቁመዋል።

ፕሬዚዳንቱ እንደገለጹት፤ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በአሁኑ ጊዜ ተቀማጭ ገንዘቡ 1 ነጥብ 15 ትሪሊዮን ብር ደርሷል። ከዚህም ውስጥ ከ85 ቢሊዮን ብር በላይ በሲቢኢ ኑር ከወለድ ነፃ የባንክ አገልግሎት የተሰበሰበ ገንዘብ ነው።

ይሁንና አሁንም የወለድ ነፃ ፋይናንስ እንቅስቃሴው በቂ አለመሆኑን ጠቁመው፤ የእምነት አባቶች በሲቢኢ ኑር ከወለድ ነፃ የባንክ አገልግሎት ተጠቃሚው ህብረተሰብ ገንዘቡን በባንክ ማንቀሳቀስና መበደር እንደሚችል ሊያስተምሩ ይገባል ብለዋል።

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የሲቢኢ ኑር ምክትል ፕሬዚዳንት አቶ ኑሪ ሁሴን በበኩላቸው እንደገለጹት፤ ባንኩ ለወለድ ነፃ የባንክ አገልግሎት ከፍተኛ ትኩረት በመስጠት የአገልግሎቱ ተጠቃሚ ደንበኞችን ፍላጎት ለማርካትና ተደራሽነቱን ለማስፋት እየሰራ ይገኛል።

ከወለድ ነፃ የተሟላ የባንክ አገልግሎትን በ 1 ሺህ 899 ቅርንጫፎች እየሰጠ መሆኑን የጠቆሙት አቶ ኑሪ፤ በ145 ቅርንጫፎች ሙሉ በሙሉ ከወለድ ነፃ አገልግሎቱን እየሰጠ መሆኑን አስታውቀዋል።

በረመዳን የፆም ወር የተቀላጠፈ የወለድ ነጻ አገልግሎቱን እየሰጠ ይገኛል። የኢፍጣር መረሃ-ግብሩ ከደንበኞች ጋር አብሮነትንና በሚያጠናክር መልኩ በማክበር በጋራ ጉዳዮች ላይ ለመወያየት ይረዳል ብለዋል።

ባንኩ እዝነትና መልካምነት፣ አገልጋይነትና መተሳሳብን መሰረት ያደረጉ የወለድ ነፃ የፋይናንስ አገልግሎቶቹን አጠናክሮ እንደሚቀጥል አስታውቀዋል።



አርሶ አደር ሁንዴ ፈይሳ



አርሶ አደር አበበ ሸዋንዳኘው

# የአርሲ ዞን 200 ሺህ ኩንታል ስንዴ ለውጭ ገበያ አቅርቧል

**ገመቹ ከድር**

ሄጦሳ፡- በዘንድሮ ዓመት 200 ሺህ ኩንታል ስንዴ ለውጭ ገበያ ማቅረቡን የአርሲ ዞን አስታወቀ። ከበጋ ስንዴ በሚገኘው ምርት ገቢያቸው እየተሻሻለ መሆኑን የዞኑ አርሶ አደሮች አስታውቀዋል ።

የሄጦሳ ወረዳ ከተር ገነት ቀበሌ ነዋሪው አርሶ አደር ሁንዴ ፈይሳ ከቀነኒሳ በቀለ ፖሊቴክኒክ ኮሌጅ በቴክኒክና ሙያ ትምህርት ተመርቆ ወደ ቤተሰቡ ተመልሶ እንደነበር በመግለጽ፤ ሕይወቱ በህብረተሰብ ላይ ጥገኛ ሆኖ እንደነበር ጠቁሟል። ነገር ግን ከሶስት ዓመት በፊት መንግሥት በዘረጋው የገጠር ልማት ኢንሼቲቭ በበጋ ሰንዴ ማምረት ሥራ ላይ ተሰማርቶ በአሁኑ ወቅት ውጤታማ መሆኑንም ተናግሯል።

እንደ አርሶ አደር ሁንዴ ገለጻ፤ በበጋ ስንዴ እርሻ ሥራ ቆይታው በአንድ ጥማድ እስከ አስራ ሶስት ኩንታል ፤በክረምት እስከ አስር ኩንታል በማምረት ላይ ይገኛል ።

በሶስት ዓመታት ውስጥ በተገኘ ሰንዴ ምርት ገቢውን በማሳደግ ከቤተሰብ ጥገኝነት በመላቀቅ ራሱን ችሎ እየተዳደረ መሆኑንም አብራርቷል።

የዩሪያ ማዳበሪያ እና ፀረ አረም ኬምካሎች እጥረት እና ነጋዴው በፈቀደ ዋጋ ምርት መግዛት እንዲሁም በበጋና በመኸር ጊዜ የትራክተርና ኮምባይነር ዋጋ ንረት ችግር መሆኑን አንስቶ ይህ ከተሻሻለ የአርሶ አደሩ ምርትና ምርታማነት በእጥፍ እንደሚጨምር ተናግሯል።

ቶርበን ኡሾ ቀበሌ አርሶ አደር አበበ ሸዋንዳኘው በበኩላቸው በበጋ ስንዴ እርሻ ኢንሼቲቭ ከመጀመሩ በፊት ጥቃቅን አትክልትና ፍራፍሬ ብቻ በመስኖ እርሻ ያለሙ ነበር። በዚህ ወቅት ለቤተሳባቸው የዓመቱን የእህል ፍጆታ ማሟላት እንዳልቻሉ ይናገራሉ። ባለፉት ሶስት ዓመታት የበጋ ስንዴ እርሻ በስፋት ማረስ ሲጀምሩ በአንድ ጥማድ 12 ኩንታል ስንዴ ምርት ማምረት ጀምረዋል። በዚህም ለቤተሰባቸው የሚያስፈልገውን ወጪ መሸፈን ችለዋል። በአሁኑ ሰዓትም በበጋና በክረምት በተከታታይ ስንዴን በማምረት ገቢያቸው መሻሻሉን ገልጸዋል።

የአርሲ ዞን ግብርና ጽህፈት ቤት ሃላፊ አቶ ገና መሀመድ መንግሥት በዘረጋው ገጠር ልማት ኢንሼቲቭ መሰረት በ23 ወረዳዎች በ 117ሺህ ሄክታር ላይ የበጋ ስንዴ እርሻ እየተካሄደ መሆኑን ጠቁመው፤ እስከ አሁን ድረስ በተሰሩ የበጋ ስንዴ ልማት ስራዎች የአርሶ አደሩ ምርትና ምርታማነት በመጨመሩ የአርሶ አደሩ ተጠቃሚነት እየጨመረ ነው ብለዋል።

ከዚህም በተጨማሪ እንደሀገር ለውጭ ገበያ ከቀረበው ስንዴ ዞኑ 200 ሺህ ኩንታል አስተዋጽኦ አበርክቷል ብለዋል።

በአሁኑ ሰዓት በበጋ ሰንዴ ምርት በደረሰባቸው ቆላማ አካባቢዎች በሄክታር 40 ኩንታል ስንዴ ምርት እየተሰበሰበ መሆኑን ገልጸው በተያዘው ዓመት አራት ነጥብ አምስት ሚሊዮን ኩንታል ስንዴ ለማምረት በትኩረት እየተሰራ መሆኑንም ጠቁመዋል።

እንደ አቶ ገና ገለጻ ፤ በባለሙያና በአርሶ አደሩ ላይ የታየው የአመለካከት ለውጥ ወደ ተግባር ተቀይሮ ለምርትና ምርታማነት መጨመር ጉልህ አስተዋጽኦ አበርክቷል። የልማት ኢንሼቲቩን ለማሳለጥ 4ሺህ ፓምፖች ፣172 ኮምባይነሮች፣ 481 ትራክተሮች በዞኑ አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛሉ ።

በኦሮሚያ ግብርና ቢሮ በጋ ስንዴ መስኖ ኢንሼቲቭ አስተባባሪ አቶ ጠሃ ሙሜ በበኩላቸው በአሁኑ ሰዓት የበጋ ስንዴ እርሻ 258 ሺህ 64 ሄክታር በላይ ደርሷል። እስከ ሳምንቱ መጀመሪያ ድረስ ከ 194ሺህ ሄክታር በላይ ስንዴ ምርት መሰብሰቡን ገልጸው ከተሰበሰበው አምስት ሚሊዮን 920 ሺህ ኩንታል ምርት ተገኝቷል ብለዋል። በተከታታይ ሳምንታት በዘነበው በልግ ዝናብ ምክንያት አሰባሰብ ሂደቱ መጓተቱን ገልጸው በሰው ጉልበትና በማሽነሪዎች በመታገዝ ምርቱን ለመሰብሰብ ጥረት እየተደረገ መሆኑንም ገለልጸዋል።

ዜና



አቶ ደመቀ መኮንን

# ለድርቅ ተጎጂዎች...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

እቅድና አፈጻጸም ላይ ተወያይቷል።

በውይይቱ የምክር ቤቱ ሰብሳቢ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ደመቀ መኮንን፤ በድርቅ ተጎጂ ለሆነው ማኅበረሰብ አስቸኳይ ምላሽ ለመስጠት እየተደረገ ያለው ርብርብ ውጤት እያመጣ መሆኑን ገልጸዋል።

ምክር ቤቱ ባለፈው አንድ ወር ያከናወነው የድርቅ አደጋ የአስቸኳይ ጊዜ ምላሽ መልካም መሆኑን ጠቁመው፤ በአሁኑ ወቅት በድርቅ ተጎጂ በነበሩ አካባቢዎች እየዘነበ ያለውን ዝናብ በአግባቡ ለመጠቀምና የጎርፍ አደጋ ጉዳት እንዳያደርስ መረባረብ እንደሚገባም አስታውቀዋል።

በጤና፣ የውሃ፣ የግብርና የመስኖና ቆላማ ተቋማት የተጀመሩ ሥራዎች ተጠናክረው እንዲቀጥሉ በተለይም የእርሻ መሣሪያዎች አቅርቦትና የመኖ ዝግጅት ትኩረት ሊሠጣቸው ይገባል ብለዋል።

በቀጣይም መረጃ ላይ የተመሠረተ የተረጂዎችን ቁጥር በመለየት ምላሽ የመስጠት ሥራን በቅንጅት ማጠናከር እንደሚያስፈልግም አንስተዋል።

ድርቅና ግጭት ያስከተሉትን ችግር ለመሻገር የሚያስችል አገራዊ አቅም መኖሩን ገልጸው፤ ሰብዓዊ ድጋፎችም ለተረጂዎች በቀጥታ መድረሳቸውን ማረጋገጥ የሁሉም የቤት ሥራ ነው ሲሉ ተናግረዋል።

መጪውን ጊዜ በአስተማማኝ ሁኔታ ለመሻገር ድርቅ ጎርፍና ግጭት ያመጧቸውን ፈተናዎች በመቋቋም ዕድሎችን በአግባቡ መጠቀም አለብን ብለዋል።

ለዚህም ከፌዴራል እስከ ክልል ሁሉም ተቋማትና አጋር አካላት ቅንጅታዊ አሰራርን እንዲያጠናክሩ አሳስበው ምክር ቤቱም አስፈላጊውን ድጋፍና ክትትል እንደሚያደርግ አረጋግጠዋል።

አቶ ደመቀ እንዳስታወቁት፤ በቀጣይም ለሰው ሰራሽና የተፈጥሮ አደጋዎች ዘላቂ መፍትሔ ሊቀመጥ ይገባል። በተለይም የቆላማ አካባቢ ልማት በመካከለኛ ዘመን እቅድ ውስጥ በአግባቡ መካተቱን ማረጋገጥ ያስፈልጋል።

ለአስቸኳይ ጊዜ የአደጋ ምላሽ መረባረብና የዘላቂ ጊዜ ፍኖተ ካርታ ማዘጋጀትም የቀጣይ ሥራችን ሊሆን ይገባል ብለዋል።

የብሔራዊ አደጋ ሥጋት አመራር ኮሚሽነር አምባሳደር ዶክተር ሺፈራው ተክለማርያም በበኩላቸው ከመጋቢት ጀምሮ እየተተገበረ ባለው የድርቅ አደጋ ምላሽ እቅድ ሰፊ ሥራዎች መከናወናቸውን ጠቅሰዋል።

በዚህም በኦሮሚያ፣ በሶማሌ፣ በደቡብና በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልሎች ድርቅ በተከሰተባቸው አካባቢዎች ሰብዓዊ ድጋፍ ተደራሽ እየተደረገ መሆኑን አንስተዋል።

የድርቅ ተጎጂ የሆኑ ከ 11 ሚሊዮን በላይ ዜጎች መኖራቸውን አንስተው የቅድሚያ ቅድሚያ ትኩረት ለሚሹ ከሦስት ሚሊዮን በላይ ዜጎች ፈጣን ምላሽ መስጠትን ጨምሮ በየደረጃው አስፈላጊው ድጋፍ እየተደረገ መሆኑን አስታውቀዋል።

በተለይም ድርቁና ሰሞኑን እየጣለ በሚገኘው ዝናብ በፈጠረው ጎርፍ ምክንያት የሰው ህይወት እንዳይጎዳ በተቋማዊ ቅንጅት እየተሠራ መሆኑን ጠቁመዋል።

የሴክተር መሥሪያ ቤት ኃላፊዎችም በጤና፣ በግብርና፣ በመስኖ፣ በውሃ ዙሪያ በትኩረት እየሠራን ነው። የበሽታ ሥጋት ክትትል፣ ህክምና፣ ውሃ ጉድጓድ ቁፋሮና ዘላቂ የቆላማ አካባቢ ሥራዎች ተጠናክረው ቀጥለዋል ብለዋል።

የእንስሳት በሽታ እንዳይከሰት መከላከልና በቂ መኖ አቅርቦትና በድርቅ ተጋላጭ የሆኑ አካባቢዎችን ዘላቂ መፍትሔ ለመስጠትም አቅጣጫ መቀመጡንም ገልጸዋል።

የፌዴራልና የክልል አስቸኳይ ጊዜ የአደጋ ምላሽ ማስተባበሪያዎች በተቀናጀ መልኩ እየሠሩ ሲሆን የጎርፍ አደጋ መከላከል ግብረ ኃይል ተቋቁሟል።

# «የክልል ልዩ ኃይልን...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

የሚመለከታቸው አካላት በጉዳዩ አስፈላጊነት ከመግባባት ተደርሶ የተጀመረ ስራ መሆኑንም ጠቁመዋል። በተጨማሪም አሁን በአገሪቱ ውስጥ ያለው ሰላም ከዚህ በፊት ከነበረው የተሻሻለ በመሆኑና ይህንን ትልቅ ተልዕኮ ለማስፈጸም የሚያስችል ሁኔታ በመፈጠሩ የመልሶ ማደራጀት ስራው ተጀምሯል ነው ያሉት።

ሠራዊቱን የማጠናከርና የማደራጀት ሥራው በጥናት ላይ የተመሰረተ መሆኑን የጠቀሱት ሚኒስትር ዴኤታዋ፤ የክልል ልዩ ኃይሎች በተለያዩ መዋቅሮች እንዲደራጁ የሚያስችላቸው ተግባራዊ ስራዎች እየተሰሩ ነው። መንግሥት ባስቀመጠው አማራጭ መሰረት የልዩ ሃይሎች ፍላጎትና ምርጫ ተከብሮላቸው የመልሶ ማደራጀት ስራው የሚከናወን ስለመሆኑ በመግለጫው አስታውቀዋል።

የመከላከያ ሠራዊትን መቀላቀል አንደኛው አማራጭ ሲሆን ይህም ትልቅ አገራዊ ጥሪ መሆኑ ተጠቅሷል። ሌላው የክልሉን የፖሊስ ሃይል መቀላቀል ወይም ወደ መደበኛ ኑሮው መመለስ የሚሉ አማራጮች የቀረቡ ሲሆን ወደ ሲቪል ለሚመለሱ የማቋቋሚያ በመንግሥት በኩል አስፈላጊውን ድጋፍ ለማድረግ ዝግጅት መደረጉን ሚኒስትር ዴኤታዋ ገልጸዋል።

የክልል ልዩ ሃይልን መልሶ የማደራጀት ሂደት በአንዳንዶች ዘንድ ግልጽ ባለመሆኑ የተሳሳቱ መረጃዎች እየወጡ ናቸው ያሉት ሚኒስትር ዴኤታዋ፤ ልዩ ሃሎችን መልሶ የማደራጀት ሂደት በሁሉም ክልሎች በተመሳሳይ እየተከናወነ መሆኑ ሊታወቅ ይገባል ብለዋል።

መርሃ ግብሩ ትጥቅን ከማስፈታት ጋር ምንም አይነት ግንኙነት የለውም፤ ይልቁንም ሁሉንም ኢትዮጵያዊ በእኩልነት ማገልገል የሚችል የአገርን ሉዓላዊነት በተሟላ ሁኔታ ማስጠበቅ የሚችልና ከአገር ውጭም ሊሰነዘሩ የሚችሉ ጥቃቶችን መመከት እንዲችል ታልሞ እየተሰራ ነው።

በሕወሓት በኩል በፕሪቶሪያው ስምምነት መሰረት ሙሉ ትጥቅ የሚፈታበት አሰራር ስላለ ይህም ያለምንም ማወላወል የሚከናወን ነው። ስለሆነም የሕወሓት ትጥቅ የማስፈታት ስራ ከሌሎች አገራዊ እቅዶች ጋር የሚገናኝ ሳይሆን ራሱን ችሎ የሚከናወን ስለመሆኑ ሚኒስትር ዴኤታዋ በመግለጫው አውስተዋል።

በሌላ በኩል በሸኔ ላይ እየተወሰደ ያለው እርምጃ አሁንም ቀጥሏል ያሉት ሚኒስትር ዴኤታዋ፤ በርካታ የሽብር ቡድን ታጣቂ ይዘዋቸው የነበሩ አካባቢዎች ነጻ በማውጣት መደበኛ የሕዝብ አገልግሎቶች ዳግም እንዲመለሱ እየተደረጉ ነው። ከምዕራብ ወለጋና ሆሮጉድሩ ወለጋ በስተቀር በሸኔ ምክንያት ተቋርጠው የነበሩ የትራንስፖርት አገልግሎቶች፣ ዳግም እንዲጀምሩ እየተደረገ ነው። መንግሥት ለቡድኑ በይፋ የሰላም ጥሪ ማድረጉን ተከትሎ በርካታ የሸኔ አባላት ትጥቃቸውን እያወረዱ ወደ ተሃድሶ ማዕከላት እየገቡ መሆኑን ገልጸዋል።

ሚኒስትር ዴኤታዋ፤ በሕገ ወጥ መንገድ ወደ ኢትዮጵያ ገብተው ወርቅና ሌች ማዕድናት ፍለጋ ላይ የተሰማሩ የውጭ አገር ዜጎችና ተባባሪዎቻቸው በተለያዩ ክልሎች በቁጥጥር ስር እንዲውሉ እየተደረገ ነው። እስካሁን 92 የውጭ አገር ዜጐች በሕገ ወጥ የማዕድን ንግድ ሥራ ሲንቀሳቀሱ በቁጥጥር ስር ውለው አስፈላጊው ምርመራ እየተደረገባቸው ነው። የስራ፣ የቪዛና የመኖሪያ ፈቃድ ሳይኖራቸው ወደ አገር ውስጥ በመግባት በሕገ ወጥ የወርቅና የማዕድን ማውጣትና ንግድ ስራ ላይ ተሰማርተው እየሰሩ በቁጥጥር ስር ውለዋል።

በጋምቤላ ክልል በሕገ ወጥ ንግድ 45 የውጭ አገር ዜጐች፣ ሶስት ኢትዮጵያውያን ከነኤግዚቢታቸው፣ በቤኒሻንጉል ክልል 47 የውጭ አገር ዜጐች፣ 9 የግል ማህበራትና 7 ኢትዮጵያውያን በጸጥታና ደህንነት ግብረሃይል በቁጥጥር ስር ውለው ምርመራ እየተደረገባቸው እንደሆነም ጠቁመዋል።

የአፈር ማዳበሪያ የአርሶ አደሩ ትልቅ የግብዓት ጥያቄ መሆኑን የገለጹት ሚኒስትር ዴኤታዋ፤ ለ2015/2016 የምርት ዘመን 12 ነጥብ 8 ሚሊዮን ኩንታል የአፈር ማዳበሪያ ግዥ ተፈጽሟል። ከባለፈው ዓመት የከረመው 2 ነጥብ 2 ሚሊዮን ኩንታል የአፈር ማዳበሪያ ተዳምሮ 15 ሚሊዮን ኩንታል የአፈር ማዳበሪያ ለአርሶ አደሩ ይሰራጫል። እስካሁን 1 ነጥብ 8 ሚሊዮን ኩንታል አፈር ማዳበሪያ ለአርሶ አደሩ ተሰራጭቷል ብለዋል።

# “ተመራማሪዎች በተለያዩ...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

አዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ ከውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር ጋር በመተባበር “8ኛው የውሃ ሀይድሮ ዲፕሎማሲና ኮሙኒኬሽን” በሚል ርእስ በትናንትናው ዕለት ፎረም ሲካሄድ ንግግር ያደረጉት የውሃና ኢነርጂ ሚኒስትር ዶክተር ኢንጂነር ሀብታሙ ኢተፋ፣ ባለፈው አንድ ዓመት በተለያዩ አካባቢዎች ባሉ የኢትዮጵያ የውሃ ሀብት አጠቃቀም ውጤታማ ሥራ ተሰርቷል ብለዋል።

በአርባምንጭ፣ በባህር ዳር እና በአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲዎች የኢትዮጵያ የውሃ ሀብት፣ አጠቃቀምና በሌሎች ሀገራት ያለው ልምድ ምን እንደሚመስል በተመራማሪዎች ልምድ በመለዋወጥ ውጤታማ ሥራዎች መሠራታቸውን ያብራሩት ሚኒስትሩ፤ ወደፊትም መንግሥት ከፍተኛ ድጋፍ በማድረግ በውሃ ዙሪያ ምርምሮች እንደሚደረጉ ገልጸዋል።

እንደ ሚኒስትሩ ገለጻ፣ የኢትዮጵያ ተመራማሪዎች በተለያዩ የዓለም ቋንቋዎች ስለ ኢትዮጵያና ስለ ሕዳሴው ግድብ እውነት ማውራት አለባቸው። ሚዲያዎች በውጭ ቋንቋዎች በስፋት ሊሰሩ ይገባል። ግብጾች በውሃ ሀብት ዘርፍ ላይ የሚያተኩሩ በርካታ ተቋማት አሏቸው፣ የሚመራመሩትም በዓባይ ውሃ ላይ ነው።

በአንጻሩ ኢትዮጵያ በውሃ ዙሪያ የሚያጠኑ ተቋማት የሏትም፤ በዘርፉ ያሉ ምሁራንም የተሰባሰቡ ባለመሆናቸው አቅም የላቸውም ያሉት ዶክተር ኢንጂነር ሀብታሙ፤ በሚቀጥለው ዓመት በውሃ ላይ የሚደረጉ የምርምር



ስራዎች ተጠናክረው እንደሚቀጥሉ ጠቁመዋል።

ኢትዮጵያ ያላትን የውሃ ሀብት እንዳትጠቀም ለዘመናት ከፍተኛ ጫና ሲደረግባት ነበር ያሉት ሚኒስትሩ፤ ከንጉሡ ጊዜ ጀምሮ ሁሉም የኢትዮጵያ መንግሥታት የዓባይን ውሃ ለመጠቀም ጥረት ሲያደርጉ ነበር፣ ይሁን እንጂ በሀሰት ትርክት እንዳትጠቀም መደረጓን ጠቅሰዋል።

በውሸት ትርክት ኢትዮጵያ የውሃ ማማ ናት በማለት ግድቦችን እንዳትገነባ ተደርጓል ብለውም፤ ይህን ትርክት ለመቀየር የዩኒቨርሲቲ ተቋማት ከፍተኛ የምርምር ስራ ሊሰሩ ይገባል ሲሉ አሳስበዋል።

ስለ ዓባይ ግድብ ብቻ ከማሰብና ከመቆጨት ምርምሮችን በማሳተም እውነታውን ለዓለም ማሳወቅና የተሳሳቱ ትርክቶችን ማስተካከል እንደሚገባም አክለው ተናግረዋል።

እንደ ሚኒስትሩ ማብራሪያ፤ ወደፊት በውሃ ሀብት ዙሪያ የዩኒቨርሲቲዎችን ቁጥር በማሳደግ በርካታ ምርምሮች ይደረጋሉ። የውጭ ሚዲያዎችን በመጠቀም ረገድ ግብጾች ከፍተኛ ስራ ይሰራሉ፤ በቀጣይ ኢትዮጵያም የውጭ ሚዲያዎችን ከመጠቀም አንጻር ጠንካራ ስራ ትሰራለች። የጋራ ተጠቃሚነትን መሰረት ያደረገ ዲፕሎማሲን መከተሏን አጠናክራ ትቀጥላለች።

የኢትዮጵያ ጎረቤት ያልሆኑ ነገር ግን የዓባይን ውሃ የሚጠቀሙ ሀገሮች የኢትዮጵያን ስም ሲያጠፉ ኑረዋል ያሉት ሚኒስትሩ፤ ኢትዮጵያ ውሃውን መጠቀም እንዳትችል የሚቻላቸውን ሁሉ ሙከራዎች ማድረጋቸውን አንስተዋል።

የኢትዮጵያ የውሃ ሀብት እውነታ ተደብቆ እንዳይቀር ከመንግሥት የዲፕሎማሲ ስራ ቀጥሎ ዩኒቨርሲቲዎች ተደጋጋሚ ፎረሞችን በማዘጋጀት ተጽዕኖ መፍጠር እንዳለባቸው አስገንዝበዋል።

# ቢሮው የመዲናዋን...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

ሚና አለው ያሉት ዶክተር ሂሩት፤ ኢፕድ ከተማን በማስተዋወቅ፣ መረጃ በመስጠት ሰፊ ሥራዎችን ሲሰራ ቆይቷል። ይህም ቢሮ የተቋቋመበትን ዓላማ የሚያጠናክር ከመሆን ባለፈ የሀገር ውስጥ ቱሪዝምን የሚያጎለብት ነው ብለዋል።

ድርጅቱ የ82 ዓመት ታሪክ የመሰነድ ልምድ ያለው ተቋም ነው ያሉት ዶክተር ሂሩት፤ አዲስ አበባ ከዛሬ ሃምሳ ዓመት በፊት እና አሁን ያለችበትን ሁኔታን በቀላሉ ለመረዳትና የቱሪዝም መስህቦቿን ታሪካዊ ዳራ በፎቶ ለሕዝብና ለቱሪስት ለማሳወቅ ከድርጅቱ ጋር በጋር መሥራት አስፈላጊ ነው። ይህም የአዲስ አበባ ቱሪዝም፣ ባህልና የኪነ ጥበብን ያሳድጋል ብለዋል።

ታሪካዊ የውይይት መድረኮችን ለማዘጋጀት የሚያስችሉና የበለጸጉ መረጃዎች በድርጅቱ ውስጥ ስለሚገኙ በቀጣይ የተለያዩ ፎቶ ኤግዚቢሽኖች እና መድረኮች በጋራ የሚዘጋጅበት ሁኔታ ይፈጠራል ሲሉም ተናግረዋል።

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ሥራ አስፈፃሚ አቶ ጌትነት ታደሰ በበኩላቸው፤ የአዲስ አበባ ከተማ ባህል፣ ኪነ -ጥበብና ቱሪዝም ቢሮ ሕዝብን ከሕዝብ የሚያቀራርብ፤ ኢትዮጵያዊነትን የሚገልጥ፤ ባህልን የሚያሳድግ ሥራ የሚሰራ ተቋም ነው። ቢሮው በቱሪዝምና በኪነ ጥበብ ያሉትን የከተማዋን ሀብቶች ከፍ አድርጎ ለማሳየትና ለማገልገል ይቻል ዘንድ ኢፕድ ከተቋሙ ጋር መስራቱ ከፍተኛ ደስታ ተሰምቶናል ብለዋል።

ኢፕድ ከከተማ አስተዳደሩ ጋር በርካታ ሥራዎችን ሲሰራ ቆይቷል ያሉት ዋና ሥራ አስፈፃሚው፤ ድርጅቱ በሥራዎቹ የከተማዋን ውበት ከመግለጽ ባለፈ በውስጧ ያለውን የጋራ እሴት በማስተዋወቅ በአንዳንድ ወቅት የሚፈጠሩ ችግሮችን ለመፍታት የሚያስችሉ ሥራዎችን በፎቶ ግራፍና በተለያዩ አማራጮች ሲሰራ ቆይቷል ብለዋል።

እንደ “ስለኢትዮጵያ” አይነት መድረክ ደግሞ ሕዝብን ከሕዝብ እና ሃሳብን ከሃሳብ የሚያቀራርብ ጉዳዮችን በመዳሰስ የሀገሪቷን ሰላም፣ አንድነትና እድገት አስተዋጽዖ የሚያበረክት ሥራዎችን ሲሰራ ቆይቷል። ይህም መድረክ በአዲስ አበባ በሰፊው የሚካሄድ ይሆናል። በዚህም ቢሮው ያሉትን ታሪካዊ መስህቦች የሚዳስስ ይሆናል ብለዋል።

# አገልግል

## የቅዳሜ መጽሔት



‹‹ኢትዮጵያ በግድቡ ግንባታ ላይ ያላትን አቋም አጠናክራ ማስቀጠል ይገባታል››

- ዶክተር ኢንጅነር ጥላሁን ኤርዱኖ የአዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ መምህር

ገጽ 6



የሴቶች የተሃድሶ እና የክህሎት ማበልጸጊያ ስልጠና ማዕከል ግንባታ

ገጽ 14



በቀና ልብ - በመልካም እጆች ስር

ገጽ 16

ባህል፣ ኪነ ጥበብ እና ቱሪዝም ቢሮ
አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ባህል፣ኪነጥበብ እና ቱሪዝም ቢሮ ጋር በመተባበር በየሳምንቱ የሚታተም

### አፍሪካዊቷ መልህቅ

# አዲስ አበባን ይጎብኙ

ኃይለማርያም ወንድሙ

አዲስ አበባ የዲፕሎማሲ ከተማ ከመሆኗም በላይ በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የአፍሪካ ኢኮኖሚክ ኮሚሽን እና የአፍሪካ ኅብረት ጽህፈት ቤቶችና የስብሰባ አዳራሾች ያላት ከተማ ናት:: ይህም ለዓለም አቀፍና ለአህጉር አቀፍ ስብሰባ የሚመጡ ሰዎችን መዲናዋን በማስጎብኘት በማዝናናት የውጭ ምንዛሪያቸውን አፍሰው እንዲሄዱ ማድረግ እንችላለን:: በዚህ ረገድ መዲናዋን በማስጎብኘት የረባ እንቅስቃሴ ሲደረግ አይታም:: የከተማው ባህል፣ ኪነጥበብና ቱሪዝም ቢሮ ይህንን ለመቀየር የሚያስችል መዲናዋን ለቱሪስቶች ለማስተዋወቅ የሚያስችል ሥራ ተያይዞታል::

የአዲስ አበባ ባህል ኪነጥበብና ቱሪዝም ቢሮ ባለፈው ሐሙስ መጋቢት 28 ቀን በአዲስ አበባ ቴክኖሎጂ ሙዚየም ዐውደ ጥናት አካሂዶ ነበር:: በዚሁ ዐውደ ጥናት ላይ ዶክተር ሂሩት ካሳው የአዲስ አበባ ባህል፣ ኪነጥበብና ቱሪዝም ቢሮ ኃላፊ፣ አቶ ፋሲል ገብረማርያም የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ ጽህፈት ቤት ተወካይ፣ አቶ አስፋው ለገሰ የባህል ዘርፍ ምክትል ኃላፊ፣ አቶ ሀፍተይ ገብረ እግዚአብሔር የቱሪዝም ዘርፍ ምክትል ኃላፊ፣ ዶክተር ቆንጂት ደበላ የሕዝብና ቦታዎች አስተዳደር ኮርፖሬሽን ዋና ሥራ አስኪያጅ፣ የመንግሥት መሥሪያ ቤት ተወካዮች እና ጉዳዩ የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ተሳታፊዎች ነበሩ::

ቢሮው በቱሪዝም ዘርፍ በ2015 ዓ.ም በልዩ ትኩረት ሲሠራባቸው ከነበሩ የማሻሻያ ሥራዎች መካከል የ Discover addis Ababa ማለትም አዲስ አበባን ይጎብኙ የሚለውን የሞባይል መተግበሪያ እና እንዲሁም የአዲስ አበባ ከተማ የቱሪዝም ብራንዱ ይጠቀሳሉ:: በሳይንስና ቴክኖሎጂ ሙዚየም የተካሄደው አውደ ጥናት ዓላማም አዲስ አበባን ይጎብኙ የሚለውን የሞባይል መተግበሪያ እና የመዲናዋን የቱሪዝም ብራንድ (አርማ/መለያ) ለማስመረቅ ነበር:: አዲስ አበባ 137 ዓመት የሆናት ከተማ ስትሆን በአራቱም የከተማዋ ዳርቻዎች እና አቅጣጫዎች ተፈጥሮአዊ ባህላዊ ኪነጥበባዊ መስህቦችና መዳረሻዎች አሏት::

ጥንታዊ ከመቶ ዓመት በላይ ያስቆጠሩ የቱሪዝም መስህቦች የተለያዩ ህንፃዎች የተለያዩ መስህቦችን የያዘች እንዲሁም በሁሉም ዘርፍ ሊባል በሚችል መልኩ የባህል የሃይማኖት የታሪክ የሀብት አርክቴክቸርና ሌሎችም የቱሪዝም መዳረሻዎች አሏት::

መዲናዋ የዓለም አቀፍና አህጉራዊ ጽህፈት ቤቶች መቀመጫ በመሆኗ እንዲሁም የብዙ አገሮች ኤምባሲዎች ስለሚገኙባት ደረጃቸውን የጠበቁ ትልልቅ ባለኮከብ ሆቴሎች በመኖራቸው ዝነኛው የኢትዮጵያ አየር መንገድም ብዙ ሰዎችን ከአገር አገር የሚያመላልስባት ስለሆነ ብዙ ቱሪስቶች የመሳብ ዕድል ያላት ከተማ ነች::

በዚህም ትልቅ የቱሪዝም ገቢ ማስገኘት የሚችሉ አዳዲስ እየተሠሩ ያሉ መስቦህች አሉ:: የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የአፍሪካ ኢኮኖሚክ ኮሚሽን ጽህፈት ቤት እና የስብሰባ አዳራሽ በተመሳሳይ የአፍሪካ ኅብረት ጽህፈት ቤትና መሰብሰቢያ አዳራሽ ያላት ትልቅ ከተማ ነች:: ይሄን ከተንከባከብነውና ካሳደግነው ብዙ የውጭ ምንዛሪ ማመንጨት የሚችል ለብዙ ዜጎችም የስራ ዕድል የሚፈጥር ነው:: አዲስ አበባን ታሪክና ቅርሶቿ እንደ ዘመናዊ ምቹና ንጹሕ ከተማ ደህንነቷ የተጠበቀ ከተማ ማድረግ ከዜጎች ይጠበቃል:: በእኔነት ስሜት ለከተማ በሠራንላት መጠን ሁሉም አዲስ አበቤያዊ በዓለም ዓቀፍ ደረጃ ከፍተኛ ተጎበኙ ከሚባል ከተሞች ደረጃ ልናደርሳት ብቻ ሳይሆን ከሁሉም ቀዳሚ ልናደርጋት እንችላለን::

የአዲስ አበባ ከተማ ባህል ኪነጥበብና ቱሪዝም ቢሮ ኃላፊ ዶክተር ሂሩት ካሳው ጉባዔውን ሲከፍቱ እንደተናገሩት፤ የአዲስ አበባን ቱሪዝም ብራንድ ለሚመለከታቸው የቱሪዝም ተዋናዮች እንዲሁም አዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ለሚኖሩ ቱሪዝም ላይና ተያያዥ ዘርፎች ላይ ለሚሠሩ ባለሙያዎች ማስተዋወቅ ያስፈልጋል:: የተቋም ባለቤቶች አጠቃላይ ዘርፉን ለሚመሩ አካላት አዲስ አበባ የቱሪዝም ብራንድን በግልፅና በጥልቀት ለማስተዋወቅና ይሔንን በደንብ ተገንዝቦ የራሳችንን አስተዋፅዖ ለመወጣት ወይም ሁሉም የአዲስ አበባ ቱሪዝም አምባሳደር ሆኖ ተልዕኮ ወስዶ ከተማዋን መስህብ ለማድረግ ነው::

ዲስከቨር አዲስ አበባ አዲስ አበባን ጐብኙ፣ ዕወቁ ወይም መርምሩ የሚለውን የቱሪዝም ፕሮሞሽንና ማርኬቲንግ ፕላትፎርምን ለማስተዋወቅ ስራዎች ተከናውነዋል:: የዓለም የቱሪዝምን ቀን ባከበርንበት ጊዜ የአዲስ አበባ የቱሪዝም ብራንድ እና የቱሪዝም ሎጎ የማስተዋወቅ ስራ ተሰርቷል::

አሁን ግን አዲስ አበባ ውስጥ የቱሪዝም ተዋንያንና ሌሎችም አካላት ይሄንን በመረዳት ብራንዱ የአዲስ አበባ ከተማ ብራንድ በመሆኑና ይህንን መጠቀም እንደ ግዴታ መቁጠር አለባቸው:: በተጨማሪም የማስተዋወቅ ስራው የዜግነት፣ የነዋሪነትና የሙያም ግዴታ ስለሆነ ይሄንን በደንብ ለማስረጽ ታስቦ የተዘጋጀ መድረክ መሆኑን አመልክተዋል::

ሁለተኛው ዲስከቨር አዲስ አበባ በአዲስ አበባ የሚገኙትን የቱሪዝም መዳረሻ ለማስተዋወቅና ወደ ገበያው ለማስገባት ሲባል የተፈጠረ የማስተዋወቂያ የማኅበራዊ ሚዲያና ድረገጽ ነው:: ማህበራዊ ሚዲያው ከጀመረ ሦስት ወር ሆኖታል:: አሁን ግን ይህንን በማስተዋወቅ በጋራ መሥራት ይኖርብናል:: ሁሉም የቱሪዝምና የሆቴል ተዋንያን እንዲሁም ሌሎችም የሚያካትት ስለሆነ እንድትጠቀሙበት ይሄንን ለማስተዋወቅና በጋራ እንድንሠራ የተጠራ ስብሰባ ነው:: ይህንን መሠረት በማድረግ ሁላችሁም የድርሻችሁን እንድትወጡ አደራ እላለሁ::

ኢትዮጵያ ቱሪዝም ከዓለም ቱሪዝም ድርጅት አመሠራረት በጣም በትንሽ ዓመት ልዩነት የተመሠረተ ነው:: ማስረጃዎች እንደሚያሳዩት በዓለም ላይ ቱሪዝም ሥርዓት ይዞ የተመሠረተው እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር በ1950 አካባቢ የሚል ነው፤ የኢትዮጵያ ደግሞ በ1954 ዓ.ም የተጀመረ ነው:: ነገር ግን እንደ ስማችንና እንደቱሪዝም መስህቦቻችን መጠቀም የቻልን አይመስልም:: በዚህ ረገድ ኬንያ የላቀ እንቅስቃሴ አድርጋለች::

በዕለቱ በተካሄደው ዐውደ ጥናት ላይ የተነሱትን ሀሳቦች ያደነቁ ተሰብሳቢዎች በሰጡት አስተያየት መዲናዋን ዞር ዞር ብሎ ለሚጎበኝ የሚሆን መጸዳጃ ለቱሪስቶች ቢዘጋጅ፤ መርካቶን በሙሉ ሊያሳይ የሚችል ከፍ ያለ ታወር ቢኖር ብለዋል:: አቶ ዳዊት ይፍሩ ከኢትዮጵያ ሙዚቀኞች ማኅበር በሰጡት አስተያየት ደግሞ ሙዚቃዎች የቱሪዝም መስህብ መሆናቸው መዘንጋት እንደሌለበትና ሙላቱ አስታጥቄ በግዮን ሆቴል ኢትዮ ጃዝ እንደሚያዘጋጅ ውጭ ሲሄድም ብዙ ሰዎች እንደሚያደንቁለት ጠቁመዋል:: የኢትዮጵያ ብቸኛ ባህላዊ ምግቦች እንጀራ፣ ቆጮ የመሳሰሉት እንዲሁም የጀበና ቡና አፈላል ስርዓታችን የቱሪዝም መስህብ ማድረግ እንደሚገባም ጭምር ተናግረዋል::

# የዘመን እንግዳ

# ‹‹ኢትዮጵያ በግድቡ ግንባታ ላይ ያሳትን አቋም አጠናክራ ማስቀጠል ይገባታል››

*ዶክተር ኢንጅነር ጥላሁን ኤርዱኖ*
*የአዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ መምህር*

ማህሌት አብዱል



ኢትዮጵያ ለዘመናት ስታልመውና ስታቅደው የነበረችውን የልማት ግብ ለማሳካት በታላቁ ወንዟ ላይ ግድብ ለመገንባት የመጀመሪያውን መሰረተ ድንጋይ በቤኒሻንጉል ጉምዝ ክልል ጉባ ላይ መሰረተ ድንጋይ ካስቀመጠች እነሆ 12ኛ ዓመቷን ይዛለች፡፡ የግድቡ ግንባታ የብስራት ዜና ከተሰማበት ዕለት ጀምሮ መላው ኢትዮጵያዊ ከዳር ዳር ተንቀሳቅሷል። በተለይም ለኢትዮጵያውያን ደግሞ ባይተዋር ሆኖ የቆየው የዓባይ ውሃን ለአገር እድገት ምሰሶ ለማድረግ መታሰቡ ሲሰማ ሁሉም የድርሻውን ለማበርከት አላመነታም፡፡ ከቅጠል ሻጪ እናት ጀምሮ እስከ ባለሃብቱ ድረስ የልማት ትልሙ እውን እንዲሆን በነቂስ ወጥቶ ድጋፉን አስመስክሯል፡፡ ይህ የዘመናት ቁጭት ሆኖ ህዝቡን አንገት ሲያስደፋ የኖረው ወንዝ ታዲያ ዛሬ ማረፊያውን አግኝቶ እውነተኛውን የልማት ብርሃን ሲያሳየን ከሁላችን ደጅ ቆሟል፡፡

በእነዚህ የልማት ዓመታት ታዲያ በውሃው ከፍተኛ ድርሻ ያላትን ኢትዮጵያ ከዳር ገፍተው ህዝቦቿ በድህነት እየማቀቁ እንዲኖር ለዘመናት ያለማንም ተጋሪ ብቻቸውን ሲጠቀሙ የኖሩት ጎረቤት አገሮች እጃቸውን አጣጥፈው አልተቀመጡም፡፡ ይልቁንም ከዚህ ቀደም ያደርጉት እንደነበረው ሁሉ የቅኝ ገዢዎቻቸው ክንድ ላይ ተንተርሰው አፍራሽ የፖለቲካ አስተሳሰባቸውንም ሆነ ተግባራቸውን ለእድገታቸው ምንጭ በሆነች አገር ላይ ለመወርወር አልቦዘኑም፡፡

ግና ችግር ያጎበጠው የኢትዮጵያ ህዝብ ለየትኛውም ችግር አልተንበረከከም፤ ይልቁንም መንግስትና ህዝቡ እጅና ጓንት ሆነው ጉዳዩን በጥበብ እና በብልሃት ያዙት እንጂ፡፡ በሃሰት የተገነባውን የዓለም ኢ-ፍትሐዊ አስተሳሰብ በትክክለኛ ሳይንስና ዲፕሎማሲ ለማክሸፍ ያደረጉትም ጥረት በብዙ መልኩ ሥኬታማ ሆኗል። እርግጥ አሁንም እነዚህ አገራት ዛሬም ድረስ የግድቡ አይቀሬነትን መቀበል ተስኗቸው የክፋት አጀንዳቸውን ለማስፈፀም ደፋ ቀና ማለታቸውን አላቆሙም፡፡ በተለይም የግድቡ ውሃ ሙሌት በተሳካ ሁኔታ በተከናወነ ቁጥር አፍራሽና ውሃ የማያነሱ አጀንዳዎችን እያነሱ የዓለም ህዝብ ማወዛገባቸውን ቀጥለዋል፡፡ ኢትዮጵያም በእነዚህ ዘመቻዎች ሳትንበረከክ ልማቷን አፋጥና አስቀጥላለች፤ ግድቡም ውሃ ከማቆር አልፎ ብርሃን ማሳየቱን ጀምሯል፡፡

አዲስ ዘመን ጋዜጣም የግድቡ ግንባታ የተጀመረበትን 12ኛ ዓመት ምክንያት በዛጋጀው ልዩ እትም በዚህና በሌሎችም አገራዊ ጉዳዮች ዙሪያ የአዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ መምህር የሆኑትን ዶክተር ኢንጅነር ጥላሁን ኤርዱኖ ጋር ቃለ-ምልልስ አድርጓል፡፡ እንደሚከተለው ይቀርባል፡፡

**አዲስ ዘመን፡- የዓባይ ግድብ ሙሉ ለሙሉ ተጠናቆ ሥራ ሲጀምር ለተፋሰሱ አገራት የሚኖረውን አስተዋፅኦ ያብራሩልንና ውይይታችንን እንጀምር ?**

**ዶክተር ኢንጅነር ጥላሁን፡-** የግድቡ መገደብ ከኢትዮጵያ ባሻገር የተፋሰስ አገራቱን በብዙ መልኩ እንደሚጠቅም ይታወቃል። ኢትዮጵያ ግድቡን ለማልማት ከያዘችው ፕሮግራም ጎን ለጎን በየዓመቱ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ዛፎች እየተተከሉ ተፋሰሱን ለማልማት እየተሰራ ያለውም ሥራ ከፍተኛ አስተዋፅኦ እያበረከተ ነው የሚገኘው። በዋናነትም በኢትዮጵያ በወንዞች ላይ የሚሰራውን ልማት የሚቃወሙት ሱዳንና ግብፅን በከፍተኛ ደረጃ የሚጠቅም ነው የሚሆነው። ኢትዮጵያ የጀመረቻቸው ተፋሰሱን የማልማት ስራዎች ለሱዳንና ለግብፅ ከፍተኛ ጠቀሜታ ያላቸውም መሆኑ ደግሞ በሳይንስ በተደረገ ጥናት የተረጋገጠ ነው።

ከዚህ በመለስ እነዚህ የልማት ስራዎች የኢትዮጵያን የአየር ሁኔታ የሚያስተካክል ነው የሚሆነው። ምክንያቱም ደግሞ በየዓመቱ የሚዘንበው ዝናብ መጠን እንዲጨምር ያደርጋል፤ በዚያው ልክ ምንጮች ይጎለብታሉ፤ የወንዞች የውሃ መጠን ከፍ እንዲል ከፍተኛ አስተዋፅኦ ይኖረዋል። የውሃው መጠን በደንብ ስለሚጨምር እነሱ ያለበቂ መሰረት የሚናገሩት ችግር ተጨባጭነት እንደሌለው ማሳያ ነው የሚሆነው። እንዳውም የበለጠ ለዚህ ልማት ተብሎ የሚወጣው ገንዘብና የሚደረገው ጥረት በሙሉ እነሱን የበለጠ ተጠቃሚ የሚያደርግ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ከዚህ አኳያ እንግዲህ ድንበር ተሻጋሪ ወንዞችን በመጠቀም ረገድ የዓለም አቀፍ ህጎች ምንድን ነው የሚሉት ?**

**ዶክተር ኢንጅነር ጥላሁን፡-** - ድንበር ተሻጋሪ ወንዞችን በሚመለከት የወጡ ዓለም አቀፍ ህጎች በሙሉ በዋናነት የሚያስምሩበት ጉዳይ ድንበር የሚሻገሩና አገራትን የሚያስተሳስሩ የውሃ ክፍሎችን በጋራ ማልማት እንደሚያስፈልግ ነው የሚደነግጉት። በጋራ ተጠቃሚነት ላይ የተመሰረተ የልማት ሥራ መስራት እንደሚገባም ያስገነዝባሉ እንጂ ለአንዱ አገር የመጠቀም መብት ሰጥቶ ለሌላው የሚከለክሉበት አንድም ዓለም አቀፍ የህግ አግባብም ሆነ መሰረት የለም። ችግሩ ያለው በብቸኝነት ለዘላለም ሲጠቀሙ የኖሩ ወይም ከዚያ የሚገኘውን ጥቅም ሁሉ ማጋበስ የለመዱ የታችኛው ተፋሰስ አገራት የተለያዩ ምክንያቶችን በየጊዜው በመፍጠር በጋራ ማልማትም አይፈልጉም፤ ሌላው ሲያለማም አይደግፉም፤ ሁልጊዜ እነሱ ብቻ መምራት ነው የሚፈልጉት፤ እነሱ የሚፈልጉት ብቻ መሆን አለበት የሚል ጥያቄ ነው የሚያነሱት። ይሁን እንጂ የዓለም አቀፍ ህጎች ሁሉም የድርሻውን ያህል በጋራ እየተስማመሙ እንዲያለሙ ነው የሚፈቅደው።

**አዲስ ዘመን፡- ወንዙን የሚያዋስኑ 11 ተፋሰስ አገራት ቢኖሩም የዓባይ ግድብን ጉዳይ የኢትዮጵያ፤ የሱዳንና የግብፅ ጉዳይ ብቻ አድርገው የሚያስቡ አካላት አሉ፤ ይህ ከምን የመነጨ ነው ብለው ያምናሉ ?**

**ዶክተር ኢንጅነር ጥላሁን፡-** በመሰረቱ በወንዙ ዙሪያ ያሉት 11 አገራት የላይኛው ተፋሰስ እና የታችኛው የተፋሰስ አገራት በመባል በሁለት ይከፈላሉ። በአብዛኛው የታችኛው ተፋሰስ አገራት የሚባሉት ግብፅና ሱዳን ናቸው፤ ምንአልባት ደቡብ ሱዳንንም ልንጨምር እንችላለን። ከሁሉ በላይ ግን ሱዳንና ግብፅ ናቸው የግድቡን ልማት በጣም ሲቃወሙና ሲወተውቱ የኖሩት። በጣም የሚገርመው ግን ምድር ከተፈጠረች ጀምሮ የአባይ ውሃ ከኢትዮጵያ ተነስቶ ወደ ግብፅ ሲፈስ ለብቻቸው ተቆጣጥረውት ሲጠቀሙ ስለኖሩ ኢትዮጵያ ውስጥ የሚደረግ ማንኛውም ከውሃ ጋር የተያያዘ ልማት እንደስጋት ነው የሚቆጥሩት። በተለይም ግብፅ ከአውሮፓና ከአሜሪካ ጋር ባላት ግኑኝነት የተነሳ የላይኛው ተፋሰስ አገራት በጋራ አቋም ሲይዙ ብዙ ጊዜ አይታይም። አብረው ለመቆም እንቅስቃሴ ቢጀምሩም እምብዛም ሲቀጥሉ አይታዩም ነበር።

እንደማስታውሰው 1993 ዓ.ም ነበር የላይኛው ተፋሰሱ አገራት ለማሰባሰብና ለማወያየት የቀድሞ የኢትዮጵያ ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ዘመቻ የጀመሩት። በዚያን ጊዜ የታየውም በአቋም ሲፈረካከሱ ነው፤ የጋራና የጠነከረ አንድነት የላቸውም። በወንዙ ተጠቃሚነት ዙሪያ ላይ ያላቸው አቋም በቅኝ ገዢዎቻቸው ልክ የተበታተኑ ሆነው ነው የሚገኙት። ኢትዮጵያ እንግዲህ እንደሚታወቀው ቅኝ ያልተገዛች ብቸኛ አገር ነች። ከዚያ አንፃር ብቻዋን እንድትቆም የማድረግ፤ ከግብፅና ከሱዳን ጀርባ እንግሊዞች በመኖራቸው ምክንያት፤ ደግሞም ህጉንም ሆነ ደንቡን ያረቀቁት እንዲሁም የፈረሙት እነሱ ስለሆኑ የቅኝ ተገዢዎቻቸውን የቀድሞ ክብር ጠብቆ ለማቆየት በኢትዮጵያ ላይ ጫና የሚያደርጉበት ሁኔታ አለ።

ከዚህ አንፃር እኔ እንዳውም የዓባይ ወንዝን ጉዳይ በሁለት ብቻ ሳይሆን በሶስት ጎራ ነው የማየው። ይኸውም ኢትዮጵያ ብቻዋን፤ ግብፅና ሱዳን በአንድ በኩል፤ በሶስተኛ ደረጃ አንድነት ያጡ እና ጠንካራ አቋም የሌላቸው ሌሎች የተፋሰሱ አገራት ጎራ ተሰልፈው ነው የሚታዩት። እናም ኢትዮጵያ በያዘችው አቋም ጠንክራ መሄድ እንጂ ከእነዚህ አካላት ጋር የሚደረግ ድርድርም አይሰራም፤ አብሮ ማልማትም የሚሆን እንዳልሆነ ባለፉት ዓመታት በተጨባጭ አይተነዋል። በተለይም ግብፅና ሱዳን ‹‹እኛ እንደፈለግነው እኛ እንደምንላችሁ አድርጉ ነው›› የሚሉት። ለምሳሌ ግብፅ ውስጥ ጤናማ አመለካከት ያለው ፖለቲካዊ ስርዓት ቢኖር ኖሮ ‹‹ከኢትዮጵያ ጋር አብረን እንስራ፤ እኛም እናግዝ፤ ወደፊት ስጋትም ቢኖር አብረን ስጋቱን አብረን እንወጣለን፤ እናንተ

# የዘመን እንግዳ

## ‹‹ኢትዮጵያ በግድቡ ግንባታ ...

በምታደርጉት ልማት ድርሻ ይኑረን›› ብለው በጠየቁ ነበር::

ከዚህ አንፃር እንደአገር በተፋሰሱ አገራት ተጠቃሚነት ዙሪያ ሁለት ዓይነት ዘመቻ ኢትዮጵያ ስታደርግ ቆይታለች። አንደኛው ዘመቻ በጣና ላይ ካጋጠመው የእንቦጭ አረም ጋር ተያይዞ ያለውን ችግር ስንናገር እነሱ ይስቁ ነበር። ግን ደግሞ አልተረዱትም እንጂ የሳቁት በራሳቸው ላይ እንጂ በእኛ ላይ አይደለም:: እኛ አነሰም በዛ አረሙን ለማስወገድ ታግለናል፤ በተቻለ መጠንም ከከፍተኛ ስጋትነት ያወረድነው ይመስለኛል። እኔ እንዳውም በወቅቱ በተለያዩ ማህበራዊ ሚዲያዎች ላይ በዚህ ጉዳይ ላይ ብዙ ፅፌያለሁ:: ማገዝ እንዳለባቸው፤ እዚያ ዳር ቆመው ውሃውን አትንኩብን ከማለት ይልቅ ውሃው እና አካባቢው በተፈጥሮ ሲጎዳ ቆመው ማየት እንደሌለባቸው፤ እንዳውም ማድረግ ያለባቸው ዶላራቸውን ኢትዮጵያን ለማውደም ለሚንቀሳቀሱ ኀሬላቸው ከመመገብ እዚህ መጥተው ዛፍ ቢተክሉ የበለጠ እንደሚጠቅማቸው በግልፅ ፅፌያለሁ፤ ብዙ ተከራክሬያቸዋለሁ:: በዚህ ዙሪያ ‹‹የግብፅና አጋሮቿ ጠላትነት እስከመቼ?›› መፅሐፍም ፅፌያለሁ::

ስለዚህ ኢትዮጵያ በግድቡ ግንባታ ላይ ያላትን በአቋማ ጠንክራ ማስቀጠል ይገባታል፤ ህዝቦቿን አስተባብራ በአንድነቷ እስከቆመች ድረስ አንድ ቀን የእነዚህ አገራት እንቅስቃሴያቸው ትክክል እንዳልሆነ፤ ራሳቸውንም መለስ ብለው የሚያዩበት ሁኔታ መፈጠሩ አይቀርም:: እኔ እንዳውም መፅሐፌ ውስጥ እንደጠቀስኩት ምንአልባት በኛ ዘመን ይህ ነገር እውን ላይሆን ይችላል፤ ግን ደግሞ እነዚህ ሶስቱ አገራት የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ በትክክል ስራ ከጀመረ በኋላ ምንም እንደማይጎዳቸው ሲያረጋግጡ የሚፀፀቱ ወይም በሰሩት ስራ የሚያዝኑ ይመስለኛል። ስለዚህ በዚያ ጊዜ ምንአልባት ድንበር አፍርሰን በጋራ የምኖርበት ሁኔታ ሊፈጠር ይችላል።

በጥርጣሬ መተያየቱ ተወግዶ በህዝቦች መካከል መፈቃቀር፤ ድንበር አጥፍቶ የጋራ አገር እስከ መመስረት መድረስ ይችላሉ የሚል እምነት ነው ያለኝ:: ምክንያቱም ይህ የውሃ ሃብት የጋራ ነው፤ ህዝቦችን ሊያቀራርብ እንጂ ሊያቃርን አይችልም። ችግሩ ያሉት በጥቂት ባለስልጣናት ዘንድ ነው። ለምሳሌ ብዙ የግብፅ ምሁራን ከኢትዮጵያ ጎን የተሰለፉ አሉ:: እነዚህ ምሁራን የግድቡ መገንባት ግብፅን ሆነ ሱዳንን በምንም መልኩ አይጎዳም ብለው በግልፅ ሲናገሩ ይደመጣሉ:: እንዳውም እኮ ከዚህ በፊት አስዋን ግድብን ሲገድቡ ትልልቅ አሜሪካዊና እንግሊዛዊ የሆኑ ሁለት ምሁራን ‹‹ ትክክል ያልሆነ ግድብ፤ ትክክለኛ ባልሆነ ሥፍራ ›› በማለት ነው የገለፁት። ከዚያ ይልቅም በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገነባ ግድብ ነው ለግብፅ የበለጠ የሚጠቅመው ብለው ነው የተነተኑት::

እነሱ ሁልጊዜ የሚያነሱት ያልተጨበጠ ክርክር ‹‹ሆድ ሲያውቅ ዶሮ ማታ!›› እንደሚባለው ነው። እነሱ በገዛ አገራቸው ውስጥ ከአባይ አጀንዳ በስተቀር የሚያነሱት ፖለቲካ የላቸውም፤ ኢትዮጵያ ግን በሰላም ግድቧን እያስቀጠለች ትገኛለች:: ስለዚህ የሚያነሱት አጀንዳ ሲያጡ እነዚህ ወታደራዊ መንግስታት ሁልጊዜ ህዝባቸውን የሚመግቡት ‹‹ኢትዮጵያ ውሃ ልታሳጣችሁ ነው፤ እኛ እዚያ ላይ ነው የምንሰራው›› የሚል ሃሳብ በማንሳት የህዝቡን አቅጣጫ ለመቀየር ጥረት ሲያደርጉ ይስተዋላሉ:: ይህም ማለት ህዝባቸው እንዳይሰራ፤ ለዲሞክራሲ፤ ለፍትህ፤ ለእኩልነት የሚያደርገውን ትግል ለማጨናገፍ ሲሉ ሁልጊዜ የአገራቸው ችግር ውሃ ብቻ እንደሆነ እንዲያስብ አድርገውታል::

**አዲስ ዘመን፡- ከዚህ አንፃር ታዲያ ግብፅ ሁልጊዜ የውሃ እጥረት ያጋጥመኛል በማለት የምታነሳው ስጋት ምን ያህል ተጨባጭነት አለው ማለት ይቻላል ?**

**ዶክተር ኢንጅነር ጥላሁን፡-** የትኛውም ሳይንስ



> በተፋሰሱ አገራት ተጠቃሚነት ዙሪያ ሁለት ዓይነት ዘመቻ ኢትዮጵያ ስታደርግ ቆይታለች። አንደኛው ዘመቻ በጣና ላይ ካጋጠመው የእንቦጭ አረም ጋር ተያይዞ ያለውን ችግር ስንናገር እነሱ ይስቁ ነበር። ግን ደግሞ አልተረዱትም እንጂ የሳቁት በራሳቸው ላይ እንጂ በእኛ ላይ አይደለም

በኢትዮጵያ ውስጥ የሚደረግ ግድብ ግንባታ በግብፅም ሆነ ሱዳን ላይ የውሃ እጥረት እንደሚያስከትሉ አላረጋገጠም። ከዚያ ይልቅ እንዳውም በየጊዜው የሚፈተኑበትን የጎርፍ አደጋ ይከላከልላቸዋል እንጂ የውሃ ችግር አያመጣም። እውነተኛ ችግራቸው የውሃ እጥረት አይደለም፤ የዓለም አቀፍ ፖለቲካ ድራማ አካል ነው:: ኢትዮጵያ ያለችበት ቀጠና ይህንን ያህል ህዝብና ግዛት ይዛ ገና እንድትወጣ፤ በልማት እንድታድግ አይፈለግም፤ ይልቁንም እየኮረኮሙ፤ እየደኸየችና እየተበጣጠሰች አገር ሆና አንድነቷን አጥታ እንድትቆይ ነው:: በአካባቢው ላይ እንደፈለጉ መፈንጨት ስለሚፈልጉ ከዚያ ጋር የተያያዘ ፖለቲካ ነው እንጂ በምን ተዓምር ነው ኢትዮጵያ ውስጥ ዛፍ መትከል ግብፅንና ሱዳን የሚጎዳው ? ከግድቡ ጋር ተያይዞ እኮ በቢሊዮን የሚቆጠሩ ዛፎች ተተክለዋል። እነዚህ የተተከሉ ዛፎች በምድር አየር ንብረትና ስነምህዳር ሁኔታ ላይ ከፍተኛ አስተዋፅኦ እንዳላቸው ይታወቃል::

በተለይ የወንዞች ውሃ መጠን እንዲጨምር በማድረግ ረገድ የላቀ ሚና እንዳለው እሙን ነው። ታዲያ ይህ እየታወቀ እንዴት አድርጎ ነው ግብፅና ሱዳንን ሊጎዳ የሚችለው ? ደግሞም እኮ የአባይን ውሃ ማንም ላቁመው ቢል ሊያቆመው የሚችለው አይደለም:: ይሄ እኮ ቀላል የሂሳብ ስሌት ነው። ይሄ ወንዝ እኮ በግብፅ እና በሱዳን ድርሻ ላይ ምንም ነገር ሳንነካ የተቆፈሩ ጉድጓዶች ከሞሉ በኋላ ውሃ ዝም ብሎ መከመር የማይቻል ነው:: እኛ ውሃ እየገደብን እንኳን ስንት ጊዜ ነው በጎርፍ እየተጥለቀለቁ ያሉት? ስለዚህ እነሱ የውሃ እጥረት ያጋጥመናል የሚሉት ስጋት ውሸትና መሰረት የለሽ ነው::

በአጠቃላይ በዚህ ጉዳይ ላይ ዓለም አቀፍ ፖለቲካው፤ የአገራቱ የውስጥ ችግር ወደ እኛ እያመጡብን ነው እየተቸገርን ያለነው:: በነገራችን ላይ ግብፅ ከፍተኛ የሆነ የከርሰ ምድር ውሃ ካላቸው አገራት ግንባር ቀደም ስትሆን ከዚህ በተጨማሪም በቀይ ባህር እና በሜዲትራኒያን ባህርም የተከበበች ናት::

በሌላ በኩል አባይ ወንዝም ቢሆን የኢትዮጵያ ዝናብም ሆነ ምንጮቹን በምንም ተዓምር ኢትዮጵያውያን ገድበው ሊያቆማቸው አይችሉም። ነገር ግን ይሄ አይነቱ የፖለቲካ አጀንዳቸው ግን ከውሃ እጥረት ጋር የሚያይዙት ነገር ለትዝብት የሚዳርጋቸው ነው የሚመስለኝ:: በመሆኑም እነዚህ አካላት አንድ ጊዜ ቆም ብለው ሊያስቡበት ይገባል። በተለይም ህዝባቸው ‹‹ከዚህ በኋላ ይበቃል!›› ሊላቸው ይገባል። ይሄ ድራማ ከእንግዲህ መቆም አለበት ብሎ መነሳት አለበት::

ኢትዮጵያ ለታችኞቹ አገራት የምትሰጣቸው የህይወት መሰረት የሆነ ውሃ ነው:: ስለዚህ ለኢትዮጵያ መታዘዝ፤ ለኢትዮጵያ ችግር መቆርቆር፤ ኢትዮጵያ ውስጥ ለሚያጋጥሙ ድርቅን በጋራ ለመከላከል ጥረት ማድረግ ነው የሚገባቸው:: ምክንያቱም ኢትዮጵያ ውስጥ ድርቅ በመጣ ቁጥር ውሃ ሊያንስ ይችላል። በመሆኑም ከዚያ ውጭ የሚያደርጉት እንቅስቃሴ ከንቱ ነው። እስካሁን ባለው ታሪክም አንድም ጊዜ የውሃ እጥረት አጋጥሟቸው አያውቅም፤ የፖለቲካ አጀንዳቸውን እያስፈፀሙ ያሉት:: ከዚህ ጋር በተያያዘ ኢትዮጵያውያን ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ ይህንን መከራከር፤ ማስረዳት በእውቀት ላይ የተመሰረተ ግንዛቤ ማስበጥ ይገባቸዋል የሚል እምነት ነው ያለኝ::

**አዲስ ዘመን፡- ኢትዮጵያ በያዘችው አቋም መቀጠል አለባት ሲሉ ምን ማለቷ ነው ? ምንስ መስራት ይጠበቅባታል ብለው ያምናሉ ?**

**ዶክተር ኢንጅነር ጥላሁን፡-** አስቀድሜ እንዳልኩት ኢትዮጵያ የግድቡን ግንባታ በማጠናቀቅም ሆነ የመልማት መብት በሚመለከት፤ እንዲሁም በዚህ ጉዳይ የያዘችውን አቋም ላይ ፈፅሞ ልታመነታ አይገባም:: ጠላት የሆኑ አገራት በሙሉ የኢትዮጵያ ወዳጅ መሆን የሚችሉት ግድቡን ጨርሰን ምንም ጉዳት እንዳላመጣባቸው ስናረጋግጥላቸው ብቻ ነው:: አገራችንን ለማሳደግ እና ማልማት ለማምጣት ይህ ግድብ ብቻ ሳይሆን ሌሎች ሶስት ግድቦች ያስፈልጉናል:: እነዚህን ግድቦች እየሞላን በሄድን ቁጥር በከንቱ ኢትዮጵያን ሲያጠቁ መኖራቸውን፤ የኢትዮጵያን አንድነት ለማፍረስ ሲንቀሳቀሱ መቆየታቸውን እየተገነዘቡ ይመጡ እና ጥሩ ወዳጆቻችን ይሆናሉ ብዬ ነው የማምነው:: ይህን ካረጋገጥን በስተቀር፤ ግድቡን ሞልተን ቶሎ ብለን ወደ ልማት ካልገባን እነሱ ይተኙልናል ብሎ ማሰብ የዋህነት ነው::

መንግስት ይፋ እንዳደረገው ሁላችንም አስተዋፅኦ በማድረግና አሻራችንን በማሳረፍ ቶሎ ጨርሰን ዝም ብለን ቁጭ ብለን ማየት ይገባናል። ደግሞም እነዚህ አገራት ፖለቲካቸው እየተበላሸ ስለመጣ በተቻለ አቅም ሁለቱም አገራት የፖለቲካ ችግራቸውን ወደ ሌላ አቅጣጫ አዙረው ሊሞክሩት የሚችሉት ነገር ስለሚኖር መንግስታችን በደንብ ሊጠነቀቅ ይገባል። በመሆኑም እንደዚህ አይነት ነገሮችን የኢትዮጵያ መንግስት ንቁ ሆኖ፤ በጊዜ ሁኔታውን ገምግሙ ዝግጅት ማድረግ መቻል አለበት:: በመሆኑም በሁሉም ድንበሮቻችንን አካባቢ ጥበቃ ማድረግ ወሳኝ ነው:: በተጨማሪም የውስጥ ችግሮቻችንን በተቻለ ፍጥነት መፍታት ይገባናል::

**አዲስ ዘመን፡- ስለጡን ማብራሪያ በዝግጅት ክፍሉ ስም ከልብ አመሰግናለሁ::**

**ዶክተር ኢንጅነር ጥላሁን፡-** እኔም ሃሳቤን እንድገልፅ እድሉን ስለሰጣችሁኝ ላመሰግን እወዳለሁ።

# ማህደረ ጤና

# የጥርስ ህመምና የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የጥርስ ህክምና ማዕከል

**እፀገነት አክሊሉ**

ከህመሞች ሁሉ የከበደ ህመምን የሚያስከትል ነው። የስቃይ ስሜቱ ደግሞ የሚብሰው ሲመሽና ሌሊት ነው ይላሉ በችግሩ ውስጥ ያለፉ ሰዎች። ይህ የህመም ስሜት ደግሞ እየባሰ ሲሄድ ሰዎችን አቅላቸውን አስቶ በራሳቸው ላይ ተገቢ ያልሆነ እርምጃም እንዲወስዱ የሚያስገድድ ስለመሆኑም ይነገራል - የጥርስ ህመም።

የጥርስ ህመምን ያለፈበት ወይም በችግሩ ውስጥ ያለ ሰው ብቻ ነው የሚያውቀው፤ የሚረዳውም የምትለን የጥርስ ህክምና ምን ስሜት አለው ብለን ለስራ በተንቀሳቀስንበት የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የጥርስ ህክምናና ትምህርት ቤት ያገኘናት ታካሚ ናት።

ታካሚዋ ወይዘሪት ሀረግ መንግስቱ ትባላለች። ጥርሷን ለረጅም ጊዜ ያማታል። ነገር ግን ህክምናው ከባድና ውድ ነው ሲባል ስለምትሰማ ደፍራ አልመጣችም። ይልቁንም በቤት ውስጥ የተለያዩ ማስታገሻዎችን እየወሰደች ቆይታለች። ነገር ግን እነዚህ የምትወስዳቸው ማስታገሻዎች ዘላቂ መፍትሔን ሊሰጧት ስላልቻሉ አሁን ጨክና ወደ ህክምና ተቋም መምጣትን መርጣለች።

"የጥርስ ህመም በጣም ከባድና ሁሉንም ነገር የሚይዝ ነው። በተለይ ሲመሽና ሌሊት ችግሩ ከፍተኛ ይሆናል። ነገር ግን በህክምናውና በጤና አጠባበቁ ላይ ያለን ግንዛቤ እጅግ አናሳ በመሆኑ ሲያመን እንኳን ወደ ህክምና ተቋም አንሄድም። እኔም ያጋጠመኝ ይኸው ነው። አሁን ወደ ህክምን መጥቻለሁ። መፍትሔም አገኛለሁ ብዬ አስባለሁ" ትላለች።

የልጇ የጥርስ ህመም እረፍት የሚነሳት ወይዘሮ ሰናይት አሰፋ በበኩሏ የጥርስ ህመም በጣም ከባድ ነው። ልጇ ገና የሁለት አመት ሆና ነው መታመም የጀመረችው። የእሷ ህመም ደግሞ እሷን ብቻ ሳይሆን መላ ቤተሰብን ነው የሚረብሸው ትላለች።

በህጻናት ጥርስ ጤና አጠባበቅ ዙሪያ ግንዛቤ ስላልነበረኝ ብሎም የመጀመሪያ ልጄ ስለሆነች የጠቀምኳት መስሎኝ የማደርጋቸው አንዳንድ ያልተገቡ ነገሮች ልጄን ገና በለጋነት እድሜዋ በጥርስ ህመም እንድትሰቃይ ምክንያት ሆኗል። እንደ እኔ ባለማወቅ የልጆቻቸውን ጥርስ ለሚያበላሹ ወላጆች በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ ትምህርት ሊሰጣቸው ይገባል ባይ ናት።

አሁን ልጇ የዘጠኝ ዓመት መሆኗን ገልጻ በእነዚህ ሁሉ ዓመታት ግን ጥርስ በሽተኛ ስለሆነች ሁሌም ለቅሶ፣ ህመም ከማሳለፏም በላይ የምትፈልገውን ምግብ እንደልቧ መብላት አለመቻሏ እንደሚያሳዝናት ትናገራለች። አሁን ላይ ረጅም የህክምና ክትትል እያደረገች ከስር ከስርም መወገድ ያለባቸው እየተወገዱ አዳዲስ ጥርሶች እየበቀሉላት ስለሆነ ህመሙ መቀነሱንም ታብራራለች።

አዎ የጥርስ ህመም ክብደቱ ይህንን ያህል ነው። ሁሉንም የህብረተሰብ ክፍል የሚያጠቃ መሆኑ ደግሞ ችግሩን ያወሳስበዋል። ከምንም በላይ ደግሞ በአገራችን ህክምናው ውድና በቀላሉ ሁሉም ሰው ሊያገኘው የሚችል አለመሆኑ ሰዎች ከህመማቸው ጋር እንዲቆዩ ያስገድዳቸዋል።

ይህም ቢሆን ግን የጥርስ ህክምናን ለዘመናት በተመጣጣኝ ዋጋ ሲሰጥ የኖረው የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የጥርስ ህክምና ማዕከል ዛሬም ስራውን አጠናክሮ እንደቀጠለ ነው።

የጥርስ ህክምና ክፍሉ አንጋፋ ከመሆኑ አንጻር በአገሪቱ ብቸኛ የጥርስ ህክምና ተቋም ሆኖም አገልግሏል። በወቅቱም አድቫንስድ ዲፕሎማ ያላቸውን ነርሶች በመቀበል በጥርስ ህክምና ሙያ በማሰልጠን ነው የማስተማር ስራውንም "ሀ" ብሎ የጀመረው። በመቀጠልም በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ስር በመጠቃለል የትምህርት አይነቱን ወደ መጀመሪያ ዲግሪ በማሳደግ ለመጀመሪያ ጊዜ 231 ተማሪዎችንም



ዶክተር ዳንኤል ሹካሬ

**የጥርስ ህክምና እንኳንስ በእኛ አገር በአደጉት አገራትም በጣም ውድ የሚያደርገው ነገር የሚፈልገው ቁሳቁስ ውድ መሆን ነው**

አስመርቋል። ከዛ በኋላም በ2003 ዓ.ም የ"ዶክተር አፍ ዴንታል ሔለዝ" ዘርፍ የ6 ዓመት ፕሮግራም በመዘርጋት 120 የሚጠጉ የጥርስ ህክምና ዶክተሮችን አስመርቋል።

የትምህርትና የህክምና ተቋሙ የሚያሰለጥናቸው የህክምና ባለሙያዎች በመላው አገሪቱ በግልም በመንግስትም የህክምና አገልግሎት መስጫዎች ላይ ህብረተሰቡን በማገልገል ላይ ናቸው።

እኛም ተቋሙ አሁናዊ ሁኔታውን፤ እንዲሁም ለህብረተሰቡ እየሰጠው ያለውን ግልጋሎት በተመለከተ ከትምህርት ክፍሉና የህክምና አገልግሎት ዋና ዳይሬክተር ዶ/ር ዳንኤል ሹካሬ ጋር ቆይታ አድርገናል።

ዶ/ር ዳንኤል በሙያቸው የጥርስ ህክምና ሰርጅን ሲሆኑ የፊት። የአፍ ውስጥና የመንጋጋ ቀዶ ህክምና ስፔሻሊስት ናቸው።

ማዕከሉ በትምህርት ክፍሉ ውስጥ የጥርስ ህክምና አገልግሎትን ለህብረተሰቡ እየሰጠም ይገኛል። ማንኛውም የጥርስ ህመም ያለበት ሰው ሪፈር በመያዝ አልያም በቀጥታ መጥቶ አገልግሎቱን ማግኘት ይችላል። በዚህ ውስጥም ጤና መድህን ያላቸው ሰዎች አገልግሎቱን ሲያገኙ፣ ሌሎች የህብረተሰብ ክፍሎች ደግሞ በተመጣጣኝ ዋጋ አገልግሎቱን የሚያገኙ ይሆናል። የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ደግሞ በዱቤ ህክምና አገልግሎቱን ያገኛሉ።

እንደ ዶ/ር ዳንኤል ገለጻ ማንኛውም ሰው ከሆስፒታልም ይሁን ከጤና ጣቢያ ሪፈር ይዞ መጣም አልመጣም፣ የህክምና ተቋሙ በእርዳታ ባገኛቸው ውድ የሆኑ የህክምና መገልገያዎች እየታገዘ ተመጣጣኝ በሆነ ክፍያ የሚፈልገውን አገልግሎት ያገኛል። በዚህም የጥርስ ሙሌት። የጥርስ ስር ህክምና። ድዱ የሸሸ ጥርስ ማከም። የቆሸሸን በማሸን ማጠብ። ወጪ ገቢ ጥርስ መስራት። የተበላሹና ከአገልግሎት ውጭ የሆኑ ጥርሶችን መንቀል። የተበላሹና የአበቃቀል ችግር ያለባቸው ጥርሶችን የማስተካከል ስራዎችን ሁሉ ይሰራል። ከዚህ በተጨማሪም ተቋሙ በተለያዩ ቦታዎች የአፍና የጥርስ ጤና አጠባበቅ ትምህርቶችን የመስጠት ስራም እንደሚያከናወን ያብራራሉ፡፡

የትምህርትና የህክምና ማዕከሉ አነስተኛ የቀዶ ጥገና ስራዎችን የሚሰራ ሲሆን፣ ከተቋሙ አቅም በላይ የሆኑትን ደግሞ በጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ከአጥንት ህክምና ጋር በመተባበር ይሰራል። ከተቋሙ ባለሙያ በመላክም በቅዱስ ጴጥሮስና ምኒልክ ሆስፒታሎች ጋር እንደሚሰሩ የተናገሩት ዶ/ር ዳንኤል ይህንን ስራውን ሲሰራም የህብረተሰቡን አቅም ባገናዘበ ሁኔታ መሆኑንም አክለው ገልፀዋል፡፡

እንደ ዶ/ር ዳንኤል ገለጻ ተቋሙ ከተወሰኑ ዓመታት በፊት አገልግሎቱን ይሰጥ የነበረው ከ15 እስከ 20 ብር በማስከፈል ነበር። አሁን ግን ከግብዓቶች ዋጋ መጨመር ጋር በተያያዘ መንግስት የፌደራል ሆስፒታሎች በሙሉ ዋጋ ማስተካከያ ያድርጉ ባለው መሰረት አሁን ላይ ሁሉንም አገልግሎቶች 1መቶ ብር ከፍሎ ካርድ በማውጣት 694 ብር በሚደርስ ወጪ አገልግሎት ማግኘት እንደሚቻል ነው ያብራሩት። ምናልባት እነዚህን አገልግሎቶች በግሉ ሴክተር ላይ በሶስት እጥፍ መክፈል ያስፈለግ ይሆናል። በዚህም ምክንያት ተቋሙ ህብረተሰቡን በአቅሙ እያገዘ ነው ማለት ይቻላል ብለዋል።

ተቋሙ የሚሰራው ስራ ሁለት ይምሰል እንጂ ሶስትና አራት ነው የሚሉት ዶ/ር ዳንኤል ማስተማር። የህክምና አገልግሎት። የጥናትና ምርመር ስራዎችን ያከናውናል። ሌላውና የመጨረሻው ደግሞ ማህበረሰብ ተኮር አገልግሎቶችን መስጠት ሲሆን በዚህም ቡታጅራ በመሄድ ከባቱ ሆስፒታል ጋር በመተባበር የህክምና አገልግሎት የመስጠትና የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርቶች እንደሰጡም ያነሳሉ።

አሁን ላይ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ራስ ገዝ ይሆናል የሚባል ሁኔታ ስላለ ይህ የትምህርትና የህክምና ተቋም ምን ዓይነት ቅርጽ ይዞ ነው መቀጠል ያለበት የሚለውን በተመለከተ ከኮሌጁም ሆነ ከዩኒቨርሲቲው አመራር ጋር በመነጋገር ላይ ነው። በዚህም በግቢው ውስጥ ተጨማሪ ህንጻዎችን በመገንባት አገልግሎቱ ሳምንቱን ሙሉ እስከ ማታ ድረስ የሚሆንበትን ሁኔታ የማመቻቸት፤ በሌላ በኩልም የአገልግሎቱን ጥራት ከፍ በማድረግና አገር ውስጥ የማይሰጡ የነበሩትን እንደ ኢምፕላንት ያሉ ህክምናዎችን ለመስጠት እየተነጋገርን ነው ይላሉ።

በሌላ በኩልም ትምህርት ክፍሉ የተማሪዎች ቅበላ መንግስት የሚመድባቸውን ብቻ የነበረ መሆኑን አስታውሰው፤ ከዚህ በኋላ ግን ከፍለው ለመማር የሚፈልጉ ተማሪዎችን ተቀብሎ ለማስተማር ዝግጅት እያደረገም ስለመሆኑ ተናግረዋል።

የትምህርትና የህክምን ክፍሉ የተለያዩ ስራዎችን እየሰራ ህብረተሰቡንም እያገዘ ከመሆኑ ጋር በተያያዘ በርካታ ችግሮችም ያጋጥሙታል የሚሉት ዶ/ር ዳንኤል ከነዚህም መካከል ትልቁን ቦታ የሚይዘው በበላይ ኃላፊዎች ዘንድ ያለው አረዳድና ለተቋሙ እየተሰጠ ያለው ትኩረት ነው።

ስለ ጥርስ ህክምና ምንነትና ስራው የሚፈልገውን ነገር ያለማወቅም ሌላው ችግር ነው።የጥርስ ህክምና እንኳንስ በእኛ አገር በአደጉት አገራትም በጣም ውድ የሚያደርገው ነገር የሚፈልገው ቁሳቁስ ውድ መሆን ነው። ይህ ሁኔታ ደግሞ በእኛ ተቋም ላይም ትልቅ ችግር ነው። የህክምና መሳሪያዎቹ በቀላሉ በአገር ውስጥ ያለመገኘታቸው ከውጭ ለማስመጣት ደግሞ ከፍ ያለ አቅምን መጠየቃቸው ስራው በሚፈለገው ልክ እንዳይሰራ አድርጎታል። በሌላ በኩልም ተጠግነው እንኳን አገልግሎት መስጠት የሚችሉትን መጠገን ላይ ክፍተቶች አሉ።

እነዚህን ችግሮች ለመፍታትም ተቋሙ በተቻለው አቅም፣ በተለይም የህክምና ግብዓቶቹን ለማሟላት በእርዳታና በሌሎች መንገዶች ለማግኘት እንደሚሞክር ገልጸው በጉዳዩ ላይ ያለውን የህብረተሰቡን፣ እንዲሁም የከፍተኛ አመራሮችን አመለካከት ሊቀይሩ የሚችሉ ስልጠናዎችን በመስጠት ግንዛቤው እንዲሰፋ እየተደረገ ነው። በእኛ አገር ስለ ጥርስና አፍ ጤና አጠባበቅ የእውቀት ደረጃው ዝቅ ያለ ነው። በሌሎች አገሮች ልጆች ተወልደው ጥርስ ማብቀል ከጀመሩበት ጊዜ ጀምሮ ክትትል ይደረግላቸዋል። ቢያንስ በዓመት ሁለት ጊዜም ጥርሳቸው ይመረመራል። የሚያስፈልገው ጥንቃቄና ያለበት ደረጃም ይነገራቸዋል። ችግሮች ቢኖሩ እንኳን በቶሎ ተደርሶባቸው የሚታከሙ ነው የሚሆነው። በተቃራኒው እኛ አገር ህጻን፣ አዋቂው ወደ ህክምና የሚመጣው ሲታመም ብቻ ነው። አንዳንዶች እንደውም ኢንፌክሽን ተፈጥሮባቸው አብጠው ነው የሚመጡት። በመሆኑም ለከፋ ጉዳት ላለመዳረግ የአፋችንን ጤና በሚገባ መጠበቅ። ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ ወደ ጤና ተቋም ሄዶ መታየት ያስፈልጋል። በተለይም ልጆች ከሚመገቡት ምግብና ከሚወስዷቸው ጣፋጭ ነገሮች አንጻር ምንጊዜም ከምግብ በኋላ ጥርሳቸውን እንዲያጸዱ ማድረግ፤ በጣም ከተቻለ ደግሞ ለብ ባለ ውሃ ውስጥ ጨው በመጨመር እንዲጉመጠመጡ ማገዝ እንደሚያስፈልግ ተናግረዋል።

ዶክተር ዳንኤል አክለውም ይህንን ሁሉ አልፎ ግን ህመም ሲያጋጥም በቶሎ ወደ ህክምና ተቋም ለመሄድ መሞከር ነገሮች ሳይባባሱ ለማከም ያግዛል። ነገር ግን ለህመሙ ጊዜ መስጠት አፋችን ውስጥ እንዲሁም ድዳችን ላይ ኢንፌክሽን ተፈጥሮ ለተባባሰ ችግር የመጋለጥ እድሉ ከፍ ያደርገዋልና ጥርስን በአግባቡ መንከባከብ፤ ከዚያ አልፎ ግን ህመም ሲሰማ በቶሎ ወደ ጤና ተቋም መሄድ አስፈላጊ መሆኑን ይመክራሉ።

". . . ህጻናት ከተወለዱ ከስደስት ወራት በኋላ ጥርስ ማብቀል ይጀምራሉ። እስከ ሁለት ዓመት ተኩል ድረስ የልጅነት ጥርሳቸው በቅሎ ያልቃል። ስድስት ዓመት ጀምሮ ደግሞ የህጻንነት ጥርሳቸውን እየነቀሉ ቋሚ ጥርስ እያበቀሉ ይሄዳሉ። በመሆኑም እያንዳንዱ ወላጅ ልጆቹን የጥርሳቸውን ጤና በምን መልክ መንከባከብ እንዳለባቸው ከልጅነታቸው ጀምሮ ማስተማር፤ ችግር ሲኖር ደግሞ ሀኪም ዘንድ ማምጣት፤ በተቻለ መጠን ጣፋጭ ነገሮችን መመጠን ያስፈልጋል" በማለት ምክራቸውን ለግሰዋል።

# የኢፌዴሪ መንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት በወቅታዊ አገራዊ ...

ከ15ኛው ገፅ የዞረ

ከዚህ ቀደም ጥልቅ ጥናቶች ተካሂደዋል። የሀገራችንም የክልሎች ነባራዊ ሁኔታም ከግምት ውስጥ ገብቶ ጭምር ነው ተግባራዊ እየተደረገ የሚገኘው።

ሁለተኛው ጉዳይ፣ ይህ መርሃ ግብር ትጥቅን ከማስፈታት ጋር ምንም አይነት ግንኙነት የሌለው መሆኑ ነው። ይህንን ሂደት ትጥቅ ከማስፈታት ጋር ለማገናኘት እና ለማያያዝ እና በህብረተሰቡ ዘንድ የተለያዩ ውዥንብሮችን ለመፍጠር የሚደረገው ጥረት ፍጹም የተሳሳተ እንደሆነ ሁሉም ህብረተሰብ ሊገነዘበው ይገባል። ጉዳዩ ትጥቅ ከማስፈታት ጋር ግንኙነት የለውም። እንዲያውም የሁሉም ኢትዮጵያዊ የሆነ፣ ሁሉንም በእኩልነት ማገልገል የሚችል፣ የሀገርን ሉዓላዊነት በተሟላ ሁኔታ ከሀገር ውስጥም ከሀገር ውጭ ሊሰነዘሩና ሉዓላዊነትን ሊዳፈሩ ከሚችሉ ጥቃቶች መከላከል የሚችል ጠንካራ የመከላከያ ሃይልን ለመገንባት የሚያስችል ትልቅ ሀገራዊ ጥሪና እድል ስለመሆኑ በዚሁ አጋጣሚ ተገቢ የሆነ ግንዛቤ መስጠት ያስፈልጋል። መገናኛ ብዙሃንም በዚሁ ላይ ሊሰሩበት እንደሚገባም ማንሳት እፈልጋለሁ።

### ሕወሓትን በተመለከተ

በተለያየ መልኩ ከሕወሓት ጋር ተያይዞ የሚነሱ ጥያቄዎች አሉ። በሕወሓት በኩል በፕሪቶሪያው ስምምነትና ከዚያም በኋላ በተለያዩ በተካሄዱ ምክክሮች መሰረት ሕወሓት ሙሉ ለሙሉ ትጥቅ እንዲፈታ እየተደረገ እንደሆነ ሊታወቅ ይገባል። ይህም ራሱን ችሎ የሚከናወን ተግባር ነው። በራሱ የተቀመጠለት የሂደት አግባብ አለ። ጉዳዩ የሚከናወንበት መርሃ ግብርም እንደዚሁ በግልጽ ተመላክቷል። ከዚህ በፊትም ይከናወን እንደነበረው ይህንኑ ጉዳይ የሚከታተሉና የሚታዘቡ ዓለም አቀፍ ታዛቢዎች ጭምር ያሉበት መሆኑንም እዚህ ላይ ማስገንዘብ ያስፈልጋል።

የሕወሓት ትጥቅ የመፍታት ሂደት በተፈረመው ስምምነት መሰረት ያለማወላወል የሚፈጸም መሆኑን ማስገንዘብ ይገባል። ከሌሎች አገራዊ ዕቅዶች ጋር የሚገናኝ ሳይሆን ራሱን ችሎ በራሱ መርሃ ግብር የሚከናወን እንደሆነ መገንዘብ ያስፈልጋል፤ ከሌሎች አገራዊ እቅዶች ጋርም የሚጣረስ እንዳልሆነም ግልጽ ማድረግ ተገቢ ነው።

በአጠቃላይ የክልሎችን ልዩ ኃይሎች መልሶ የማደራጀት መርሃ ግብር በከፍተኛ ጥንቃቄ የሚካሄድ መሆኑን ሁሉም ሰው ሊገነዘበው ይገባል። በሁሉም ክልሎች የሚፈጸምና በከፍተኛ ጥንቃቄና መግባባት ጭምር የሚካሄድ በመሆኑ፤ በሂደቱ ወቅት በሁሉም ክልሎች ላይ ሰላምና ደህንነትን ለማረጋገጥ በተለይም አንዳንድ ቦታዎች ላይ የጸጥታ ስጋት ያለባቸው እንደዚሁም ሌሎች የማህበረሰብ ጥያቄዎች ባሉባቸው አካባቢዎች ላይ ሰላምና ደህንነትን ማረጋገጥ እንዲቻል የሀገር መከላከያ ሠራዊት በሁሉም ቦታዎች ላይ ስምሪቶችን ወስዶ እየተንቀሳቀሰ ይገኛል። ዋና ዋና ተልዕኮዎች ተሰጥተውት ይህንኑ ተግባራዊ ወደማድረግ ሂደት እየገባ ነው የሚገኘው። ስለዚህ በዚህ በኩል የሚፈጠር ምንም አይነት ክፍተት አይኖርም ማለት ነው።

ይህ የክልል ልዩ ኃይሎችን መልሶ የማደራጀቱ ተግባር ጠንካራ ሉዓላዊነቷ የተከበረ፣ ከአገር ውስጥም ሆነ ከውጭ ሊሰነዘሩባት የሚችሉ የተለያዩ ጥቃቶችን በአግባቡ መመከት የምትችል ኢትዮጵያን ለመፍጠር የሚደረገው ጥረት ዋነኛ አካል መሆኑን ሁሉም ማህበረሰብ ሊያውቀው ይገባል። ከዚህ በተቃራኒው ትልቁን አገራዊ ስዕል ወደ ጎን በመተው፣ የተለያዩ ሀሰተኛ መረጃዎች እየወጡ ነው። እነዚህ ሀሰተኛ መረጃዎች መውጣታቸውን ይቀጥላሉ፤ ምክንያቱም በዚህ ሂደት የዜጎችን ሰላምና ደህንነት በመንሳት ሂደት ውስጥ የሚጠቀሙ ብዙ አካላት መኖራቸው መረሳት የለበትም።

ስለዚህ በእነዚህ አካላት የሚሰነዘሩ ሀሰተኛ መረጃዎችን፣ የጥፋት መልዕክቶችንና በአጠቃላይ ሕዝብን ለማደናገር፣ አቅም የሌሌለው እንዲሁም የተበታተነ ኃይል ያላት ኢትዮጵያን ለመፍጠር የሚደረጉ ጥረቶች መሆናቸውን ከግምት ውስጥ በማስገባት በመንግሥት ደረጃም ይሁን በሁሉም ክልሎች ውስጥ በተመሳሳይ እየተፈጸመ የሚገኘው ይህ ትልቅ አገራዊ ተልዕኮ እንዲፈጸምና ውጤታማ እንዲሆን ከማድረግ አንጻር ማህበረሰቡ እነዚህን የተሳሳቱ መረጃዎችን ባለመስማት ባለማመንም ጭምር ሃላፊነቱን መወጣት አለበት። በመንግሥት በኩልም ትክክለኛ መረጃዎች በየጊዜው ወደ ሕብረተሰቡ እንዲደርሱ የተለያዩ ጥረቶች መደረጋቸውን የሚቀጥሉ ይሆናል።

ከአገር ውስጥም ከውጭም ክፉዋን በሚያስቡ ኃይሎች፣ የተጋለጠች ኢትዮጵያን ማየት በሚፈልጉ ኃይሎች ደግሞ የተመቸች ኢትዮጵያን ላለመፍጠር የሚደረግ ትልቅ ጥረት አለና የሚነዙት የተሳሳቱ መረጃዎች እነዚህን ሃይሎች የሚያግዙ መሆናቸውን ከግምት ውስጥ በማስገባት ሕዝቡም ሆነ የጸጥታ ኃይሉ ሊደናገር አይገባውም። እነዚህን ሂደቶች በተመለከተ በሁሉም ክልሎች ውስጥ የሚካሄደው መርሃ ግብር ሂደት ምን ይመስላል የሚለውን በተከታታይ ለህብረተሰቡ የምናደርስ ይሆናል።

### አሸባሪው ሸኔ እና ተያያዥ ሥራዎች

ከሰላምና ጸጥታ ጉዳይ ጋር በተያያዘ የሚነሳው ሌላ ጉዳይ የሸኔን ጉዳይ ነው፤ በዚህ የሽብር ቡድን ላይ ከዚህ በፊት የተጀመሩት የተለያየ ወታደራዊ እርምጃዎች አሁንም ቀጥለዋል። በተለይ የመከላከያ ሠራዊት ቦታዎቹ ላይ ከገባ በኋላ በጣም ከፍተኛ የሆነ ውጤት እየተገኘበት መሆኑ ይታወቃል። በጣም በርካታ የሆኑ የሽብር ቡድኑ ይዟቸው የነበሩ አካባቢዎች አሁን ላይ ነፃ እየወጡ ነው። ነፃ የወጡትም ወደ መደበኛ የሕዝብ መገልገያ አገልግሎቶች ዳግም እንዲመለሱ የተለያዩ ስራዎች እየተሰሩ ነው የሚገኙት።

በተለይም ነፃ የወጡት አካባቢዎች ላይ ትምህርት ቤቶች፣ የገጠር ሆስፒታሎች፣ ጤና ጣቢያዎች ሌሎችም መንግሥታዊ መዋቅር አገልግሎት የሚሰጥባቸው የተለያዩ አገልግሎት መስጫዎች ተመልሰው የማደራጀቱ ስራዎች ብዙ የኦሮሚያ አካባቢዎች ላይ እየተከናወነ ነው የሚገኘው። ከምዕራብ ወለጋና ከሆሮ ጉርዱ በስተቀር በሌሎች አካባቢዎች ላይ በተለይ ደግሞ በሸኔ ምክንያት ተቋርጠው የነበሩ የተለያዩ የትራንስፖርት አገልግሎቶችም ዳግም እንዲጀመሩ እየተደረገ ነው የሚገኘው።

ከዛ ባሻገር ደግሞ እንደሚታወቀው መንግሥት ለዚህ ቡድን በይፋ የሰላም ጥሪ ማቅረቡ የሚታወስ ነው። ይህን ተከትሎ እንግዲህ በርካታ የሸኔ አባላት ትጥቃቸውን እያወረዱ ወደ ተሃድሶ ማዕከላት እየገቡ ነው የሚገኙት። የሰላም ጥረቱን ለማስተባበርም በብሄራዊ ደረጃ የተቋቋመው ኮሚቴ በርካታ ስራዎችን እየሰራ ነው የሚገኘው። በማህበረሰቡ በኩልም የሚቀርቡ ጥያቄዎች አሉ። እነዚህ ጥያቄዎች ዋነኛው የሰላም ሂደቱ በሀገር ሽማግሌዎች፣ በአባ ገዳዎች እንዲከናወን ብዙ ጥያቄዎችና ግፊቶች አሉ። ይህንን ደግሞ መንግሥት ሙሉ ለሙሉ ያከብራል።

ከማህበረሰቡ በኩል የሚመጡት እነዚህ ጥያቄዎች በተለይ የሕዝቡን ፍላጎት ባከበረ መልኩ በሰላም ጥረት ውስጥ የሚሳተፉ የሀገር ሽማግሌዎችና አባ ገዳዎችን እውቅና በመስጠትም ጭምር መንግሥት አስፈላጊውን ድጋፍ እያረገ፤ አሁንም የሰላም አማራጮችን ሙሉ ለሙሉ ክፍት አድርጎ እየሰራ ይገኛል።

እንደሚታወቀው መንግሥት ከመነሻው ጀምሮ ማንኛውም ነፍጥ አንግቦ አላማዬን በጦርነት፣ በጥቃት፣ በሽብር አስፈፅማለው የሚል አካል ሙሉ ለሙሉ የያዘውን ነፍጥ በማውረድ ሰላምና ደህንነትን በሚያረጋግጥ መልኩ ወደ ሰላም እንዲመጣ ለማድረግ ከዚህ በፊት በርካታ ጥሪዎችን ሲያደርግ ቆይቷል። ይሄም ተጨባጭ ውጤት የተገኘባቸው የተለያዩ ክልሎች የሚንቀሳቀሱና ከዚህ በፊት በሽብር ስራ ላይ የነበሩ የተለያዩ ቡድኖች አሁን የሰላም አማራጩን ተከትለው ወደ መደበኛ ማህበራዊ ኑሯቸው እየተመለሱ መሆኑ ይታወቃል። ይሄ የሰላም ጥሪ አሁንም በመንግሥት በኩል የሚቀጥል ነው የሚሆነው። ለሰላም ቅድሚያ ሰጥቶ ይሄንን አማራጭ የሚከተል ማንኛውም አካል ካለ የመንግሥት በር ሁሌም ክፍት ነው።

ከዚሁ ጋር በተያያዘ መንግሥት በመላ ሀገሪቱ የሚያከናውናቸው የልማትና የመልካም አስተዳደር ጥቄዎች አሉ፤ በሕዝቡ በኩል የሚነሱ። እነዚህን ለመመለስ እንዲሁም በዋነኛነት የዜጎችን ሰላምና ደህንነትን ለማረጋገጥ እንዲቻል የቀበሌ መዋቅሮችን ማጠናከር፤ በተለይ ከሕዝቡ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያላቸው የዕለት ተለት ትስስር ያላቸው እነዚህ መዋቅሮች በመሆናቸው በሁሉም የሀገሪቱ አካባቢዎች የሚገኙ የቀበሌ መዋቅሮችን በማጠናከር አቅማቸውን መገንባት እጅግ ወሳኝ የሆነ ተግባር መሆኑን መንግሥት በፅኑ ያምናል። በዚህ መሰረት ከዚህ በፊት የፀጥታ ችግር የነበረባቸው አካባቢዎች ላይ የነበሩ፤ እንዲሁም በተለያየ መልኩ የመከላከያ ሠራዊታችን እንዲሁም ደግሞ በተለያዩ አካላት የፀጥታ መዋቅራችን የተከናወኑ ኦፕሬሽኖች ተከትሎ ነፃ የወጡ አካባቢዎች ላይ ቀበሌዎችን ጨምሮ በዚህ ውስጥ የሚገኙ መዋቅሮችን የማጠናከርና የማስፈፀም አቅማቸውን የማደራጀት ስራ እንደዚሁም በተለያየ መልክ ያሉባቸውን ክፍተቶችንም በመሙላት አቅማቸውን የመገንባት ስራ በመላ ሀገሪቱ እየተተገበረ ነው የሚገኘው።

ለአብነት፣ በኦሮሚያ ክልል ውስጥ የሚገኙ ስድስት ሺ 398 ቀበሌዎች የተውጣጡ ከ635 ሺ በላይ የሚሆኑ የቀበሌ፣ ከቀበሌ መዋቅር በታችም ቀጥታ ከህብረተሰቡ ጋር በተለያየ መልኩ ግንኙነት ያላቸው አመራሮች የተሳተፉባቸው የተለያዩ ምክክሮች እንደዚህም ደግሞ ሥልጠናዎች እየተደረጉ ነው የሚገኙት በአሁኑ ሰዓት። ሥልጠናው እንግዲህ በታችኛው መዋቅር አመራሮች መካከል የሀገራዊ ክልላዊና አካባቢያዊ ጉዳዮችን በጥልቀት የሚመለከቱበት ነው። ሀገራችን ያለችበትን ነባራዊ ሁኔታ በተጨባጭ እንዲገነዘቡ ለማድረግ ትልቅ አስተዋፅኦ ያላቸው መድረኮች ናቸው። ከዛ ባሻገር ደግሞ እነዚህ አካላት በተመደቡበት ቦታ ውጤታማ በሆነ መልኩ የተሰጣቸውን ኃላፊነት መወጣት እንዲችሉ አቅም የሚሰጣቸው እንደሆነ ታምኖበታል። በእለት ተዕለት እንቅስቃሴያቸውም ከህብረተሰቡ የሚነሱ የተለያዩ ጥቄዎች አሉ። እነዛንም ወደ መድረክ በማምጣትም ጭምር ለውይይት እድልንም የሚፈጥር ነው።

ይሄ በመላ ሀገሪቱ ሲካሄድ የነበረ ሥልጠና በተለይም ቀደም ሲል ባነሳሁላችሁ ቁጥር በኩል ለአብነት ባነሳነው በኦሮሚያ ሲካሄድ የነበረው ሥልጠና ዛሬ የሚጠናቀቅ ይሆናል። ሠልጣኞች በተለያየ ርዕሶች የያዙ ሥልጠናዎች ሲከታተሉ ነበር። ከፌዴራል ጀምሮ የክልል አመራሮች እንደዚሁም ደግሞ በየደረጃው ያሉ አመራሮች የተሳተፉባቸው ናቸው እነዚህ ምክክሮች፤ በተለያዩ አካባቢዎች የሚገኙ የልማት ስራዎችን በመጎብኘት ጭምር ምን ያህል ኃላፊነት እንደተጣለባቸው ህብረተሰቡ ከነዚህ አመራሮች ምን እንደሚጠብቅም ጭምር በግልፅ የተመላከተበት ስራ ነው ሲሰራ የነበረው። እነህም ጉብኝቶች ተጠናቀው ዛሬ ወደ መደበኛ ስራቸው የሚመለሱ ይሆናል።

### ኮንትሮባንድ እና ተጓዳኝ ወንጀሎች

ሌላው ጉዳይ፣ እንደ ሀገር ከተደቀኑብን ትልቅ ፈተናዎች መካከል አንደኛው የሕገወጥ ንግድና የኮንትሮባንድ፤ እንደዚሁም በተለያየ መልኩ የሚፈጸሙ የንግድ አሻጥሮች ናቸው። ይሄ ሀገራችን ያላትን ከፍተኛ ሀብት እንዲባክን አድርጓል። ከዛ ባሻገር ኢትዮጵያ ያላትን እምቅ አቅም እንዳለ ሆኖ፣ ማግኘት የሚገባትንም ጥቅም እንዳታገኝ ትልቅ እንቅፋት ሆኖ መቆየታቸው ይታወቃል። ይህ እንግዲህ ዘርፈ ብዙ ችግር ነው፤ ከሀገር ውስጥም አልፎ ደግሞ በዓለም አቀፍ ደረጃ ጭምር የተዘረጋ ሰንሰለት ያለበት በመሆኑ የሚወሰዱት እርምጃዎች በፌዴራል፣ በክልል እንዲሁም በሀገር አቀፍ ደረጃም የሚከናወኑ የተለያዩ ተልዕኮዎች ናቸው።

ከእነዚህ ጉዳዮች መካከል ከሰሞኑ በሕገወጥ መንገድ ወደ ኢትዮጵያ ገብተው የተለያዩ የወርቅ እና ሌሎችም ማዕድናት ፍለጋ ላይ የተሰማሩ የነበሩ የውጭ ሀገር ዜጎችና ተባባሪዎቻቸው በተለያዩ ክልሎች በቁጥጥር ስር እንዲውሉ እየተደረገ ነው። እነዚህ አካላት ከውጭ ሀገር ወደ ኢትዮጵያ ሲገቡ የጸና የጉዞ ሰነድ የላቸውም፤ የመግቢያ ቪዛ፣ እንደዚሁም ደግሞ የመኖሪያ ፈቃድ፣ የመስሪያ ፈቃድም ሳይኖራቸው ነው በተለያዩ ቦታዎች ላይ እየተንቀሳቀሱ በሕገወጥ መልኩ የመዓድን ማውጣትና ማምረት ስራ ላይ ተሰማርተው የነበሩት። ከእነዚህ መካከል በሕገወጥ መንገድ ወደ ኢትዮጵያ ገብተው በጋምቤላ ክልል በሕገወጥ የወርቅ እና የተለያዩ ማዕድናት ፍለጋ ላይ የተሰማሩ 45 የውጭ ሀገር ዜጎች እና 3 ኢትዮጵያውያን ከእነ ኤግዚቢታቸው በቁጥጥር ስር እንዲውሉ ተደርገዋል። ምርመራም እየተጣራባቸውም ነው።

ከዚያ ባሻገር የጸጥታና የደህንነት የጋራ ግብረኃይሉ በወሰዳቸው የተለያዩ ርምጃዎች በተመሳሳይ ሁኔታ በሕገወጥ መንገድ ወደ ኢትዮጵያ ገብተው በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ውስጥ በሕገወጥ የወርቅና የተለያዩ ማዕድናት የፍለጋ እና ማምረት ስራ ላይ ተሰማርተው የነበሩ 47 የውጭ ሀገር ዜጎች፤ እንዲሁም 9 ኃላፊነታቸው የተወሰነ የግል ማህበራት፣ ደግሞ 7 ኢትዮጵያውያን የዚህ ስራ ተባባሪ ሆነው በመገኘታቸው ከእነ ኤግዚቢቱ ጭምር በቁጥጥር ስር እንዲውሉ ተደርጓል። እነዚህ አካላት ላይ ተገቢ የሆነ ምርመራ እየተጣራባቸው ነው የሚገኘው።

አሁን ሀገራችን ካላት የማዕድን ዘርፍ ተጠቃሚ እንዳትሆን በጣም አብዛኛው ሀብቷ በሕገወጥ መንገድ ወደውጭ ሀገራት እንዲወጣ እየተደረገ ነው። ተገቢ የሆነ ጥቅም ዜጎች ከሀገራቸው እንዳያገኙ ጭምር እየተደረገ በመሆኑ፤ ይህንን ለመቆጣጠር በሀገር አቀፍ ደረጃ እየተወሰዱ ካሉ እርምጃዎች መካከል አንደኛው ይኼ ተግባር ነው። በኮንትሮባንድ ሀገር የሚያወጡና የንግድ ሰንሰለቱን ከሀገር አቀፍ እስከ ዓለም አቀፍ ደረጃ የተዘረጋ መሆኑንም እዚሁ ላይ መመልከት ያስፈልጋል።

ለዚህ ሕገወጥ ሥራ ምቹ ሁኔታን የፈጠረው ደግሞ ምንድነው ብሎ መጠየቅም ያስፈልጋል። በተለይ እነዚህ አካባቢዎች ላይ። ትልቁ ለዚህ ሥራ ምቹ የነበረው እነዚህ ሕገወጥ አካላት ወደ ሀገር ውስጥ ገብተው እነዚህ ቦታዎቹ ላይ የማዕድን መፈለግና ማውጣት ሥራ ላይ እንዲሰማሩ የሆነው የነበረው የሰላም መደፍረስ ነው ምቹ ሁኔታን መደፍረስ እንደፈጠረላቸው ማንሳት ያስፈልጋል።

አሁን በእነዚህ ክልሎች ላይ በተለይ ነፍጥ አንግበው የነበሩ፣ በተለያየ የሽብር ሥራ ላይ ተሰማርተው የነበሩ የተለያዩ አካላት ወደ ሰላም መምጣታቸውን ተከትሎ ከመንግሥት ጋር እንዲሁም ከክልሉ ጋር በተለያየ መልኩ ወደ ሰላም ስምምነቶች ተደርሰው ወደ መደበኛ ኑሯቸው እንዲመለሱ መደረግ በመቻሉ፤ የሰላም እጦትን ሽፋን በማድረግ በጣም በርካታ ሕገወጥ ሥራ ይሰራባቸው የነበሩ አካባቢዎች አሁን ግልጽ እንዲወጡ አድርጓል። መንግሥት እነዚህን ወንጀሎች ተከታትሎ እርምጃ እንዲወስድባቸው ለማድረግ በጣም ምቹ አጋጣሚን የፈጠረው ሰላም በመኖሩ መሆኑን ሁሉም ሊገነዘብ ይገባል።

ሕገወጥ ተግባር በተለይ እነዚህ ቀደም ሲል ያነሳናቸው በኮንትሮባንድ እንዲሁም በሕገወጥ መንገድ ወደ ሀገር በመግባት ሲከናወኑ የነበሩ የማዕድን ማውጣትና መፈለግ ሥራዎች በጣም በርካቶችን ያሳተፈ ነበር የነበረው። ከሀገር ውስጥ ከኢትዮጵያን ባሻገር በዓለም አቀፍ ደረጃም ጭምር ሰንሰለቱ የተዘረጋ እንደሆነም ይታወቃል። ይህንን ደግሞ በቁጥጥር ስር ለማዋል ያለ ማህበረሰቡ ተሳትፎ ምንም ውጤት ማምጣት እንደማይቻል በግልጽ ማወቅ ያስፈልጋል።

በወንጀል ሥራው ላይ ተሳትፈዋል የተባሉትን ግለሰቦች ከእነኤግዚቢታቸው በቁጥጥር ሥር ማዋል የተቻለው በአካባቢው በሚገኙ የማህበረሰብ ክፍሎች ጥቆማ በመስጠታቸው፤ ምርመራዎች በሚደረጉበት ጊዜ፣ ጥናቶች በሚደረጉበት ጊዜ ሁሉ ማህበረሰቡ ከፍተኛ ትብብር ሲያደርግ እንደነበረ በተለያዩ አካላት በኩል ሲነሳ የነበረ ነው። ይህም ኦፕሬሽን ውጤታማ እንዲሆን ከፍተኛ ትብብር ላደረጉ የማህበረሰብ ክፍሎች፤ በየክልሉ ለሚገኙ ዜጎች መንግሥት ምስጋናውን ያቀርባል።

እነዚህ ሥራዎች ከፍተኛ የሆነ የኮንትሮባንድ ሕገወጥ ንግድ ሥራዎች አሁን ቀደም ሲል በጠቀስኳቸው ክልሎች ላይ ብቻ አይደለም፤ ሁሉም ክልሎች ላይ እየተፈጸመ ያለ ወንጀል ነው። ስለዚህ ይህንን ወንጀል ደግሞ ማስቆም የሚቻለው በተለይ በሀገራችን ኢኮኖሚ ላይ እየተፈጸሙ የሚገኙ እነዚህ ትልልቅ ወንጀሎችን ለማስቆምና ዜጎች የሚገባቸውን ጥቅም ከሀገራቸው ማግኘት እንዲችሉ ለማድረግና ለመከላከልም ጭምር፤ እነዚህን ወንጀሎች በሚፈጸሙበት ጊዜ ሕብረተሰቡ ከጸጥታ አካላት ጋር ያለውን ቅንጅት በማጠናከር ከዚህ በፊት ሲያደርግ የነበረውን ተግባር አጠናክሮ መቀጠል እንዳለበት በዚሁ አጋጣሚ መንግሥት ጥሪውን ያቀርባል።

### ግብርና እና የልማት ሥራዎች

በመጨረሻ የምንመለከተው የልማት ሥራዎች በተለይ የግብርናውን ዘርፍ ነው። ወቅታዊ የበልግ የበልግ እርሻ ስራ መረጃዎችን ስንመለከት፤ በ2015 የምርት ዘመን በበልግ ወቅት 2.2ሚሊዮን ሄክታር መሬትን ነው ለማልማት እቅድ የተያዘው፤ ከዚህም ውስጥ ወደ 24 ሚሊዮን ኩንታል ምርትም ይጠበቃል። እስከ አሁን ድረስ ባለው ወቅታዊ መረጃ ከግማሽ በላይ የሚሆን መሬት መታረሱን ነው የተለያዩ መረጃዎች የሚያሳዩት በሁሉም ክልሎች በተለይ በበቆሎ፣ ማሽላ፣ ስንዴና ጤፍ በዋንኛነት እንግዲህ በበልግ አብቃይ አካባቢዎች የሚመረቱ ምርቶች ናቸው። 92 በመቶ የሚሆነው እንግዲህ አነስተኛ ይዞታ በላቸው አርሶአደሮች ነው እነዚህ የእርሻ ስራዎች የሚፈጸሙት። 5 በመቶ ደግሞ በጠቃላይ ለሀገራዊ ምርትም ድጋፍ የሚያደርግ የእርሻ ዘመን/ወቅት ነው።


አረሶአደሩ ከፍተኛ ጥያቄ ከሚያቀርብባቸው እና ለልማት ስራውም ትልቅ አስተዋጽኦ ከሚያበረክቱት መካከል የአፈር ማዳበርያ አንደኛው ነው። ይሄም ደግሞ አቅርቦቱን ስንመለከት ለ2015/16 የምርት ዘመን ወደ 12 ነጥብ8 ሚሊዮን ኩንታል የአፈር ማዳበርያ ግዢ መፈጸሙን መረጃዎች ያሳያሉ። ከባለፈው ዓመት ደግሞ የከረመ 2 ነጥብ 2 ሚሊዮን ኩንታል አለ። ይህ የከረመው የአፈር ማዳበርያ ጋር ተደምሮ እንግዲህ በጠቅላላው ለ2015/16 የምርት ዘመን እስከ 15 ሚሊዮን ኩንታል የሚሆን የአፈር ማዳበርያ ለአሶአደሩ ለማሰራጨት ያስችላል። እንግዲህ ለበልግ ወደ 36 ሺህ 199 ኩንታል የሚሆን የአፈር ማዳበርያ ለስርጭት ዝግጁ ተደርጓል። በአጠቃላይ እንግዲህ እስከ አሁን የተሰራጨ የሚገኘውን ቁጥር ስንመለከት ወደ 1 ነጥብ 8 ሚሊዮን ኩንታል የአፈር ማዳበርያ ነው።

አሁን ላይ ከፍተኛ የሆነ ዝናብ አለ። በተለይ የበልግን ዝናብ ለልማቱ በአግባቡ መጠቀም እንዲቻል ከዛም በሻገር በመስኖ ለምቶ የደረሱ ሰብሎችን በተገቢው መንገድ ያለብክነት መሰብሰብ እንዲቻል ሁሉም ማህበረሰብ በተለይ ደግሞ በዚህ ስራ ላይ የተሰማራው አካላት እና ድጋፍ የሚያደርጉ አካላትም ጭምር ትልቅ ትኩረት ሰጥቶ ሊሰሩበት ይገባል። ምክንያቱም አሁን ያለው ዝናብ በመስኖ ስንዴ ሰብል ላይ ተጽኖ ሊያሳርፍ ስለሚችል ሰብል በደረሰባቸው አካባቢዎች ላይ በዝናቡ ምክንያት ብክነት እንዳይፈጠር በልዩ ትኩረት ህብረተሰቡ አስፈላጊውን ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርበታል።

# ተናጋሪው ዶሴ

## ሩቅ አስባ ቅርብ ያደረችው ወጣት

**አስመረት ብስራት**



ስደትን በአዎንታዊ ጎኑ ስንመለከት ከድህነት አረንቋ ለማውጣት የሚወሰድ እርምጃ ቢሆንም፣ በአሉታዊ ጎኖች ያመዝናሉ። ወጣቶች ተሰደው በሚኖሩበት አገር ከሚደርስባቸው አሉታዊ ገጽታዎች መካከል ጥቂቶቹ የሚከተሉት ናቸው።

በግለሰብ ደረጃ፣ ወጣት ስደተኞች ከሚያጋጥማቸው ተግዳሮቶች መካከል ለስነ-ልቦናዊና፣ ለአካላዊ፣ ስሜታዊና ለአእምሮአዊ ችግሮች ይዳረጋሉ፣ በኢኮኖሚያዊ ዘርፍ እንዲሁም፤ የሞራል ውድቀት፣ የዕዳ ቀውስ፣ የሥራ ጫና በተለይም በቋንቋ ችግር ምክንያት የበለጠ ለችግር ይዳረጋሉ።

ስደት በቤተሰብ ውስጥ መከፋፈልን ያመጣል። ምክንያቱም ወጣቶች ትዳር ከመሰረቱ በኋላ ለስደት በሚዳረጉበት ወቅት ቤተሰብ ላይ መከፋፈል ይፈጥራል፣ በተለይም በትዳር ውስጥ ውዝግብ ያስከትላል፣ እስከ መለያየት ሊያደርስ ይችላል፣ አልፎ ተርፎም ሕጻናትን ለአደጋ ያጋልጣል፣ ይህ በብዙ ቤተሰብ ውስጥ ትልቅ ፈተና ሆኖ የሚታይ ሀቂ ነው፣ ምክንያቱም የቤተሰብ ኑሮ ለማሻሻል ሲባል የተወሰደ እርምጃ ቢሆንም በቤተሰብ መካከል ክፍተት ይፈጥራል።

ሰላማዊ ማህበራዊ ግንኙነቶችን ለማዳበር እና ለመጠበቅ ሁሉም አባላት በውይይት የሚሳተፉበት ተለዋዋጭ መዋቅራዊ ሂደትን ይጠይቃል። ማህበራዊ ውህደት ቁሳዊ የሆኑ ነገሮች በሚፈጥሩት ልዩነት፣ በራስ ወዳድነት፣ አግባብ ባልሆነ የደሞዝ ክፍያ ምክንያት ተገድቦ በኅብረተሰቡ አኗኗሪ ዘይቤ ላይ ተጽዕኖ ያሳድራል። ይህ ቢሆንም እንኳን በድህነት ተቆራምዶ ከመተያየት ሞትም ቢሆን መድፈር ይሻላል ያሉቱ በብዙ ሺዎች የሚቆጠሩ ወጣቶች ወደ መካከለኛው ምስራቅ ይሰደዳሉ። ከእነዚህ መካከልም መቅደስ ደረጄ የተባለችው ወጣት አንዷ ናት። መቅደስ እንደ አብዛኞቹ ኢትዮጵያውያን ወጣቶች ስደትን ምርጫዋ አድርጋ ለመሄድ ከተነሳች ሰነባብታለች።

የመቅደስ የጉዞ እቅድ

ሳቂታ ናት፤ ፈገግታ ከፊቷ የማይጠፋ አይነት ወጣት። ለቤተሰቦቿ የመጀመሪያ ልጅ ስለነበረች እንደ ቤት መብራት የቤተሰቡን ህይወት የምታደምቅ አይነት ልጅ። ይች ወጣት ምንም ነገር አድርጋ ቤተሰቧን ማስደሰት፤ የቤተሰቧን ችግር መቅረፍን ህልሟ ለማሳካት በተቻለት አቅም በሙሉ መስራት ያለባትን ስራ በሙሉ ትሰራለች። ስራ ባትሰራም ገንዘቡ በምትፈልገው ልክ የቤተሰቧን ኑሮ መሻሻል ባለመቻሏ የተነሳ አረብ አገር ሄዳ የተሻለ ገቢ ለማግኘት ታቅዳለች።

በዚህም ምክንያት እቁብ መጣል ተጨማሪ ስራ መስራት ገንዘብ ከዚህም ከዚያም ማፈላለግ ትጀምራለች። በዚህ ወቅት ደረጄ የተባለ ግለሰብ ታገኛለች፤ የምትፈልገውን ገንዘብ እንደሚሞላላትም ይነግራታል፡ ፡ ይህንኑ ታሳቢ አድርጋም ደላላ ታፈላልጋለች፡፡ በዚህ መሀል ሮባ በሪሶ የሚባል በህጋዊ መንገድ ወደ ዱባይ ወደ ውጭ አገር ይልካል ከተባለ ሰው ጋር ትገናኛለች።

ሰውየውም በህጋዊ መንገድ ወደ ዱባይ እንደሚልካት ገልጾላት በመጋቢት ወር 2014 ዓ.ም አዳማ ከተማ ፓስፖርት ፎቶግራፍ እና ለጤና ምርመራ ብሎ ብር 6ሺ ብር ተቀብሏት ቪዛው ሲመጣ 20 ሺ ብር ትከፍያለሽ በማለት ይለያታል። ጥቂት ጊዜ ቆይቶ ይደውልላትና ቪዛሽ መጥቷል ገንዘቡን ይዘሽ ነይ ይላታል። ወጣቷም ከምትኖርበት ጅማ ዞን ሊሙ ኮሳ ወረዳ ወዳጅ ዘመዶቿን ተሰናብታ ወደ አዲስ አበባ ከተማ ትመጣለች።

አዲስ አበባ ጀሞ 01 አካባቢ ከደላላው ጋር ተገናኝተው ከሌላ እንደ እሷ አረብ አገር ለመሄድ ቪዛ መጣልሽ ከተባለች ሶፊያ ገበየሁ ከተሰኘች ልጅ ጋር ወደ አዳማ ከተማ ወደ ራሱ መኖሪያ ቤት ይልካቸዋል። ከዛ በኋላ ለሥራ የመላክ ፍቃድ ሳይኖራት ወደ ዱባይ አገር እልካችኋለሁ ከምትል በድሪያ ኡመሬ አሚኖ ጋር ይገናኛሉ። ሴትየዋ በህጋዊ መንገድ ወደ ዱባይ አገር እንደምትልካት በማረጋገጥ ስታገኛቸው ምንም ሳትጠራጠር በጥሬ ገንዘብ 19 ሺ ብር ለፕሮሰስ ማስጨረሻ የሚሆን ብላ መቅደስ ለበድሪያ ትሰጣታለች።

በድርያም ብርን ከተቀበለች በኋላ ከሌሎች እንደ መቅደስ አረብ አገር ለመሄድ ከተዘጋጁ ሌሎች ወጣቶች ጋር አንድ ላይ በማድረግ ከአዳማ ከተማ ወደ አዲስ አበባ ከተማ ይዛቸው መጥታ የካ ክፍለ ከተማ ላምበረት መናኸሪያ አካባቢ ለጊዜው ካልተያዘው ኡስማን አሊ ከሚባል ግለሰብ ጋር በመሆን አልጋ እንዲይዙ ታደርጋታለች፡፡

ሆኖም በዚህ መሃል በቀን 03/09/2014 ዓ.ም በድርያ በፖሊስ በቁጥጥር ስር ትውላለች፡፡ በፈፀመችው በህገ-ወጥ መንገድ ሰውን ለስራ ወደ ውጭ አገር መላክ ሙከራ ወንጀል ተከሳለች፡፡ እነ መቅደስም በባበዶ ጉጉት የለፉበትንና ከወዳጅ ዘመድ ፈላልገው ያገኙትን ገንዘብ አስረክበው ችግር ላይ ወደቁ።

### በድሪያ ዑመሬ አማኖ

በድሪያ ዑመሬ አማኖ ለዓመታት አረብ አገር ኖራ የመጣች ሴት ናት። በአረብ አገር ከሰው ቤት ስራ እስከ ሰራተኞችን እየተቀበሉ ሰው ቤት እስከ ማሰማራት ድረስ ሰርታለች። ወደ አገሯ ከተመለሰች በኋላም ለሥራ የመላክ ፍቃድ ሳይኖራት ሰዎችን በህገ ወጥ መንገድ መላክን ዋነኛ ስራዋ አድርጋ ይዛዋለች።

በዚህም በርካቶችን በመላከ የብዙ ወጣቶች ህይወት የባህር ሲሳይ እንዲሆን አድርጋለች። በለስ ቀንቷቸውም ዱባይ የደረሱቱ ያለፈቃድ በመሄዳቸው የተነሳ እንግልቱ በዝቶባቸው ሌት ከቀን ያነባሉ። በድሪያ ግን በሌሎች ሰቆቃ ገንዘብ ማግኘትን ስራዬ ብላ ተያይዛዋለች። በዚህም ተግባሯ ለሥራ የመላክ ፍቃድ ሳይኖራት ወደ ዱባይ አገር እልካችኋለሁ በማለት ከ9 ግለሰቦች ገንዘብ በመቀበሏ ልትያዝ ችላለች።

ከፍትህ ሚንስቴር ድረገፅ ያገኘነው መረጃ እንደሚያመለክተው በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ፍትህ ሚኒስቴር የጠቅላይ ዐቃቤ ህግ ዘርፍ የተደራጁና ድንበር ተሻጋሪ ወንጀል ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ጀነራል ዐቃቤ ሕግ ሰውን ለሥራ ለመላክ ፍቃድ ሳይኖራት በህጋዊ መንገድ ወደ ዱባይ አገር እንደምትልካቸው በማረጋገጥ ካልተያዙ ግብረ-አበሮቿ ጋር በመሆን ከግል ከተበዳዮች ያለአግባብ ገንዘብ ተቀብለሻል በማለት ክስ ተመስርቶባታል።

የዐቃቤ ህግ የክስ መዝገብ

የዐቃቤ ህግ የክስ መዝገብ ላይ እንደተመለከተው በድሪያ ዑመሬ አማኖ የተባለችው ተከሳሽ ለጊዜው ካልተያዙ ግብረ-አበሮቿ ሮባ በሪሶ እና ኡስማን አሊ ጋር በዋና ወንጀል አድራጊነት ተካፋይ በመሆን በመላ ሃሳቧ፣ በወንጀሉ ድርጊት እና በሚሰጠው ውጤት ሙሉ ተካፋይ የሆነች ናት፡፡

ወደ ውጭ አገር ሰውን ለሥራ ለመላክ ፍቃድ ሳይኖራት የግል ተበዳይ መቅደስ ደረጄ የተባለችው ለስራ ወደ ውጭ አገር መሄድ ስለምትፈልግ ሮባ በሪሶ የሚባል የተከሳሽ ግብረ-አበር በህጋዊ መንገድ ወደ ዱባይ እንደሚልካት ገልጾላት በመጋቢት ወር 2014 ዓ.ም አዳማ ከተማ ፓስፖርት ፎቶግራፍ እና ለጤና ምርመራ ብሎ ብር 6ሺ ብር ተቀብሏታል፡፡

ቪዛው ሲመጣ 20 ሺ ብር ትከፍያለሽ ካላት በኋላ፣ ደውሎላት ቪዛሽ መጥቷል ገንዘቡን ይዘሽ ነይ ባላት መሰረት ከምትኖርበት ጅማ ዞን ሊሙ ኮሳ ወረዳ ወደ አዲስ አበባ ከተማ የመጣችና አዲስ አበባ ጀሞ 01 አካባቢ ተገናኝተው ከግል ተበዳይ ሶፊያ ገበየሁ ጋር ወደ አዳማ ከተማ ወደ ራሱ መኖሪያ ቤት የላካቸው ሲሆን፣ በኋላ ተከሳሿ በህጋዊ መንገድ ወደ ዱባይ አገር እንደምትልካት በማረጋገጥ ከተበዳይ በጥሬ ገንዘብ 19 ሺ ብር ለፕሮሰስ ማስጨረሻ የሚሆን ብላ በመቀበል ከሌሎች ተበዳዮች ጋር አንድ ላይ በማድረግ ከአዳማ ከተማ ወደ አዲስ አበባ ከተማ ይዛቸው መጥታ የካ ክፍለ ከተማ ላምበረት መናኸሪያ አካባቢ ለጊዜው ካልተያዘው ኡስማን አሊ ከሚባል ግለሰብ ጋር በመሆን አልጋ እንዲይዙ ካደረገች በኋላ ሳትልካት በቀን 03/09/2014 ዓ.ም በቁጥጥር ስር የዋለች በመሆኑ በፈፀመችው በህገ-ወጥ መንገድ ሰውን ለስራ ወደ ውጭ አገር መላክ ሙከራ ወንጀል ተከሳለች፡፡

እንዲሁም ዐቃቤ ህግ በተደራራቢነት ባቀረባቸው ሌሎች 8 ክሶች ተከሳሿ ለጊዜው ካልተያዙ ከላይ ከተጠቀሱት ግብራበሮቿ ጋር በመሆን ሰሚራ ከሚል፣ ሁሴን መሀመድ፣ አብዱ ግርማ፣ ሱልጣን ኮቴ እና አሸሩ ከድር የተባሉ ተበዳዮችን ለስራ ወደ ውጭ አገር መሄድ ስለሚፈልጉ ሮባ በሪሶ የሚባል የተከሳሽ ግብረ-አበር በህጋዊ መንገድ ወደ ዱባይ እንደሚልካቸው በመግለፅ በመጋቢትና ሚያዝያ ወር 2014 ዓ.ም ሮባ በሪሶ የተባለውም የሚቀበሏቸውን ግብረ-አበሮቹን ያልተያዘው ኡስማን አሊ እና ተከሳሿን ልኮላቸው እነሱም ከተለያየ ቦታ ተነስተው የመጡትን ተበዳዮች ተቀብለዋቸው የካ ክ/ከተማ ላምበረት መናኸሪያ አካባቢ ወደሚገኝ ስሙ ባልታወቀ አልጋ ቤት ይዘዋቸው በመሄድ ተከሳሿ እና ያልተያዙ ግብረ-አበሮችም በህጋዊ መንገድ ወደ ዱባይ እንደሚልኳቸው በማረጋገጥ ለፕሮሰስ ማስጨረሻ የሚሆን ከሁሴን መሀመድ እና ሱልጣን ኮቴ ከያንዳንዳቸው 25 ሺ ብር ስትቀበል፣ አብዱ ግርማ ከተባለው የግል ተበዳይ 30 ሺ ብር፣ ከአሸሩ ከድር ከተባለችው 20 እንዲሁም ሰሚራ ከሚል ከተባለችው 21 ሺ ብር በጠየቋቸው መሰረት ለተከሳሿ የሰጧት ሲሆን ተከሳሿ ሳትልካቸው በቀን 03/09/2014 ዓ.ም በቁጥጥር ስር የዋለች በመሆኑ በፈፀመችው በህገ-ወጥ መንገድ ሰውን ለስራ ወደ ውጭ አገር በመላክ ሙከራ ወንጀል ዐቃቤ ህግ ክስ መስርቶባታል፡፡

ዐቃቤ ህግ በ1996 ዓ.ም የወጣውን የወንጀል ህግ አንቀፅ 27(1)፣ 32 (1) (ሀ)፣ (ለ) እና በሰው የመነገድ እና ሰውን በህገ ወጥ መንገድ ድንበር ማሻገር ወንጀልን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የወጣ አዋጅ 1178/2012 አንቀፅ 11(1) ን መሰረት በማድረግ ነው ክስ ያቀረበባት።

### ውሳኔ

በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የልደታ ምድብ 14ኛ ወንጀል ችሎት የቀረበችው ተከሳሽ የተከሰሰችበት ክስ በችሎት ተነቦላት የክስ መቃወሚያ የለኝም ጥፋተኛም አይደለሁም ያለች ሲሆን አቃቤ ህግም ተከሳሿ ክዳ የተከራከረች በመሆኑ በጉዳዩ ላይ የሚያስረዱ የህግ ምስክሮቻችን ስላሉ ይሰሙልኝ በማለት 9 የሰው ምስክሮችን አቅርቦ ያሰማ ሲሆን የአቃቤ ህግ ምስክሮችና ማስረጃዎችም በተከሳሿ ላይ በክሱ መሰረት ያስረዱ በመሆኑ በቀረበባት ክስ መሰረት እንድትከላከል የመከላከያ ማስረጃ እንድታቀርብ ቀጠሮ በተሰጣት መሰረት የተከሳሿ ተከላካይ ጠበቃ የመከላከያ ምስክሮችን ከክፍለ አገር ፈልገው ማቅረብ እንዳልቻሉ ገልጸው ተከሳሽ የመከላከያ ማስረጃ ማቅረብ ስላልቻለች ትከላከል በተባለበችበት ድንጋጌ ስር ጥፋተኛ ነሽ ብሏታል፡፡

ፍርድ ቤቱም ተከሳሽን ያርማል ሌሎችንም ያስተምራል በሚል በ18 ዓመት ጽኑ እስራትና በ106 ሺ ብር የገንዘብ መቀጮ እንድትቀጣ ሲል ወስኖባታል፡፡

መዝናኛ

# ማረፊያ/ ትዝብት

## “ይትባረክ እንደ አብርሃም...”ብለን ሳንጨርስ...?

**ቃልኪዳን አሳዬ**

ለአቅመ ሔዋን የደረሰች ኮረዳንና ለአቅም አዳም የደረሰን ጎረምሳ አንች ትብሽ በአንተ ይብስ በሚል ቃልኪዳን አስተሳስራ ገመናቸውን ሸፍና የምታኖራቸው፤ በደሴት ላይ ያለች መርከብ መሳይ ህይወት ናት። ተባብረው ጀልባዋን መቅዘፍ ከቻሉ ሞገዱን፤ ውሽንፍሩን፣ ማዕበሉን አሸንፈው ወልደው ከብደው አርጅተው ይኖሩባታል፡፡

ይችን በማዕበልና ሞገድ የተወጠረችውን፤ በእሳትና በውሀ የተከበበችን ህይወት ቅበላና ትንሳኤ ሲመጣ በአታሞው ድለቃ፣ በጥሩምባው ጩኸት፣ በዳስ በድንኳኑ ማጌጥ፣ በገበያ ትርምስምሱ፣ በጠጁ ሽታ፤ በበሬው በበጉ ጩኸት በሙሽራዎችና በሚዜዎች ዳንስ ልምምድና ልብስ ምርጫ የውል ቀኗ መድረሱ ይታወቃል፡፡

የውል ቀኗ ዕለት ይትባረክ እንደ አብረሃም ተብላ ተዘፍኖላት ተመርቆላት የታደሉት ጀልባዋን እየቀዘፉ በአብርሃምና በሳራ ቤት ሲኖሩ ያልታደሉት አቅጣጫ ጠፍቶባቸው ሲባዝኑ ቀሪዎች የማዘጋጃን ቤት ወረቀት ሲያጸዱ ይገኛሉ፡፡

ሶስት ጉልቻን የሚመሩበት ከትልቅ ውቅያኖስ ጥልቅ ማስተዋል አጥተው ማሬ ወደ ኮምዛዜ፤ ባባዬ ወደ ሰውዬ ቋንቋ ተደበላልቆባቸው፤ ንክሻና ንትርክ ጀልባቸውን አስምጦባቸው ‹‹አይንሽን ባየው ባየው አልሰለችህ አለኝ››፣ ብለው የጀመሩት ጀልባ ቀዘፋ ‹‹አይንሽን ላፈር፣ አይንህን ላፈር›› በሚል ስንክሳር ላይታደስ ይወድማል፡፡

የትዳር መፍረስ የልጆች የወደፊት እጣ ፈንታ ከማጨለም ባለፈ በአገር ላይ ትልቅ ኪሳራ የሚያደርስ ነው፡፡ ኢትዮጵያ ሀይማኖተኞች እና ባህላቸውን አጥባቂዎች የሚበዙባት አገር እንደመሆኗ መጠን ለትዳር ትልቅ ስፍራ ከሚሰጡ አገራት መካከል አንዷ ናት። ይሁን እንጂ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ፍቺ በተለይ በከተሞች አካባቢ እየጨመረ መምጣቱ ይነገራል። ይህ ማለት በገጠር አካባቢ ፍቺ የለም ማለት አይደለም።

የእንጀራ ዋጋ ስለተወደደብኝ ትዳር ልመሰርት ነው የሚሉም አልጠፉም፤ በዚህ ሁኔታ ትዳር የመሰረቱ ሰዎች የኑሮ ውድነቱ ሲስተካከል ተመልሰው ሊፋቱ ነው ብዬ አስብና ለራሴ እገረማለሁ፡፡ ታዲያ የሆነው ሆኖ፤ የአዲስ አበባ ከተማ ወሳኝ ኩነት ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ፤ በመዲናይቱ ብቻ ባለፉት 6 ወራት አንድ ሺህ 342 ፍቺዎች መመዝገባቸውን አሳውቋል፡፡ ይህ ማለት በቀን ሰባት ትዳሮች በፍቺ ይቋጫሉ ማለት ነው፡፡

ዘንድሮ በ6 ወራት ብቻ የተመዘገበው የፍቺ ቁጥር ካለፈው ዓመት ጋር ሲነጻጸር ተቀራራቢ ሲሆን፤ በ2014 በጀት ዓመት አንድ ሺህ 623 የፍቺ ምዝገባዎች መደረጋቸውን መረጃዎች ያመለክታሉ። እነዚህ መረጃዎች የሚያመላክቱት በመስሪያ ቤቱ በህጋዊ መንገድ የተመዘገቡትን ብቻ ነው። ያልተመዘገቡትን ቤት ይቁጠረው።

በተለያዩ ቦታዎች በህጋዊም ሆነ በባህላዊ መልኩ ፍቺ እና ጋብቻ ይከናወናል፤ ነገር ግን ወደ ወሳኝ ኩነት ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ መጥተው የሚመዘገቡት ቁጥራቸው አነስተኛ እንደሆነ ይነገራል። በአዲስ አበባ ከ2012 እስከ 2014 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ ብቻ 16 ሺህ 35 ፍቺዎች እንደተካሄዱ የወሳኝ ኩነት መረጃ ያሳያል።

ለፍቺ ዋነኛ መንስዔዎች ተብለው የሚጠቀሱት የኢኮኖሚ መዳከም፣ አለመተማመን፣ የምዕራባውያን አገራት የባህል ጫና፣ ቅናት እና የወሲብ አለመጣጣም ናቸው ይባላል፡፡ ትዳሮች በተለያዩ ምክንያት የሚፈርሱ ቢሆንም እንኳን፣ ኢኮኖሚያዊ ችግሮቹ ትልቅ ድርሻ አላቸው።

በንብረት ላይ መጋጨት፣ አለመግባባት፣ እርስ በእርስ መጠራጠር እንዲሁም የቤተሰብና የሌሎች ሰዎች ጣልቃ ገብነት፤ በልጆች ቁጥር፣ በአኗኗር ሥርዓት፣ በመኖርያ ስፍራ ምርጫ ለባልና ሚስት የፍቺ ምክንያት መሆናቸውን ሁላችንም የምናውቀው ጉዳይ ነው።

ነገር ግን ተጋቢዎቹ ከተግባቡ፣ ከተመካከሩና ከተከባበሩ ሦስተኛ ወገን ትዳርን ለማፍረስ ቦታ ይኖረዋል?፣ በአሁኑ ሰዓት ግን ፍቅራችንን በቀለበት እንሰረው፣ በሰርግ እናድምቀው የሚሉትን ያህል ፍቺያችንን አጽድቁልን ብለው የፍርድ ቤት ደጃፍ የሚጠኑ ቁጥራቸው ቀላል የሚባል አይደለም።

የትዳሮች በፍቺ መጠናቀቅ በርካታ የማህበራዊ ቀውሶች መንስኤ ነው፡፡ ፍቺ በየትኛውም የእድሜ ክልል ለሚገኙ ሕጻናት ላይ የሚያደርሰው የስነልቦና ጠባሳ ቀላል የሚባል አይደለም። የትዳር መፍረስ ልጆችን፣ ቤተሰብን፣ ማህበረሰብን እና አገርን እንደሚጎዳ በርካታ ጥናቶች ያስረዳሉ። በፍቺ ምክንያት ሕጻናት ለአካላዊ፣ ለአእምሯዊና ስነልቦናዊ ጉዳት ይጋለጣሉ።

የሁለቱንም ወላጆቻቸውን ክትትልና እንክብካቤ ማግኘት ስለማይችሉም በቀጣይ ህይወታቸው ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ያሳድራል። ከእናትና ከአባታቸው ጋር ያላቸው ግንኙነትና ፍቅር ይቋረጣል። ይህ ደግሞ አእምሯቸውን ከመጉዳቱ ባሻገር በቀሪው ዘመናቸው በድንጋጤ እና ፍርሃት እንዲኖሩ ያደርጋቸዋል።

ልጆች የወላጆቻቸውን ፍቅር በጋራ ይፈልጋሉ ፍቺ ትውልድን፣ ቤተሰብን፣ ማህበረሰብን ከመጉዳት አልፎ ለአገርም ትልቅ ጉዳት ነው። ወላጆች በጋራ ያፈሩትን ልጅ በመንከባከብ በስርዓት ማሳደግ እና ማስተማር፣ ለአገር እንዲሆኑ አድርገው መቅረጽ አለባቸው። ልጆችን በኃላፊነት ካላሳደግናቸው ጠንካራ ማኅበረሰብ ሊገነባ አይችልም። ጠንካራ ማኅበረሰብ የሌላት አገር ሁሌም ችግር ውስጥ መግባቷ የማይቀር ነው፡፡

እንደ እኔ እምነት ባለትዳሮች የተረጋጋ የኢኮኖሚ ሁኔታ እስኪያገኙ ድረስ ልጅ ባይወልዱ የተሻለ ነው፡፡ ልጅ በእድሉ ይደግ በሚለው አባባል አላምንም፡፡ የኛ አገር ሰው በድህነት እየኖረ የልጁን ስም ተስፋዬና ሚሊዮን እያለ ሰይሞ በተስፋ ይኖራል፡፡

አንተ ሳታገባ ለፍቺ ምን አስጨነቀህ ያላችሁኝ እንደሆነ ጉዞዬም ወደዛው ነውና ስጋታችሁ ስጋቴ ነው፡፡ ትዳርን ከፍቺ አረንቋ ለማውጣት ግን ወላጆች የሚከፍሉት መስዋዕትነት እንደሚኖር ግልጽ ነው። ይህ ሳይሆን ቀርቶ የፍቅር ሸማ የለበሰው ትዳር፣ የፍቺ ጸሐይ ከሞቀው ግን በመካከል ያሉ ልጆች እንዳይጎዱ ማህበረሰቡና መንግሥት ተገቢ የሆነ እርምጃ መውሰድ እንዳለባቸው አምናለሁ።

ሁላችንም ቢሆን ትዳር በፈለግንበት ጊዜ ጎራ የምንልበት መሸታ ቤት አለመሆኑን ልንረዳ ይገባል። በእቅድና በትኩረት የተገነባ ትዳር ከሁሉም የበለጠ ጠንካራ መሰረት ይኖረዋል። ጋብቻ ማኅበራዊ ተቋም እንደመሆኑ ተጋቢዎች በሰከነ አዕምሮ ሊጠብቁት ካልቻሉ ሌላ አካል ማንም አይጠብቀውም፡፡

ፍቺ በሰው እና በፈጣሪ ፊት ቃልኪዳን ተግባብተው መልሰው ሲለያዩ የአደባባይ እውነታ ነው። ትዳር በፈጣሪ ፍቃድና ዓላማ በአዳምና ሄዋን ተመስርቶ እስካሁን የመጣ ትልቅና የከበረ ተቋም መሆኑን ሁሉም ሰው በመረዳት በጥበብና በጥንቃቄ መምራት ይጠበቅበታል። መንግስትም ቢሆን ፍቺን እየመዘገበ ይፋ የሚያደርግ ተቋም ማቋቋም ብቻ ሳይሆን፤ ትዳርን ከፍቺ የሚጠብቅ ተቋም ሊመሰርት ይገባል፡፡

የእምነት ተቋማትን ጨምሮ ጥብቅ ትምህርትና ስልጠና መስጠት፣ መንግስትም ትዳር ለአገር መሠረት በመሆኑ ስልት ቀይሶ ማስተማርና መገንባት ይኖርበታል፡፡ እንግዲህ የእምነት ተቋማትና የሀይማኖት አባቶች ስራችሁ ብዙ ነው፡፡

“ይትባረክ እንደ አብረሀም...” ብለን ሳንጨርስ... አለ አይደል... “ዓይንህ ለአፈር/ዓይንሽ ለአፈር” ተባባሉ ሲባል መልካም አይደለም፡፡ እና እላችኋለሁ ያገባችሁ በትዳራችሁ ፈጣሪ ያጽናችሁ፤ ያላገባችሁ ካላችሁ ቸር ትዳር እንዲገጥማችሁ ምኞቴ ነው፡፡

# ዓለም አቀፍ



## እስራኤል በሊባኖስና ፍልስጤም ላይ ከፍተኛ የአየር ጥቃት ሰነዘረች

የእስራኤል መከላከያ በፍልስጤም ታጣቂ ቡድን ሐማስ ይዞታዎች ላይ ጥቃት ሰነዘረ። ጥቃቱ ከሊባኖስ ወደ እስራኤል የተተኮሱ ተከታታይ ሮኬቶችን ተከትሎ የመጣ የአጸፋ እርምጃ ነው። የእስራኤል መከላከያ እንዳለው በዚህ የአየር ጥቃት በደቡብ ሊባኖስ የሚገኝ የ‘አሸባሪ’ው ሐማስ የጦር ቀጠና ከፉኛ ተደቁሷል።

ከሰሞኑ የእስራኤል ፖሊስ የአል አቅሳ መስጂድ ላይ ወረራ ከፈጸመ በኋላ በአካባቢው ውጥረት ነግሶ ሰንብቷል። አል አቅሳ ለእስልምና እምነት ተከታዮች ሦስተኛው ቅዱስ ስፍራ ነው። ይህም በመሆኑ የእስራኤል ፖሊስ መስጂድ ቅጥር በመዝለቁ በአካባቢው አገራት ጭምር ቁጣን ቀስቅሶ ነበር።

ሮኬቶቹ ሲተኮሱ በሊባኖስ የነበሩት የሐማስ መሪ ኢስማኤል ሐኒያህ ጥቃቱን ተከትሎ “ፍልስጤማዊያን በእስራኤል ወራሪዎች ሲደፈሩ እጃችንን አጣጥፈን አንመለከትም” ብለዋል። የእስራኤል መከላከያ በበኩሉ ሐማስ በሊባኖስ የመሸገበትን ስፍራና የወታደራዊ መሠረተ ልማቱን ማውደሙን አስታውቋል። ሐማስ ከሊባኖስ የተተኮሱት ሮኬቶች ዙርያ መረጃ የለኝም ይላል።

እስራኤል በሰሜን በኩል ጎረቤት አገር ሊባኖስ በኩል የተሰነዘረውን የሮኬት ጥቃት በ17 ዓመታት ከፍተኛው ነው ብላለች። ከ37 ሮኬቶች አብዛኛዎቹን ማክሸፏንም ተናግራለች። 6 ሮኬቶች በሕንጻዎች ላይ ጥቃት አድርሰዋልም ብላለች። ይህን ተከትሎ የእስራኤል የጦር አውሮፕላኖች በጋዛ ሰርጥ ጥቃት ያደረሱ ሲሆን በ10 ደቂቃ ብቻ 20 ሚሳኤሎች የተለያዩ ቦታዎችን አጥቅተዋል።

የፍልስጤም ታጣቂቆችም ሮኬቶችን ወደ ደቡብ እስራኤል የተኮሱ ሲሆን በአካባቢው የማስጠንቀቂያ ደውሎች ተሰምተዋል። የእስራኤል ጄቶች የምድር ውስጥ የጦር መሣሪያ ማምረቻ ስፍራን ማውደማቸውን እየሩሳሌም ፖስት መከላከያውን ዋቢ በማድረግ ዘግቧል።

እስራኤል ከዚህ ቀደም በእስላሚክ ጂሃድ ላይ ተመሳሳይ ጥቃት ካደረሰች ከነሐሴ 2022 ወዲህ ይህ ጥቃት ትልቁ ነው ተብሏል። ይህ ጥቃት ጠቅላይ ሚኒስትር ናታንያሁ አስቸኳይ የደኅንነት ጉዳይ ስብሰባ ከጠሩ በኋላ የተሰነዘረ ነው። ናታያንያሁ በቴሌቪዥን ባደረጉት ንግግር ጠላቶቻችን ሁሉ እኛን በተዳፈሩ ጊዜ ከባድ ዋጋን ይከፍላሉ” ብለዋል።

የሊባኖስ ጠቅላይ ሚኒስትር ነጂብ ሚካቲ እስራኤል ሉዓላዊ ግዛት በመጣስ የሰነዘረችውን ጥቃት አውግዘዋል። የተባበሩት መንግሥታት የሰላም አስከባሪ ኃይል በሊባኖስ ‘ሁኔታዎች አስፈሪ ናቸው’ ያለ ሲሆን ሁለቱም ወገኖች ነገሩን ከማባባስ እንዲቆጠቡ መምከሩን ቢቢሲ ዘግቧል።



የጣሪያ ቆርቆሮ ሰረቁ የተባሉት የኡጋንዳ ሚኒስትር ፋሲካን እስር ቤት ሲያሳልፉ ነው

የኡጋንዳ የካቢኔ ሚኒስትር ሜሪ ኪቱቱ የጣሪያ ቆርቆሮ ሰርቀዋል በሚል ተከሰሱ። ሚኒስትሯ ድርጊቱን አልፈጸምኩም ብለዋል። የጣሪያ ቆርቆሮዎቹ ለሰሜን ምሥራቅ ኡጋንዳ ተፈናቃዮች እንዲደርሱ ነበር የታሰቡት። የሙስና አጣሪ ኮሚሽን እንዳለው ቆርቆሮዎቹ ለታሰበላቸው ወገኖች ሳይደርሱ ሚኒስትሮች ተከፋፍለዋቸዋል።

ከእነዚህ ሚኒስትሮች አንዷ ደግሞ የካቢኔ ሚኒስትር የሆኑት ሜሪ ኪቱቱ ናቸው ሲል ከሷል። ሜሪ ኪቱቱ የዚህ ካራሞጃ የተባለው ክልል አስተዳዳሪ ናቸው። ከሜሪ ኪቱቱ ሌላ 10 ሌሎች ከፍተኛ ባለሥልጣናት ቆርቆሮውን ተቀራምተውታል ተብሏል። መርማሪ ኮሚሽኑ እንዳለው የጣሪያና የአጥር ቆርቆሮውን ከተቀራመቱት መሀል ምክትል ፕሬዚዳንቱ፣ ጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ የፓርላማ አፈ ጉባኤው ይገኙበታል።

በጠቅላላ ተዘረፉ የተባሉት የጣሪያ ቆርቆሮዎች ብዛት 14ሺህ 500 ይደርሳል። ስማቸው ከዘራፊዎች ተርታ የተጠቀሰው ጠቅላይ ሚኒስትር ይቅርታ ጠይቀው ቆርቆሮ የመለሱ ሲሆን ሌሎችም የእርሳቸውን ፈለግ እንዲከተሉ መክረዋል። አንድ ሌላ ሚኒስትርም ደግሞ ተቀብለው የነበረው ቆርቆሮ ከአጥር ላይ ነቅለው መልሰዋል ሲሉ የአገሬው ሚዲያዎች ዘግበዋል።

ካራሞጃ ክልል ለተከታታይ ዓመታት በድርቅ የሚጎሳቆል ሲሆን ዝናብ ሲዘንብ ደግሞ በጎርፍ የሚጠቃ አካባቢ ነው። በዚህ የተነሳም አካባቢው በተረጂነት የሚታወቅ ነው። የዚህ አካባቢ አስተዳዳሪ ሚኒስትሯ ሜሪ ኪቱቱ ረቡዕ በቁጥጥር ሥር ውለዋል። ክሳቸው እንደሚለው እርሳቸው ቆርቆሮዎቹን ለተረጂዎች ከማድረስ ይልቅ ለዘመዶቻቸውና ለባለሥልጣናት አከፋፍለዋል። እርሳቸው ግን ክሱ ውሸት ነው ሲሉ ፍርድ ቤት ተከራክረዋል።

ከርሳቸው ጋር ወንድማቸው ማይክል ኪቱቱም የተከሰሰ ሲሆን 100 ቆርቆሮ ወስዷል ይላል ክሱ። እርሱም ልክ እንደ እህቱ ጥፋተኛ አይደለሁም ብሏል። የሚኒስትሯ ሜሪ ኪቱቱ ፍርድ ቤት መቅረብ በኡጋንዳ ሚዲያ በስፋት ሲጠበቅ የነበረ ነው ተብሏል። በርካታ ሚዲያዎችም ፍርድ ቤት ታድመዋል። ፍርድ ቤት በቀረቡበት ወቅትም ፊታቸውን እና ጭንቅላታቸውን በሻሽ ሸፍነው ነበር።

የሚኒስትሯ ጠበቃ የዋስ መብት እንዲከበርላቸው የጠየቁ ሲሆን ጥያቄያቸው ግን ተቀባይነት አላገኘም። አቃቢ ሕግ በዋስ እንዳይለቀቁ የተከራከረ ሲሆን በተለይ ኪቱቱ የእናታቸው ቤት ሲፈተሽ ቆርቆሮ የተገኘ ቢሆንም ቃል እንዳይሰጡ ከልክለዋቸዋል ብሏል። ስለዚህ በዋስ ቢለቀቁ አደጋው የከፋ እንደሆነ ለፍርድ ቤቱ አስረድቷል።

ኪቱቱ የአካባቢ ጥበቃ ሳይንቲስት ሲሆኑ ማውንት ኢልጎን የሚባለውን የተወለዱበትን አካባቢ በስፋት በማጥናት ይታወቃሉ። የፓርላማ አባል የሆኑት በአውሮፓውያኑ 2016 ሲሆን ከዚህ ቀደም የኢነርጂና ማዕድን ሚኒስትር ሆነው አገልግለዋል። በኡጋንዳ ትልልቅ ባለሥልጣናት በሙስና መዘፈቅ ዜና የተለመደ ቢሆንም ሚኒስትሮቹ ይቅርታ ሲጠይቁ አልያም ሥልጣን ሲለቁ ማየት ግን ብዙም አልተመለደም። ፕሬዚዳንት ሙሴቬኒ የሰረቁት ሁሉ ተገቢውን ፍርድ እንዲያገኙም መጠየቃቸውን የዘገባው ቢቢሲ ነው።

# የአሸናፊነት ሥነ-ልቦናን እንዴት ማዳበር ይቻላል?

**አስናቀ ፀጋዬ**



የሕይወታችን ስኬት በየቀኑ በውስጣችን በሚመላለሱ ሃሳቦችና በምንፈፅማቸው ድርጊቶች ይወሰናል። አሸናፊዎች ሁሌም የመሻሻልና የእድገት አስተሳሰብ አላቸው፡፡ ይህ አስተሳሰብ ባሉበት መርገጣቸውን በፀጋ ተቀብለው ከሚኖሩ ወይም ለመሻሻል የሚያስፈልገውን ለውጥ ለማድረግ ድፍረት አጥተው ከተቀመጡ ሰዎች በእጅጉ ይለያል፡፡ ህልማችንን እናሳካለን ወይስ ሁሌም የሌሎችን ስኬት በስስት እያየን አልያ ደግሞ የአርባ ቀን እድላችንን እንኖራለን የሚለውን ከሚወስኑት መካከል አንደኛው አስተሳሰባችን ነው፡፡ ከዚህ በታች የሚቀርቡት ሰባት ነጥቦችም አሸናፊዎች ጠንካራ አስተሳሰብና አመለካከት የሚያዳብሩባቸው መንገዶች ናቸው፡፡

1ኛ. **አሸናፊዎች ከራሳቸውም ሆነ ከሌሎች ስኬቶች ይማራሉ**

አንዳንድ ጊዜ የተሳካላቸው ሰዎች ስናይ ያገኙትን ስኬት ለማግኘት ያለፉበትን መንገድ በደምብ ተረድተን ከዛ የምንማረውን ከመለየት ይልቅ ወይ ስኬቱን እናንኳስሳለን አልያ ደግሞ ስኬቱን ያገኙት በዘመድ፣ በጉቦ፣ በስርቆት፣ በአጋጣሚ... ወዘተ ነው ብለን እናጣጥላለን፡፡ ሰርቆም ሆነ አጭበርብሮ የሚሳካለት ጥቂት ባይጠፋም የዛኑ ያህል በጠንካራ ስራ የሚያድግ አለና እነሱን ለይቶ የተሻለውን እውቀት መቅሰም ተመራጭ ነው፡፡

ሌላ ጊዜ ደግሞ እነዚህን ስኬታማ ሰዎች እንደተለዩ ሰዎች በመውሰድ ያን ስኬት ለእኛ እንደማይሆን አድርገን እንደመድማለን፡፡ ነገር ግን ይህ ልክ አይደለም። ልብ በሉ የሆነ ነገር ልታደርጉ አስባችሁ ‹‹አይ! የሄማ አይሆንም›› ስትሉ ገና ሳትጀምሩ ተሸንፋችኋል፡፡ አሸናፊዎች ሊሳሳቱ ወይም ያሰቡት ላይሳካ እንደሚችል አስቀድመው ያውቃሉ፡፡ ሳይወድቁ በፊት ግን ‹‹ተሸንፌያለሁ ወይም ያሰብኩት አልሆነም›› ብለው እጃቸውን አጣጥፈው አይቀመጡም፡፡ ያሰቡት ሳይሳካ ቢቀር እንኳን ከስህተታቸው ተምረው ለተሻለ ሕይወት የጀመሩትን ጉዞ ይቀጥላሉ፡፡

2ኛ. **አሸናፊዎች ከራሳቸውም ይሁን ከሌሎች ሰዎችና በተለያዩ ሁኔታዎች በሚመጡ መሰናክሎች ምክንያት የጀመሩትን ጉዞ አያቋርጡም**

ችግር ወይም መሰናክል አያጋጥምም ማለት አይቻልም፡፡ ነገ ግን አሸናፊዎች ለህልማቸው ታማኝ ስለሆኑ የሚያጋጥሟቸውን መሰናክል እንደሰበብ አይጠቀሙባቸውም፡፡ የሚገጥማቸውን ችግር አግዝፎ በማየትም እጃቸውን በተስፋ መቁረጥ አይሰጡም። ይልቁንም ለችግሮቹ መፍትሄ በመፈለግ የጀመሩትን ለውጥ ቀን ተቀን ይተገብራሉ፡፡ አስተውሉ ስኬት በአንድ ጀምበር የሚሆን ተዓምር አይደለም፡፡ በእያንዳንዱ ቀን የምናደርጋቸው ትንንሽ ስራዎች ስብስብ ውጤት እንጂ በሕይወታችን ውስጥ ልናደርግ የምንፈልገውን ለውጥ ከወሰንን በኋላ ያዝ ለቀቅ ማድረግ የለም፡፡ በየቀኑ ለራሳችን ስንታመን የምናደርገው ለውጥ መልካም ልማድ ሆኖ በብዙ ትግል ልንተገብረው እንችላለን፡፡

3ኛ. **አሸናፊዎች ነገሮች ባላሰቧቸው አቅጣጫ ሲሄዱ ‹‹ወይ እድሌ! ወይም የአርባ ቀን እድሌ! ነው‹‹ አይሉም፡፡**

ያን ካደረግን ከጅምሩ ከጨዋታ ውጭ ሆነናል። ማን የአርባ ቀን እድሉን መቀየር ይቻለዋል እያሉ ማማረር ተገቢ አይደለም፡፡ ማንጀሎ የተሰኘው ታዋቂው አሜሪካዊ ፀሐፊ በልጅነታቸው አያታቸው የሰጧቸው አንድ ምክር ነበር፡፡ ‹‹ሰማሽ ልጄ አንዳንድ ሰዎች በትልቁም በትንሹም ያማርራሉ፡፡ ስለሙቀቱ፣ ስለብርዱ ...ወዘተ፤ የምናማርርባቸው ነገሮች ብዙ ናቸው፡፡ ልጄ በእያንዳንዱ ቀን ከዓለማችን አንዱ ጫፍ እስከ ሌላኛው ጫፍ በሰላም ወደ አልጋቸው ሄደው ከእንቅልፋቸው ሳይነቁ የሚቀሩ ብዙ ሰዎች አሉ። ሀብታምና ደሃ፣ ነጭና ጥቁር፣ ረጅምና አጭር ብቻ እነዚህ ሰዎች አልፈዋል፡፡ ለአምስት ደቂቃ ያህል እንኳን ተመልሰው ይሄ የምናማርርበትን አየር ማየትና እንደገና መሳብ ቢችሉ ምን ያህል በተደሰቱ፡፡ ስለዚህ ልጄ አንቺም ብትሆኚ በረባ ባልረባው ከማማረር ራስሽን ጠብቂ፡፡ የማትወጂው ነገር ካጋጠመሽ ለመቀየር ሞክሪ፡፡ ያልወደድሽውን ነገር መቀየር ካልቻልሽ ደግሞ ነገሩን የምታይበትን እይታ መቀየር እንጂ አታማሪ›› ሲሉ መክረዋታል፡፡

ስለዚህ ሕይወታችንን በማንፈልገው አቅጣጫ እየሄደ ከሆነ ጊዚያችንን በማማረር ሳይሆን መፍትሄ በመፈለግ ልናሳልፍ ይገባል፡፡ ሰዎች ስለሚጠሉት ነገር ሲያማርሩ ከሚውሉ ይልቅ የሚወዱት ነገር ላይ በትጋት ቢሰሩ ዓለም እንዴት የተሻለች ትሆን ነበር፡፡

**4ኛ. አሸናፊዎች የሚደሰቱት በሌሎች ሰዎች ውድቀት ወይም መከራ አይደለም**

ሌሎች ሰዎች ሲያሸንፉ ወይም ሲሳካላቸው ማየት ደስ ይላቸዋል፡፡ ስለሆነም የሚናገሩት ነገር ሰዎችን የሚያበረታታ እንጂ ሰዎችን የሚጎዳ ወይም ተስፋ የሚያስቆርጥ እንዳይሆን ይጠነቀቃሉ፡፡ ምክንያቱም ቃል ይገድላልም፤ ያንፃልምና፡፡ ነገር በምሳሌ ጠጅ በብርሌ እንደሚባለው ለዚህ እውነት አስረጂ ታሪክ እንካችሁ፡፡

በአንድ ወቅት ብዙ እንቁራሪቶች በአንድ ላይ ሆነው በጫካ ውስጥ እየሄዱ እያለ ሁለት እንቁራሪቶች ጥልቅ ከሆነ ጉድጓድ ውስጥ ወደቁ፡፡ ከገደል ያልወደቁት እንቁራሪቶች ከጉድጓዱ አፋፍ ዙሪያ ተሰባስበው የጉድጓዱን ጥልቀት ተመለከቱና ሁለቱን እንቁራሪቶች ‹‹አዬ ጉድ ምን አይነት ጉድ አገኛችሁ እናቴ! ይሄ ጉድጓድ ጥልቅ ነው መውጣት አትችሉም›› አሏቸው ሁለቱ እንቁራሪቶች ግን ከጉድጓዱ ዘለው ለመውጣት ጥረታቸውን ሳያቋርጡ ቀጠሉ፡፡ ከጉድጓድ ውጭ ያሉ እንቁራሪቶችም ‹‹ይሄ ነገር ተስፋ የለውም ነው የምንላችሁ፤ ዝም ብላችሁ ነው የምትደክሙት›› ማለታቸውን አላቋረጡም፡፡

ከብዙ ቆይታ በኋላ ታዲያ አንደኛው እንቁራሪት ውጭ ያሉ እንቁራሪቶች የሚሉትን ተቀብሎ ዘሎ ለመውጣት ሲያደርግ የነበረውን ጥረት አቆመ፡፡ ተስፋውን ሲያጣም ነው መሰል ብዙም ሳይቆይ ሞተ። ሌላኛው እንቁራሪት ግን ምንም ያህል ቢደክመው መዝለሉን አላቋረጠም። ውጭ ያሉት እንቁራሪቶችም ‹‹ኧረ አሟሟትህን እንኳን አሳምር፤ እንደው ዝም ብለህ አትድከም፤ አጉል መንፈራገጥ ለመላላጥ ነው ሲሉ አልሰማህም›› እያሉ መጮሃቸውን ቀጠሉ፡፡ ያ እንቁራሪት በመጨረሻ ጥረቱ ፍሬ አፍርቶ ከጉድጓድ መውጣት ቻለ፡፡

ውጭ ያሉት እንቁራሪቶችም ዙሪያውን ከበው ‹‹አልሰማኸንም እንዴ? እኛ እኮ ያለመታከት ተው ይቅርብህ ብለንህ ነበር›› ቢሉት እንቁራሪቱ ግን ምን እያሉት እንደሆነ እንኳን ሊገባው አልቻለም፡፡ ለካስ መስማት አይችልም ነበር፡፡ ያን ሁሉ ጊዜ ጉድጓድ ውስጥ ሆኖ አትችልም፤ ይቅርብህ እያሉ ሲጯጯሁ ‹‹በርታ! ትንሽ ነው የቀረህ!›› እያሉት መስሎት ነበር ዝላዩን ያላቋረጠው፡፡

ስለዚህ ለጓደኞቻችን፣ እህቶቻችን፣ ወንድሞቻችንና ልጆቻችን የምንሰጣቸው ምክሮችና የምንናገራቸው ነገሮች ለሕይወታቸው ትልቅ ትርጉም ስለሚኖረው ቃላቶቻችንን መምረጥ ተገቢ ነው፡፡

5ኛ. **አሸናፊዎች ከሚያሳንፉና ተስፋ ከሚያስቆርጡ ሀሳቦች ራሳቸውን ይጠብቃሉ**

**አሸናፊዎች ከራሳቸውም ይሁን ከሌሎች ሰዎችና በተለያዩ ሁኔታዎች በሚመጡ መሰናክሎች ምክንያት የጀመሩትን ጉዞ አያቋርጡም ችግር ወይም መሰናክል አያጋጥምም ማለት አይቻልም**

በእያንዳንዱ ሰው ጭንቅላት ውስጥ በአማካይ ወደ ስልሳ አራት ሺ ሃሳቦች በየቀኑ ይመላለሳሉ። አብዛኛውን ጊዜ እነዚህ ሀሳቦች ያለኛ ቀጥተኛ ፍቃድ ነው በአእምሯችን ሲመላለሱ የሚውሉት። አስተውላችሁ ከሆነ የሆነ ነገር እየሰራችሁ ወይም ዝም ብላችሁ በተቀመጣችሁበት በሀሳብ ሩቅ ሄዳችሁ ብንን ስትሉ ወይ ስላለፈ ጊዜ አልያም ገና ስለሚመጣው ጊዜ ስታውጠነጥኑ ራሳችሁን ታገኙታላችሁ፡፡ ከየት ተነስታችሁ እንዴት እዛ እንደደረሳችሁ ግር እስኪላችሁ ድረስ፡፡ የእንደዚህ አይነት ሀሳብ ችግሩ ብዙን ጊዜ ወይ ድሮ ስለሰራነው ስህተት፣ ስላመለጠን እድል፣ ስላላገኘነው እድገት... ወዘተ አልያ ደግሞ መጪውን ጊዜ በፍራቻና በስጋት ማየታችን ነው፡፡

አሸናፊዎች ሀሳባቸውን ይመረምራሉ፡፡ በውስጣቸው ለሕይወታቸው መሻሻል የማያግዙ ሃሳቦች ብልጭ ሲሉ በፍጥነት ይቀጯቸዋል፡፡ አትችልም አልችልም፣ ከባድ ነው አይሆንም፣ አንተማ እንዴት ሆኖ፣ አንቺማ በየት ብለሽ አይነት ጨለምተኛና ጎታች ሃሳቦችን ቦታ አይሰጧቸውም፡፡ ይልቁንም ‹‹እችላለሁ፤ እደርሳለሁ ፈጣሪ የሚያስፈልገኝን እምቅ አቅም ሰጥቶኛል ያን ደግሞ አውጥቶ መጠቀም የኔ ኃላፊነት ነው ለዛም ጠንክሬ እሰራለሁ፤ ህልሜንም አሳካለሁ›› ብለው ጉልበት የሚሰጡ ሃሳቦችን ያዘወትራሉ፡፡

6ኛ. **አሸናፊዎች መድረስ የሚፈልጉበትን ቦታ በግልፅ ያውቁታል**

አሸናፊዎች ህልማቸውን ሲያልሙም በትልቁ ነው፡፡ ይሆናል ብላችሁ ከምታስቡት በላይ አልሙ፡፡ አለበለዚያ ሁሌ ልንደርስበት የምንችልበትን ቦታ አሳንሰን ስለምንነሳ ጥረታችንም ያን ያህል ትንሽ ይሆናል፡፡ ትንሽ ችግር መንገዳችን ላይ ሲያጋጥመን ስንነሳ ከሰነቅነው ትንሽ ህልም ያነሰ ቦታ የመድረስ እድላችን ይሰፋል። ያን ካደረጋችሁ በኋላ በሕይወታችሁ የምታዩትን ለውጥ በቀጣይነት ገምግሙ፡፡ የምትከታተሉት ያሰባችሁበት ቦታ የመድረስ ያለመድረሳችሁን ብቻ ሳይሆን ከእለት እለት በሕይወታችሁ የምታዩትን ለውጥ መሆን አለበት፡፡

ለምሳሌ አንድ መቶ ኪሎ ግራም የሚመዝን ሰው ቢኖርና ወደ ሰባ ኪሎ ግራም መቀነስ ቢፈልግ ከአምስት ወር ጥረት በኋላ ራሱን ሲለካ ሰማንያ አምስት ኪሎ ግራም ቢመዝን ሰባ አለመድረሱ ደስታውን ሙሉ ባያደርገውም እያሳየ ላለው ለውጥ ተገቢውን እውቅና ካልሰጠ ተስፋ ቆርጦ ከጀመረው መልካም መንገድ ሊያፈገፍግ ይችላል። ሰማንያ አምስት ኪሎ ግራም ላይ ለመድረስ በራሱ ብዙ ለውጦችን አድርጎ ወይም አድርጋ ሊሆን ይችላል፡፡ ለአብነትም በየቀኑ ስፖርት መስራት፣ ጤናማ የአመጋገብ ስርአትን መከተል፣ አስፈላጊውን ያህል እንቅልፍ በየቀኑ መተኛት .... ወዘተ፡፡ እነዚህ ለውጦች በራሳቸው እንደ ትልቅ ድል ተቆጥረው ለቀጣዩ ጥረት የበለጠ መነቃቃት እርሾ መሆን ይችላሉ፡፡

ለዚህ ነው መድረስን ብቻ ሳይሆን መቅረብን መከታተል ያስፈልጋል የሚባለው፡፡ ትልቅ ህልም ከሰነቅን በኋላ ያንን ህልም ማሳካት የምንችልበት እቅድ ያስፈልጋል፡፡ ያ እቅድ ሊኖሩት ከሚገባቸው ነገሮች አንዱ የጊዜ ሰሌዳ ነው፡፡ መቼ ምን አድርገን መቼ ውጤቱን ለውጡን ለማየት እናስባለን፤ አለበለዚያ እንዲሁ በድፍኑ ሀብታም መሆን እፈልጋለሁ፣ በስራ ቦታዬ እድገት ማግኘት እፈልጋለሁ፣ ስራ ማግኘት እፈልጋለሁ፣ ሚስት ማግባት እፈልጋለሁ....ወዘተ ቢባል አይሰራም፡፡ አስፈላጊውን ሥራ የምንሰራበትና ቆም ብለን ራሳችንን የምንገመግምበት ግልፅ ቀን፣ ሳምንት፣ ወር ወይም ዓመት ያስፈልገናል፡፡

7ኛ. **አሸናፊዎች ከተለያዩ ሰዎች ጋር ጠንካራ ማህበራዊ የስራ፣ የቢዝነስ ወዘተ ግንኙነትን ይመሰርታሉ**

ለብቻ የሚሆን ነገር የለም፡፡ ከሰዎች ጋር የምንመሰርታቸው ግንኙነቶች መረጃ ለመለዋወጥ በሃሳብ ለመረዳዳት፣ በስራ ለመተጋገዝ ወዘተ ወሳኝ ናቸው፡፡ ሕይወታችሁ እንዲሄድ በምትፈልጉት መንገድ ላይ ያሉ ወይም ተመሳሳይ ህልም ካላቸው ሰዎች ጋር መሆን ጉዟችሁን የተቃና ሊያደርገው ይችላል፡፡ ታዲያ በእንደዚህ አይነት ግንኙነት ውስጥ ከሰው የምንጠብቅ ብቻ ሳንሆን ይነስም ይብዛ የአቅማችንን የምናበረክትም ብንሆን መልካም ነው፡፡

በዚች ዓለም መውደቅም መነሳትም ያለ ነው፡፡ አንዱ ሲሳካለት ሌላኛው ይወድቃል፡፡ የወደቀው ሲነሳ የተሳካለት መልሶ ይወድቃል፡፡ ዋናው ቁምነገሩ ግን ከውድቀት ተምሮ ዳግም ላለመውደቅ መጣር ነው። ስኬትና አሸናፊነት ደግሞ እንዲሁ በቀላሉ የሚመጣ ባለመሆኑ ሁሌም ቢሆን የሚያጋጥሙ መሰናክሎችን ለመቋቋምና እንደ አመጣጣቸው ለመመለስ ራስን ማዘጋጀት እንዲሁም ለችግሮች መፍትሄ መፈለግ ያስፈልጋል፡፡

እናም ሰው ሆይ ህልምን ለማሳካትና አሸናፊ ለመሆን ከፈለክ እነዚህን ሰባት ነጥቦችን ተግባራዊ ለማድረግ ይሞክር!! ነገር ግን እነዚህ ነጥቦች አንዳንዴ ላይሰሩም የሚችልበት እድል ስለሚኖር ከራስ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር በማዛመድ ተግባራዊ ማድረጉ አይከፋም፡፡

## ከቅዱስ አማኑኤል የአእምሮ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል ጋር በመተባበር በየሳምንቱ የሚታተም

# የሆስፒታሉ አመሰራረት እና የአእምሮ ሕክምና በኢትዮጵያ

**አብዩ የኔአለም**

በአገራችን ካሉ ጥቂት አንጋፋ የህክምና ተቋማት መካከል ግንባር ቀደም እና በሚሰጠው አገልግሎት ብቸኛ በመሆን የሚታወቀው ቅዱስ አማኑኤል የአዕምሮ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል በ1930 ዓ.ም በጣሊያን ወረራ ጊዜ የተመሰረተ ሲሆን በዓለም ዓቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ያለው ስትራቴጂ እየተገበረ ያለ ተቋም ነው።

የፋሺስት ጦር በ1928 ዓ.ም አዲስ አበባን ከተቆጣጠረ በኋላ ከተማዋን ለአገዛዝ በሚመቸው መልኩ ለመሪዎች፤ ለጦር ሰፈር፤ ለነጮችና ለባንዳ ጀሌዎች ሳይቀር በከፋፈለበት ወቅት በአገሪቱ የነበሩ የጤና ተቋማትም በክፍፍሉ እጣ ውስጥ ገቡ። በዚህም በአገሪቱ ውስጥ ያሉ አምስት አንጋፋ ሆስፒታሎች ማለትም ዳግማዊ ምኒልክ ሆስፒታል፤ የቀድሞው ሆስፒታል ላምቤ የአሁኑ ፓስተር ፤ የቀድሞ ኃይለ ስላሴ የአሁኑ የካቲት 12፤ እና ዘውዲቱ ሆስፒታሎች መካከል አንዱ የሆነው አማኑኤል ሆስፒታልም በዚህ ዕጣ ውስጥ ተካተተ።

ቅዱስ አማኑኤል የአዕምሮ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል ከሌሎቹ በተለየ መልኩ በወቅቱ በነበረው የመደብ ልዩነት ምክንያት ለጥቁር ኢትዮጵያውያን አገልግሎት እንዲሰጥ ተደረገ። ይህ አንጋፋ ሆስፒታል በወቅቱ አገልግሎቱ ለአዕምሮ ህክምና ተብሎ ሳይሆን ለጠቅላላ አገልግሎት እንዲውል ተደርጎ የተገነባ ነበር። ከአምስት ዓመት በኋላ በ1933 ዓ.ም የጣሊያን ጦር ተሸንፎ ከአገሪቱ ሲወጣ በከተማው የነበሩ ሆስፒታሎች ራስ ደስታ ሆስፒታልን ጨምሮ በወቅቱ ለነበረው ህብረተሰብ በቂ ናቸው በሚል በጦርነት ሳቢያ በከተማዋ እየተስተዋለ የመጣውን የአዕምሮ ጤና ችግር መጨመር፤ ከጭንቀት ጋር ለተያያዙ ችግሮች መፍትሄ ለማበጀት፤ የአዕምሮና የባህሪ ችግር ላለባቸው ሰዎች አገልግሎት እንዲሰጥ ተደረገ። በተለይም በየካቲት 12 ቀን የግራዚያኒን የግድያ ሙከራ ተከትሎ በዜጎቻችን ላይ የደረሰው ጭፍጨፋ በብዙዎች ላይ የአካልና ስር የሰደደ የአዕምሮ ጉዳት አድርሶ ስለነበር እጅግ በርካታ ወላጅና ጧሪ አልባ ዜጎች በየቤቱ ወድቀው ረዳት ባጡበት ሰዓት ከሁሉም ለከፋው የአዕምሮ ችግር ተጠቂዎች ሆስፒታሉን ክፍት ማድረግ የተሻለ እንደሆነ ታመነበት። በመሆኑም በመንግስት ፍቃድ አግኝቶ ሆስፒታሉ በ1930ዎቹ መጨረሻ የአዕምሮ ጤና ችግር ማገገሚያ ቦታ ሆኖ በመቋቋም ስራውን በይፋ ጀመረ። በወቅቱ ሆስፒታሉን ተረክቦ የነበረው አገር ግዛት ሚኒስቴር ቢሆንም በ1940ዎቹ መባቻ ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር በአዋጅ ሲቋቋም ሆስፒታሉን ተረክቦ ማስተዳደር ጀመረ።

ከተቋቋመ 80 ዓመታትን ያስቆጠረው ይህ አንጋፋ ሆስፒታል የአሁኑን ስያሜ ከማግኘቱ በፊት «ተክለ ሃይማኖትና አካባቢው ሆስፒታል» ተብሎ ይጠራ የነበረ ሲሆን ከጥቂት ጊዜ በኋላም ከሆስፒታሉ ጎን ከነበረው አማኑኤል ቤተ-ክርስቲያን በመነሳት የአሁኑን ስያሜውን አገኘ። እስከ 1960 ዎቹ ድረስ ከህንድ፤ ከአርጀንቲና፤ ከእንግሊዝና ከቀድሞዋ ዩጎዝላቪያ በተለያየ ጊዜ በበጎ አድራጎት ተግባር እየመጡ የህክምና አገልግሎት በመስጠትና በማስተዳደርም ጭምር በሆስፒታሉ ትልቅ አሻራቸውን ያኖሩ ግለሰቦችም እንደነበሩ መረጃዎች ያትታሉ። በዚህም የአብዮቱን መምጣት ተከትሎ ብዙ የምስራቅ አውሮፓ አገራት ለተለያዩ ህክምናዎች ወደ አገሪቱ መምጣት ጀመሩ። በተለይም የኩባ፤ የራሺያ፤ የቡልጋሪያ፤ ሃንጋሪና ሌሎችም ዶክተሮች በስፋት ይመጡ ስለነበር አማኑኤል ሆስፒታልም የአዕምሮ ህክምና ባለሞያዎችን በስፋት ማግኘት ጀመረ።

በተቋሙ ምንም እንኳን በተለያዩ ጊዜያት የውጭ ዜጋ የሆኑ የህክምና ባለሞያዎች ከባህር ማዶ መጥተው አገልግሎት ቢሰጡበትም በአገር ውስጥ ምንም ዓይነት የሰለጠነ የሳይካትሪስት እና የስነ-ልቦና ባለሙያ የሌለውን የህክምና ተቋም የአገሪቱ መንግስትና ባለስልጣናቱ ድጋፍ የማያደርጉለትና መጥተው የማይጎበኙት ሆኖ ለረጅም ጊዜ ተረስቶ ኖሯል። በ1970ዎቹ ዓ.ም መጀመሪያ ላይ የቀድሞ የዩጎዝላቪያ ተወላጅ የሆኑት ዶክተር ማሪንኮ ፓቪቼቪች (D.r Marinko Pavicevic) ለረዥም ጊዜ ሆስፒታሉን በዳይሬክተርነትና ሃኪም በመሆን አገልግለዋል። በእኚህ የህክምና ዘመን የኤሌክትሪክ ንዝረት ህክምና ECT (Electro-Convulsive Therapy) ተጀመረ። በዚህም ሳያበቃ በወቅቱ በነበር መንግሥታዊ ጋዜጣ ላይ በአንደኛው ገጽ እንደተጻፈው "... ዐውቆ አበዶችን የሚያጋልጥ መሣሪያ አማኑኤል ሆስፒታል በሥራ ላይ አዋለ" የተባለለት የአንጎል ኤሌክትሪክ እንቅስቃሴ መዝጋቢ መሣሪያ EEG (Electro-Encephalo Graph) ሥራ ላይ ዋለ።

ኤርትራ በዘመኑ የኢትዮጵያ አንደኛዋ ጠቅላይ ግዛት ስለነበረች በአገሪቱ ሁለተኛው የአዕምሮ ሆስፒታል በጣልያናዊው የነርቭና አዕምሮ ስፔሻሊስት ፕሮፌሰር ሲልላ ይመራ የነበረው በአሥመራ ከተማ ልዩ ስሙ ጸጸረት በሚባለው አካባቢ የሚገኘው ቅድስት ማርያም ሆስፒታል ተጠቃሽ ነው። በወቅቱም በተጠቀሰው ሆስፒታል ያገለግሉ የነበሩ ዶክተር ቦያጂቭ/ቫ የሚባሉ ቡልጋርያውያን ባልና ሚስት የአዕምሮ ሐኪሞች ይታወሳሉ።

ከዶክተር ፓቪቼቪች ህልፈት ተከትሎ አገራችንም ወደ ሶሻሊስቱ ጎራ ተጠቃልላ በመግባቷ የአዕምሮ ሐኪሞች ከሁለቱም ጾታ ከአጋር የምሥራቅ አገራት ወደ አገራችን መምጣት ጀመሩ። ቀደም ብለው ከመጡት ሐኪሞች ውስጥ ዶክተር ካራጆቫ (Dr. Karajova) እና ዶክተር ሉኪች (Dr. Lukich) ተጠቃሾች ናቸው። በተለይም ዶክተር ካራጆቫ (Dr. Karajova) በተደጋጋሚ የአማኑኤል ሆስፒታል ዳይሬክተር በመሆን አገልግለዋል። በመቀጠልም ዶክተር አሴኖቭ (Dr. Acinov) እና ዶክተር ኢቫኖቫ (Dr. Evanova) ከቡልጋሪያ፤ ዶክተር ኦብሮሶቭ (Dr. Obrosove) እና ዶክተር ኢና (Dr. Ena) ከቀድሞዋ ሶቪየት ህብረት፤ በጠቅላላ ሐኪምነት ደግሞ ዶክተር ሱክ (Dr. Suk)፣ ዶክተር ኩ (Dr. Ku)፣ ዶክተር ሊ (Dr. Lee) ከደቡብ ኮርያ፤ እና ሌሎችም ከስድሳዎቹ አጋማሽ እስከ ሰማኒያዎቹ መጀመርያ ድረስ አማኑኤል ሆስፒታልን በትጋት አገልግለዋል።

## ከአዲስ አበባ ከተማ ፕላንና ልማት ኮሚሽን ጋር በመተባበር በየወሩ የሚታተም

# የመሬት አጠቃቀም ምድቦች

**በስጥሻቸው ልዑልሰገድ**

በከተማው ውስጥ የሚከናወኑ የልማት ሥራዎችን በፕላን በመምራትና በመቆጣጠር የከተማውን እድገት እና ልማት ማሻሻል፤ እና በከተማው ውስጥ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተመዘገበ ያለውን እድገት እና ልማት በፕላን በመደገፍ ቀጣይነቱን የበለጠ ማረጋገጥን ዓላማው ያደረገው የአዲስ አበባ መዋቅራዊ ፕላን አዋጅ ቁጥር 52 /2017 የመሬት አጠቃቀም ፕላን አበይት ምድቦችን በ14 አብይ እና 72 ንዑሳን ምድቦች ከፍሎ ያስቀምጣቸዋል። እነዚህም:- ቅይጥ መኖሪያ፣ ንግድ ሥራ፣ አስተዳደራዊ አገልግሎት፣ ማህበራዊ አገልግሎት፣ ማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎት፣ የመጓጓዣ አገልግሎት፤ የመሠረተ ልማት አገልግሎት፣ የመንገድ መረብ፣ የአካባቢ ጥበቃ፣ የከተማ ግብርና፣ ማምረቻና ማከማቻ፣ ልዩ ፕሮጀክቶች፣ ታሪካዊ ግንባታዎችና ስፍራዎች፤ እና ጥብቅ አካባቢዎች መሆናቸውን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፕላንና ልማት ኮሚሽን ኮሚሽነር ዳዲ ወዳጆ (ዶ/ር) ይገልፃሉ።



ዶክተር ዳዲ ወዳጆ

እንደ ዶክተር ዳዲ ገለፃ፥ ቅይጥ የመኖሪያ መሬት አጠቃቀም ምድብ ስንል:- አነስተኛ ጥግግት ያለው ቅይጥ የመኖሪያ መሬት፣ መካከለኛ ጥግግት ያለው ቅይጥ የመኖሪያ መሬት፣ ከፍተኛ ጥግግት ያለው ቅይጥ የመኖሪያ መሬት፣ ከአካባቢ ጥበቃና ከአረንጓዴ የደን ክልል ቦታ ተነስተው ለሚሰፍሩ ነዋሪዎች የተከለለ መሬት አጠቃቀምን ያካትታል፤ ከወንዝ ዳርቻ ክልልና ከተለያዩ አነስተኛ የአረንጓዴ መናፈሻ ቦታዎች የሚነሱ ነዋሪዎች በወንዝ ዳርቻና መናፈሻ ፕሮጀክቶች መሰረት በልማቱ ይታቀፋሉ።

ሌላው የንግድ ሥራ መሬት አጠቃቀም ምድብ ሲሆን የንግድ ሥራ ቦታ እና የገበያ ቦታ ምድብን በውስጡ ያካተተ ነው የሚሉት ኮሚሽነሩ፤ ከአነስተኛ እስከ ከፍተኛ የገበያ አይነት ድረስ በዚህ ምድብ ይካተታሉ። የአስተዳደራዊ ተቋማት መሬት አጠቃቀም ስንል የመንግስታዊ ተቋማት ቦታ እና የበይነ መንግስታዊ ተቋማት ቦታዎችን የሚያካትት ሲሆን የመንግስታዊ ተቋማት ቦታ፤ የከተማ አስተዳደር፣ የክፍለ ከተማ አስተዳደር፣ የወረዳ አስተዳደር እና ሌሎች መንግስታዊ ተቋማትን ያጠቃለለ ነው። በማናቸውም የአስተዳደራዊ ተቋም ቦታ ምድብ የማምረቻና ማከማቻ መጋዘን፣ የቆሻሻ አያያዝ ጣቢያ እና ቆሻሻ ማጎሪያ ቦታ፣ መካነ-መቃብር፣ የሃይማኖት ድርጅት የአምልኮ ተቋም፣ ካባና ማዕድን ማውጫ፣ ስቴዲየም፣ ማረሚያ ቤት እና ወታደራዊ ተቋም መገንባት እንደማይቻልም ይናገራሉ።

የማህበራዊ አገልግሎት መሬት አጠቃቀም ምድብ ለማህበረሰቡ የተለያዩ አገልግሎቶችን የሚሰጡ እንደ ትምህርት፣ ጤና፣ የስፖርት ማዘውተሪያ እና የህብረተሰብ እንክብካቤ ማዕከላት የሚያጠቃልል የመሬት ምድብ ሲሆን የአምልኮ ቦታዎችንም ጭምር እንደሚያጠቃልል ኮሚሽነሩ ያስረዳሉ።

ዶክተር ዳዲ እንደሚጠቅሱት፤ የእሳትና ድንገተኛ አደጋዎች አገልግሎት፤ የቄራ አገልግሎት፤ አረንጓዴ መካነ መቃብር፤ የክብረ በዓልና ክፍት የሕዝብ መናኸሪያ ቦታዎች እና ባህላዊና ማህበረሰብ አቀፍ ማዕከላት በማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎት ምድብ ውስጥ ይመደባሉ። በእያንዳንዱ የማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎት ቦታ ንዑስ ምድብ በመሬት አጠቃቀም ፕላኑ ከተመደበለት አገልግሎት ውጭ ግንባታ ማካሄድ እንደማይቻል ተደንግጓል።

የመሰረተ ልማት አገልግሎት የመሬት አጠቃቀም ምድብ ስር ውሃ ማከማቻ፣ ኤሌክትሪክ ኃይል ጣቢያ፣ ከፍተኛ የኤሌክትሪክ መስመር ክልል፣ ቀላል ባቡር ኃይል ጣቢያ እና ቴሌኮሚዩኒኬሽን ጣቢያ ተካተዋል። የመጓጓዣ አገልግሎት የመሬት አጠቃቀም ምድብም፡ - መናኸሪያና መኪና ማቆሚያ ጣቢያ በተሰኙ ሁለት ንዑስ ምድቦች ተለይቶ በመሬት አጠቃቀም ፕላኑም ሆነ በመንገድና መጓጓዣ መረብ ፕላን ተወስኗል። የከተማ አውቶቡስ መናኸሪያ፣ የከተማ ለከተማ አውቶቡስ መናኸሪያ፣ አገር አቋራጭ አውቶቡስ መናኸሪያ፣ አውቶቡስ ማሳደሪያ፣ አየር ማረፊያ፣ ቀላል ባቡር ጣቢያ እና አገር አቋራጭ ባቡር ጣቢያ፣ ጭነት መጓጓዣ መናኸሪያ እና ታክሲ መናኸሪያ ያካትታል በማለት ያስረዳሉ።

የመንገድ መረብ መሬት አጠቃቀም ምድብ በሶስት ዝርዝር ምድቦች ተለይቶ መመደቡን የሚገልፁ ኮሚሽነሩ፤ ዋና መንገድ፣ መለስተኛ ዋና መንገድ እና መጋቢ መንገድ እንደሚካተቱና የውስጥ ለውስጥ መንገድ ደግሞ በከተማ ፕላን የአሰራር ደንቦች፣ ሙያዊ ልምዶችና ደረጃዎች መመሪያ እና ኮሚሽኑ በሚያዘጋጀው ዝርዝር ዲዛይን መሰረት ይወሰናል ይላሉ።

የአካባቢ ጥበቃ የመሬት አጠቃቀም ምድብ፤ አረንጓዴ መሰረተ ልማት፣ የቆሻሻ ማጎሪያ ቦታና የፈሳሽ ቆሻሻ አያያዝ ጣቢያ እና ካባ እና የውሃ አካላትን የተባሉ ንዑስ-ምድቦችን ያጠቃልላል። ለካባ አገልግሎት የዋለ ቦታ አገልግሎቱ ሲያበቃ፣ ለሕዝብ ተደራሽ በሆነ አረንጓዴ ልማት እንዲውል ተደርጎ መደልደል፣ መስተካከል እና መልማት ይኖርበታል። በከርሰ ምድር እና በገጸ ምድራዊ ውሃ አካላት መከላከያ ቀጠና ቦታ ምድብ ግንባታ ለማካሄድ አግባብ ባለው የአካባቢ ጥበቃ ሕግ መሰረት የአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ በቅድሚያ በማካሄድ ችግር የማያስከትል መሆኑ መረጋገጥ እንደሚጠበቅበትም ዶክተር ዳዲ ያብራራሉ።

በከተማ ግብርና የመሬት አጠቃቀም ምድብ ውስጥ አትክልት፣ ፍራፍሬ እና ዛፎች ማልማት እንዲሁም የእንስሳት እርባታና ተዋጽዖ ልማት ለንግድ ዓላማ ማካሄድ ይቻላል። በከተማ ግብርና የመሬት አጠቃቀም ውስጥ ፀረ-ተባይና ኬሚካላዊ ሰው ሰራሽ ማዳበሪያ መጠቀም እና ከከተማ ግብርና ጋር በቀጥታ ተያያዥነት ካላቸው ተግባራት ውጪ የሆነ ሥራ ማካሄድ ክልክል ነው።

ማምረቻና ማከማቻ፣ ነዳጅ ዲፖ፣ እህል ጎተራ እና ከግብርና ቦታዎች ለሚነሱ ለመኖሪያና ለአነስተኛና ጥቃቅን ሥራዎች የሚውሉ ቦታዎች የማምረቻና ማከማቻ የመሬት አጠቃቀም ምድብ ውስጥ የተካተቱ መሆናቸውን የሚናገሩት ኮሚሽነሩ፤ የታሪካዊ ግንባታዎችና ሥፍራዎች የመሬት አጠቃቀም ምድብ በተመለከተም ታሪካዊ ሕንፃዎችና መዋቅሮች እንዲሁም ታሪካዊ ስፍራዎችን ያጠቃለለ ሲሆን በታሪካዊ ግንባታዎችና ስፍራዎች የመሬት አጠቃቀም ውስጥ ያሉትን ከማደስና ከመንከባከብ ውጪ ግንባታውን የሚመለከት ሌላ ተግባር መፈፀም እንደማይፈቀድ ያስረዳሉ።

ኢኮኖሚ

# መሠረተ ልማት

## የሴቶች የተሃድሶ እና የክህሎት ማበልጸጊያ ስልጠና ማዕከል ግንባታ

መላኩ ኤሮሴ

የአገራችን ብሎም የመዲናዋ አዲስ አበባ ሴቶች ከሚያጋጥማቸው ችግሮች አንዱ ኢኮኖሚያዊ ችግር ነው። ይሁንና ይህን ኢኮኖሚያዊ ችግር በትዕግስት ተቋቁመው በተለያዩ የስራ መስኮች ላይ ተሰማርተው ሴት የባሏን እጅ ጠባቂ የሚያደርገውን የተሳሳተውን የማህበረሰቡን አመለካከት መለወጥ የቻሉ በርካታ እንስቶች አሉ። በይቻላል መንፈስ ተነስተው ችለው ያሳዩንን በርካታ ኢትዮጵያውያን ሴቶችንም መጥቀስ ይቻላል፡፡ በአንጻሩ ጥቂት የማይባሉ ሴቶች ደግሞ ሴተኛ አዳሪነትን ጨምሮ በአስቸጋሪ ስራዎች ላይ ጭምር በመሰማራት ኢኮኖሚያዊ ችግሮችን ለመፍታት ሲጥሩ ይታያል፡፡

ከ10 ዓመት በፊት በተደረገው ጥናት በአዲስ አበባ ከ15ሺህ በላይ በሴተኛ አዳሪነት እንደተሰማሩ ጠቁሟል። ከነዚህ ዓመታት ወዲህ የተደረጉ ጥናቶችን ማግኘት ባንችልም፣ ባለፉት ዓመታት የተከሰቱ ሰው ሰራሽ (ጦርነት) እና ተፈጥሯዊ ችግሮችን (ኮቪድ እና ድርቅ) ተከትሎ በተፈጠሩ ምስቅልቅሎች ምክንያት አሀዙ በከፍተኛ ሁኔታ ሊጨምር እንደሚችል ይገመታል፡፡

ለሴተኛ አዳሪነት እና ሴቶችን የሚያጋጥሟቸውን ሌሎች ችግሮችን ለመፍታት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በተለያዩ ወቅቶች የተለያዩ ጥረቶች ሲያደርግ ነበር፡፡ ከነዚህ ጥረቶች መካከል በዚህ ተግባር ላይ ለተሰማሩ ሴቶች የስራ መጀመሪያ ብድር፣ የመስሪያ ቦታ፣ ስልጠናና የመሳሰሉትን በማመቻቸት ቋሚ የኢኮኖሚ አቅም እንዲያዳብሩ ማድረግ አንዱ መንገድ ነው፡፡

ይሁን እንጂ በከተማዋ ውስጥ እየተስፋፋ የመጣውን የሴተኛ አዳሪነት ህይወትን ለማስቀረትና ሌሎች ችግሮችን ለመፍታት አላስቻለም፡፡ ችግሩን ለመፍታት ያልተቻለበት ዋነኛው ምክንያት የተከናወኑ ተግባሮች ችግሩን በዘላቂነት ለመቀነስ የሚያስችሉ ባለመሆናቸው ነው፡፡

የከተማ አስተዳደሩ እነዚህን ችግሮች ለመፍታት የሚያደርገውን ጥረት አሁንም ቀጥሏል፡፡ በተለያዩ ምክንያቶች ጎዳና ላይ የወጡ ሴቶችን ካሉበት ችግር ለማላቀቅ የሚያግዝ ማዕከል ግንባታም በቅርቡ ተጀምሯል። በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ እየተገነባ የሚገኘው ይህ ማእከል በተለያዩ ችግሮች ውስጥ የሚገኙ ሴቶች የተሃድሶ እና የክህሎት ማበልጸጊያ ስልጠና የሚያገኙበት ነው፡፡

ኢንጂነር ዙሪያወርቅ ወዳጆ በአዲስ አበባ ትላልቅ ፕሮጀክቶች ግንባታ ጽህፈት ቤት የሴቶች የተሃድሶና የክህሎት ማበልጸጊያ ማዕከል ግንባታ ተወካይ ናቸው፡፡ ኢንጂነር ዙሪያወርቅ እንደሚናገሩት፤ በማዕከሉ የተሃድሶ እና የክህሎት ማበልጸጊያ ስልጠና ይሰጣል፤ የተሃድሶ እና የክህሎት ማበልጸጊያ ስልጠናው ተጠቃሚ የሚሆኑት ደግሞ በዋናነት ከጎዳና የሚነሱ ሴቶች ናቸው፡፡ በራሳቸው የመማር አቅም የሌላቸው፣ ሙያ ነክ ስልጠናዎችን መውሰድ እየፈለጉ ስልጠና መውሰድ ያልቻሉ ሴቶችን ከጎዳና ላይ በማንሳት ስልጠና እንዲያገኙ የሚደረግበት ይሆናል፡፡

በአንድ ጊዜ 2000 ሴቶችን የሚያሰልጥንና የክህሎት ባለቤት እንዲሆኑ የሚያስችል ሲሆን፣ በዓመት ደግሞ እስከ 10ሺህ ሴቶች የተለያዩ ሙያ ነክ ስልጠናዎችን እንዲያገኙ የሚያደርግ ትልቅ ማዕከል ነው፡፡ የማዕከሉ ስልጠና ሴቶች በተለያዩ የሙያ ዘርፎች የሚያገኙትን ክህሎት በመጠቀም ራሳቸውን እና አገራችውን የሚጠቅሙ እንዲሆኑ ያስችላል።

ማዕከሉ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ፋይዳው ከፍተኛ ነው፤ የጎዳና ሴቶችን ከችግር ከማላቀቅ ባሻገር በኢኮኖሚ ረገድ የላቀ ጥቅም ይኖረዋል፡፡ የጎዳና ላይ ሴቶችን አንስቶ የክህሎት ባለቤት እና አምራች እንዲሆኑ ያስችላል፡፡ የከተማዋን ገጽታም በመሰረታዊነት ይቀይራል፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ የማዕከሉን ግንባታ መሰረተ ድንጋይ ባስቀመጡበት ወቅት እንደተናገሩት፤ የሴቶች የተሃድሶና የክህሎት ማበልጸጊያ ማዕከል የአገሪቷን ወይም የከተማዋን ሴቶች ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ችግሮችን ብቻውን ይፈታል ተብሎ አይታሰብም። ነገር ግን በዋናነት በአዲስ አበባ ለተለያዩ ችግሮች ከተጋለጡ ሴቶች መካከል የተወሰኑት በማዕከሉ የተሃድሶና የክህሎት ማበልጸጊያ ስልጠና ወስደው የተወሰነ ድጋፍ ቢደረግላቸውና ለስራ ስምሪት የሚሆን ድጋፍ ቢሰጣቸው ለሌሎች ምሳሌ ይሆናሉ፡፡



የማዕከሉ ግንባታ ባለፈው የካቲት የተጀመረ ሲሆን፣ በአስራ ሶስት ወራት ለማጠናቀቅ እየተሰራ ይገኛል፤

ፎቶ በአ/አበባ ትላልቅ ፕሮጀክቶች ግንባታ ጽህፈት ቤት

በአዲስ አበባ የሚመጣው ለውጥ ለክልል ከተሞችም መነቃቃትን የመፍጠር አቅም እንደሚኖረው ከንቲባዋ ጠቅሰው፣ በመገንባት ላይ ያለው ማዕከል ሴቶች ችግር ሲያጋጥማቸው እና ህይወት ስትጨልምባቸው መግቢያ ቤታቸው እና ማረፊያቸው፣ የጠወለገ ተስፋቸው የሚለመልምበት ስፍራ መሆኑን አስታውቀዋል፡፡ ቀጣይ ህይወታቸው እንዲቀየር እና ወደ ሌሎች ፕሮጀክቶች እንዲሸጋገሩ ታስቦ የሚሰራ ነው ብለዋል፡፡

‹‹አዲስ አበባ የሁሉም ኢትዮጵያዊያን መልካም ቤት እንደመሆኗ፤ በአዲስ አበባ ጎዳና በተለያዩ ችግሮች ምክንያት ለሴተኛ አዳሪነት እና ለሌሎች ማህበራዊ ችግሮች በተጋለጡ ላይ ሊፈረድባቸው ሳይሆን ሊደረስላቸው ይገባል›› ያሉት ከንቲባዋ፤ ለነዚህ ወገኖች የሚደረስላቸው አንዱ መንገድ የተሃድሶ እና የክህሎት ስልጠናዎችን በማቅረብ እንዲሁም እንዲህ አይነት የተሃድሶ እና ስልጠና ማዕከላትን በማስፋፋት መሆኑን አብራርተዋል፡፡

ማዕከላትን ከማስፋፋት ጎን ለጎን ማዕከላቱ የታለመላቸውን ዓላማ እንዲያሳኩ የቅርብ ክትትል ሊደረግባቸው የሚገባ ሲሆን፤ ከዚህ ቀደም ሌሎች ማዕከላት ላይ ሲያጋጥሙ የነበሩ ማዕከላትን ከታለመላቸው ዓላማ ውጪ የማዋል ሁኔታዎች እንዳይኖሩ የቅርብ ክትትል ሊደረግባቸው ይገባል፡፡

እንደ ኢንጂነር ዙሪያወርቅ ማብራሪያ፤ ለማእከሉ ግንባታ ሦስት ነጥብ አንድ ቢሊየን ብር በጀት ተይዞለታል፤ በ50 ሺህ ካሬ ሜትር ቦታ ላይም ያርፋል፤ በውስጡ እያንዳንዳቸው 640 ካሬ ሜትር ላይ የሚያርፉ 12 ህንጻዎችንም ያካትታል፡፡ ከነዚህ ውስጥ አምስቱ ህንጻዎች ጂ+1 (G+1) ናቸው፡፡ ስድስት ህንጻዎች እንደ መኝታ ቤት /ዶርም/ የሚያገለግሉ ሲሆኑ፣ አንድ ህንጻ ደግሞ ለአስተዳደር አገልግሎት የሚውል ነው፡፡ ማዕከሉ በአንድ ጊዜ ከ2000 በላይ ሴቶች ለማሰልጠን የሚያስችል ሲሆን፣ በዓመት እስከ 10ሺህ ሴቶች የተሃድሶ እና የሙያ ስልጠና እንዲያገኙ ያስችላል፡፡

የማዕከሉ ግንባታ የካቲት 30 ቀን 2015 ዓ.ም የተጀመረ ሲሆን፤ ግንባታውን በ13 ወራት ወይም በ395 ቀናት ውስጥ ለማጠናቀቅ ታቅዶ እየተሰራ ነው፡፡ ለሚቀጥለው ዓመት የዓለም አቀፍ የሴቶች ቀን (ማርች 8) ለማጠናቀቅ እቅድ እንደተያዘለት ከጽህፈት ቤቱ የተገኘው መረጃ ያመለክታል።

በማዕከሉ ውስጥ ከሚገነቡ ህንጻዎች ባሻገር ሙሉ 50 ሺህ ካሬው ላይ የተለያዩ የማስዋቢያ ስራዎች የሚሰሩበት ሲሆን፣ ማሰልጠኛ ክፍሎችን የሚያገናኙ የአስፋልት መንገዶችም እንደሚኖሩት ጠቁመዋል። ማዕከሉ ዘመናዊ ቴክኖሎጂዎችም ይኖሩታል፡፡ የራሱ የሆነ የካሜራ ሲስተም፣ የዳታ ማዕከልን ጨምሮ ዘመናዊ ማዕከላት ማሟላት ያለባቸውን መሰረተ ልማቶች ያሟላ እንደሚሆንም ኢንጂነሩ ጠቁመዋል፡፡

እንደ ተወካዩ ማብራሪያ፤ የፕሮጀክቱ የዲዛይን እና የግንባታ ስራዎች በአንድ ወቅት ጎን ለጎን እየተካሄዱ ይገኛሉ፡፡ የመኝታ ቤቶቹ ህንጻ /የማደሪያ ዶርሙ/ ከመሬት በታች የሚሰሩ አብዛኛዎቹ ስራዎች ተሰርተዋል፤ ስልጠና የሚሰጥባቸው ህንጻዎች የዲዛይን ስራዎች እየተሰሩ ነው። የዲዛይን ስራዎቹ እንደተጠናቀቁ የቁፋሮ ስራዎች ይጀመራሉ፡፡

ባለፈው ሰሞን በተከታታይ የጣለው ዝናብ ለቁፋሮ ስራ አመቺ አለመሆኑን ተከትሎ የግንባታ ስራው የተወሰነ መጓተት እንደተፈጠረበት የጠቀሱት ኢንጂነር ዙሪያወርቅ፤ እንዲያም ሆኖ ግን ዝናቡ ሲቆም የቁፋሮ ስራዎች መሰረታቸውንም ገልጸዋል፤ ግንባታውን በተያዘለት ጊዜ ለማጠናቀቅ ርብርብ እንደሚደረግም ጠቁመዋል፡፡

በሜጋ ፕሮጀክቶች የማእከሉ መገንባት አገራዊ ጠቃሜታ ከፍ ያለ መሆኑን ከግንዛቤ በማስገባት የአካባቢው አስተዳደር አካላት በተለይም ክፍለ ከተማው እና ወረዳው ለፕሮጀክቱ ትኩረት ሰጥተው ትብብር እያደረጉ መሆኑን የጠቆሙት ተወካዩ፤ በአሁኑ ወቅት የሚታየው ትብብር እና ቅንጅት ፕሮጀክቱ እስኪጠናቀቅ ድረስ ተጠናክሮ ሊቀጥል የሚገባ ነው ብለዋል፡፡

ፕሮጀክቱ እንደ ሌሎቹ ፕሮጀክቶች ሁሉ በሲሚንቶ ችግር እየተፈተነ መሆኑን የተናገሩት ኢንጂነር ዙሪያወርቅ፤ ችግሩን ለመፍታት በተቻለ መጠን ከሚመለከተው አካል ጋር በመነጋገር እየተሰራ መሆኑንም ነው የገለጹት። ከሲሚንቶ አምራቾች ጋር ደብዳቤ በመጻጻፍ ሲሚንቶ እንዲቀርብ ጥረት እየተደረገ መሆኑንም አስታውቀዋል፡፡

ኢንጂነር ቴዎድሮስ ተበጀ የሳይት መሃንዲስ አማካሪ ናቸው፡፡ እሳቸው እንዳሉት፤ ብሎክ ኤ (A) ወይም የዶርም ህንጻ የቁፋሮ ስራ ተጠናቋል፣ ብሎክ ቢ (B) እና ብሎክ ሲ (C) ላይ ደግሞ የመሰረት ስራዎች እየተሰሩ ናቸው። ብሎክ ዲ (D) እና ብሎክ ኢ (E) ላይም በተመሳሳይ የመሰረት ስራ እየተሰራ ነው፡፡ ማዕከሉ ክሊኒክ ይኖረዋል፤ የክሊኒኩም የመሰረት ስራ እየተሰራ ነው፡፡ የክህሎት ማሰልጠኛ ህንጻዎች አካባቢን ለግንባታ የማዘጋጀት እና የማጽዳት ስራዎች እየተሰሩ ናቸው፡፡

እየጣለ ያለውን ዝናብ ተከትሎ ከታየው መጠነኛ መጓተት ውጪ ፕሮጀክቱ ጥሩ እንቅስቃሴ እየታየበት መሆኑን ያነሱት ኢንጂነር ቴዎድሮስ፤ በተጀመረው መልካም እንቅስቃሴ ማስቀጠል ከተቻለ ፕሮጀክቱ በተያዘለት ጊዜ ውስጥ ሊጠናቀቅ እንደሚችል ተናግረዋል፡፡

ከሜጋ ፕሮጀክቶች ጽህፈት ቤት የተገኘው መረጃ እንደሚያሳየው፤ በፕሮጀክቱ ግንባታ ላይ በርካታ የስራ እድሎች ተፈጥረዋል፡፡ የስራ እድል ከተፈጠረላቸው መካከል ከዚህ በፊት ጎዳና ላይ የነበሩ 260 ወጣቶች ይጠቀሳሉ፡፡ አብዛኞቹ የቀን ሰራተኞች በተለያዩ ችግሮች ምክንያት ጎዳና ላይ ወድቀው የነበሩ ናቸው፡፡ ወጣቶቹ ከጎዳና ህይወት ከመላቀቅ ባሻገር በዘላቂነት የሙያ ባለቤት እንዲሆኑ በትኩረት እየተሰራ ነው፡፡

በፕሮጀክቱ የስራ እድል ከተፈጠረላቸው መካከል አንዱ አቶ አበበ ነጋሽ ናቸው፤ በማዕከሉ ግንባታ በጉልበት ሰራተኛነት እየሰሩ ይገኛሉ፡፡ አቶ አበበ በአፋር ክልል በግብረ ሰናይ ድርጅት ውስጥ ይሰሩ ነበር፡፡ በሰሜን ኢትዮጵያ የተቀሰቀሰውን ጦርነት ተከትሎ ድርጅቱን ሲመሩ የነበሩ ግለሰብ አካባቢውን ለቀው መሄዳቸውን ተከትሎ ድርጅቱ መፍረሱን ይናገራሉ፡፡ ይህን ተከትሎም የአንድ ዓመት ደመወዝ እንዳልተከፈላቸው ይናገራሉ። በመጨረሻም የጎዳናን ህይወት ውስጥ መግባታቸውን ይገልጻሉ፡፡

አቶ አበበ ለአንድ ዓመት በአስቸጋሪ ሁኔታ ኖረዋል፤ በ2014 ወደ አዲስ አበባ መጥተው የመንገድ ጽዳት ስልጠና መውሰዳቸውን የሚናገሩት አቶ አበበ፣ ወዲያው ግን ስራ አላገኙም፡፡ በዚህም ምክንያት አንድ ዓመት ያለ ስራ ካሳለፉ በሁዋላ የማዕከሉ ግንባታ ሲጀመር በቀን ሰራተኝነት ተቀጥረው መስራት እንደጀመሩ ያብራራሉ፡፡ ከሁለት ዓመት አስቸጋሪ ጊዜ በኋላ ወደ ስራ በመመለሳቸው ደስተኛ መሆናቸውን የሚያነሱት አቶ አበበ፣ በማዕከሉ ውስጥ የተለያዩ ሙያዎችን ለመልመድ ጥረት እያደረጉ ናቸው፡፡

አቶ መስፍን ዘበርጋ በማዕከሉ ግንባታ በቀን ሰራተኝነት ተቀጥረው በመስራት ላይ የሚገኙ ሌላኛው የሥራ እድል ተጠቃሚ ናቸው፡፡ አሁን ማዕከሉ እየተገነባ ባለበት ቦታ ሌላ ማዕከል እንደነበር ያስታውሳሉ፡፡ በዚያ ማእከልም ለሁለት ዓመት ገደማ ያለ ምንም ስራ ቆይተዋል፡፡

በመንገድ ጽዳት ስራ ላይ ትሰማራላችሁ ተብሎ ስልጠና ተሰጥቷቸው እንደነበር የሚያስታውሱት አቶ መስፍን፣ እሳቸውም በጽዳት ስራ ላይ ሳይሰማሩ ቆይተዋል። በመጨረሻም በማዕከሉ ግንባታ በቀን ሰራተኝነት ተቀጥረው እንዲሰሩ እድል እንደተፈጠረላቸው ይናገራሉ፡፡

በመንገድ ጽዳት ስራ ለመሰማራት ፍላጎቱ እንደነበራቸው የሚገልጹት አቶ መስፍን፤ ይህ ፍላጎታቸው ግን ሊሳካ እንዳልቻለ ተናግረዋል፡፡ በኮንስትራክሽን ስራው ሲሰማሩ ደስተኛ እንዳልነበሩም ያልነበሩት አቶ መስፍን፣ በሂደት ግን ስራውን እየወደዱት መጥተዋል። በአሁኑ ወቅት የተለያዩ ሙያዎችን ለመልመድ ጥረት እያደረጉ ናቸው፡፡ አናፂ የመሆን ፍላጎታቸው እየጨመረ በመምጣቱ የአናጺነት ልምድ ካላቸው ባለሙያዎች ጋር በቅርበት እየሰሩ መሆናቸውን ገልጸዋል፡፡

# ርዕሰ አንቀፅ

## የህዝባችንን ዘላቂ ሰላምና ደህንነት በአስተማማኝ መልኩ ለመጠበቅ

ከለውጡ ማግስት ጀምሮ ለውጡን ለመቀልበስ፤ ለአገርና ለህዝብ ይዞት የመጣውን ተስፋ ለማክሰም ማቆሚያ የሌላቸው የጥፋት ተልእኮዎች በተቀናጀ መንገድ ታቅደው ሲተገበሩ ቆይተዋል፤ ዛሬም እየተተገበሩ ነው። በዚህም ሕዝባችን አላስፈላጊ የሆኑ ዋጋዎችን ለመክፈል ተገድዷል።

ግልጽ ጦርነትን ያካተቱት እነዚህ የጥፋት ተልእኮዎች፤ በፈጠራ ወሬዎች፣ በተዛቡ መረጃዎችና በተሳሳቱ ትርክቶች አቅም እየገዙ የለውጡ ዋነኛ ኃይል የሆነውን ህዝባችንን ግራ በማጋባትን እና በማደናገር፤ ለውጡ በተነሳበት ፍጥነት እንዳይጓዝ፤ ሂደቱም በብዙ ተግዳሮቶች እንዲፈተን አድርገውታል።

በተለይም ለተወሰነ ህዝብ /ብሄር፣ ብሄረሰብ/ እና ለአገር ተቆርቋሪ ነን የሚሉ ግለሰቦችና ቡድኖች፣ የለውጡን ሂደት ተከትለው በየወቅቱ የሚፈጥሯቸው የጥፋት አጀንዳዎች፣ ሂደቱን ወደኋላ መቀልበስ የሚያስችል አቅም ባይኖራቸውም፣ ለጊዜው ለለውጡ ተግዳሮት መሆናቸው አልቀረም።

እነዚህ ኃይሎች ቀደም ባሉት ጊዜያት ጠንካራ መከላከያ ሰራዊት በጥቅሉም የፌዴራል የጸጥታና የደህንነት ኃይል መፈጠር ሲገባው የክልል ልዩ ኃይል አደረጃጀት መኖሩ ለአገርም ሆነ ለህዝብ ደህንነት አደጋ ስለመሆኑ አብዝተው ሲጮሁ፤ "መበተን " አለበት እያሉ በአደባባይ ሲሞግቱ፤ መንግስት ይህንን ማድረግ ባለመቻሉ ሲኮንኑ፣ ሲከስሱና ሲያብጠለጥሉ እንደነበር የቅርብ ጊዜ ትዝታ ነው።

አሁን ላይ መንግስት በጉዳዩ ዙሪያ በቂ ጥናት አድርጎ እና ከሚመለከታቸው አካላት ጋር መክሮ የክልል ልዩ ኃይሎችን መልሶ በማደራጀት አንድ ጠንካራ የተማከለ ሕብረ ብሄራዊ የመከላከያና የጸጥታ ኃይል ለመገንባት መንቀሳቀስ ሲጀምር፤ የትናንት ጩኸታቸውን ሁሉ ዘንግተው በሌላ ዜማና በተለመደው የሕዝብ ማደናገሪያ ጩኸታቸው ተከስተዋል።

በርግጥ የክልል ልዩ ኃይሎችን መልሶ የማደራጀት ስራው ዋና አላማ የጥፋት ኃይሎች እንደሚሉት፤ ኃይሉን ትጥቅ በማስፈታት ወይም አንድን ብሔር ለይቶ ለማዳከምና ለጥቃት አሳልፎ ለመስጠት አይደለም ።

ከዚህ ይልቅ ልዩ ኃይሉ ትጥቁን ይዞና የተሻለ ዐቅም ተፈጥሮለት በምርጫው መሠረት የክልል ፖሊስን፣ የፌደራል ፖሊስን ወይም የአገር መከላከያ ሠራዊትን እንዲቀላቀል ማድረግ የሚያስችል ነው። በዚህ ሂደት መካተት ያልፈለገም ወደ መደበኛ የሲቪል ሕይወት እንዲገባ በመንግሥት በኩል አስፈላጊ የማቋቋሚያ ሥራዎች እንዲከናወኑ የሚያመቻች ነው።

ይሄም በአንድ ክልል ብቻ ሳይሆን በመላ አገሪቱ በሁሉም ክልሎች በተመሳሳይ ጊዜ የሚካሄድ ነው፤ የልዩ ኃይል አባላቱን ወደ ሌሎች የጸጥታ መዋቅሮች የማስገባት ተግባር በሚፈጸምበት ጊዜም በክልሎች አስተማማኝ ሰላምና ጸጥታን ለማረጋገጥ የአገር መከላከያ ሠራዊት በሁሉም ቦታዎች ሥምሪት ወስዷል።

ሕወሓትን በተመለከተም በደቡብ አፍሪካ ፕሪቶሪያ በተደረሰበት የሰላም ስምምነት መሠረት ትጥቁን ሙሉ በሙሉ እንዲፈታ የሚደረግ መሆኑ በሂደቱ እንደ ስጋት ሊያስቆጥረው የሚችል አይሆንም። ከዚህም በላይ የመከላከያ ሰራዊት በሁሉም ቦታ ሰላምና ጸጥታን ለማስከበር መሰማራቱ ስጋቶችን ለማስወገድ አስተማማኝ አቅም እንደሚሆን ይታመናል።

የመልሶ ማደራጀት ሥራው አሁን ላይ በሁሉም ክልሎች በሰላማዊ መንገድ በጥንቃቄ እየተከናወነ ባለበት ሁኔታ፤ በአማራ ክልል በሚገኙ የተወሰኑ የልዩ ኃይል ክፍሎች ውስጥ አንዳንድ ችግሮች ተስተውለዋል። ችግሮቹ አንድም የመልሶ ማደራጀት ስራን ዓላማ በአግባቡ ካለመረዳት፤ ካልሆነም የጥፋት አጀንዳ አራጋቢዎች ሆን ብለው በሚነዙት የሐሰት ወሬ ከመጠለፍ የመነጨ ሊሆን እንደሚችል ይታመናል።

የሥራውን ዓላማ ካለመረዳት ሆነ በጥፋት ኃይሎች የፈጠራ ወሬ፣ የተዛባ መረጃ እና የተሳሳተ ትርክት ሰለባ የሆኑ እነዚህ የልዩ ኃይል ክፍሎች፤ የክልል ልዩ ኃይሎችን እንደገና የማደራጀት ሥራ አላማና ተልእኮ በአግባቡ ሊረዱት፣ ለተግባራዊነቱም በኃላፊነት መንፈስ ሊንቀሳቀሱ ይገባል።

የኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያውያን ሰላም እና ደህንነት አስተማማኝ ሊሆን የሚችለው የአገሪቱን የመከላከያና የጸጥታ ኃይሎች ሕብረ ብሄራዊ በሆነ ጠንካራ መሰረት ላይ ሲዋቀሩ፤ ጊዜውን ሊዋጅ በሚችል አቅምና ዝግጁነት ሲገነቡ ብቻ ነው። ይህ ደግሞ መንግስት ከለውጡ ማግስት ጀምሮ ተግባራዊ እያደረገው ያለው ትልቁና ዋነኛው የሪፎርም ስራው ነው።

አሁን ላይ ተግባራዊ እየተደረገ ያለው የክልል ልዩ ኃይሎችን እንደገና የማደራጀቱ ሥራም ጠንካራ ህብረ ብሄራዊ የመከላከያና የጸጥታ ተቋማት የመገንባት ሂደት አካል ነው፤ የህዝባችንን ዘላቂ ሰላምና ደህንነት ለማስከበር የሚደረገው አገራዊ ጥረት ስኬት ዋነኛ አቅም ተደርጎ የሚወሰድ፤ ሕዝባችንን ከትናንት እና ከዛሬ የጸጥታ ስጋት በአስተማማኝ ሁኔታ ለመታደግ የሚያስችል ነው። ይህንን በአግባቡ ተገንዝቦ ለተግባራዊነቱ ስኬት መንቀሳቀስ ደግሞ የልዩ ኃይሉ ብቻ ሳይሆን የዜጎች ሁሉ ኃላፊነት ነው።


# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4240
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

ማከፋፈያ :- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# የኢፌዴሪ መንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት በወቅታዊ አገራዊ ጉዳዮች ላይ የሰጠው መግለጫ፤

**የኢፌዴሪ መንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት ትናንት በተለያዩ እና ወቅታዊ አገራዊ ጉዳዮች ላይ መግለጫ ሰጥቷል። መግለጫውን የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት ሚኒስትር ዴኤታ ሰላማዊት ካሳ የሰጡ ሲሆን፤ ትኩረቱም ጠንካራ እና ወጥ የሆነ አንድ አገራዊ የመከላከያ እና ደህንነት ኃይል በመገንባት ሂደትን ጨምሮ በማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ ያደረገ ነበር። የመግለጫው ሙሉ ይዘትም እንደሚከተለው ቀርቧል።**

### የመከላከያ እና የጸጥታው ዘርፍ ሪፎርም ሥራዎች

የሪፎርም ስራዎቻችን የመከላከያ ሠራዊታችንን በመሳሪያ፣ በቴክኖሎጂ፣ በሰው ኃይል እንደዚሁም በተለያዩ አስፈላጊ በሆኑ መንገዶች ሁሉ ማጠናከር ላይ ያተኮሩ ነበሩ። በአጭር ጊዜ ውስጥ በመከላከያ ሠራዊት ላይ የተሰሩት የሪፎርም ስራዎች ደግሞ ምን ያህል ውጤት እንዳስገኙ ባለፉት ጥቂት ዓመታት የተመለከትነው ነው። በተጨባጭም እንደ ሀገር ተደቅኖብን የነበረውን የህልውና አደጋ በዘላቂነት ለመቀልበስ ያስቻለ መሆኑንም ሁሉም የሚገነዘብ ሃቅ ነው።

የኢፌዴሪ መከላከያ ሠራዊት የመጨረሻ ብሄራዊ ኃይላችን ነው። እንደሀገርም የህልውና የመጨረሻ ምሽጋችንም ይህ ብሄራዊ መከላከያ ኃይላችን ነው። እንደ ኢትዮጵያ በብዙ ሀገራዊና ቀጣናዊ ትኩሳቶች ለተከበበ ሀገር ያለጠንካራ መከላከያ ሠራዊት ጠንካራ ሀገርን መገንባት አይቻልም። ይህም እግዲህ ሠራዊቱን የተሟላ ስብዕና በማላበስ ፤ ሙሉ ኢትጵያዊነቱን በማላበስ፤ በሰው ሃይል በመሳርያ፤ በቴክኖሎጂ በሞራልም ጭምር ማጠናከር ዋነኛ ሀገራዊ አጀንዳችን ሆኖ መቆየቱ የሚታወቅ ነው።

ይህንን የሪፎርም ስራ መነሻ በማድረግ መንግሥት የሀገሪቱን ሉዓላዊነት እንዲሁም የግዛት አንድነት መጠበቅ የሚያስችል ጠንካራ መከላከያ ሠራዊት ለመገንባት የሚያስችል ብዙ ጥረቶች ነበሩ። ይህንንም በሰፊ ጥናቶች አስደግፎ ነው ሲከናወን የነበረው። ይህንን ጥናት ተከትሎም መንግሥት ባስቀመጠው አቅጣጫ መሰረት የክልል ልዩ ኃይሎች በተለያዩ መዋቅሮች እንዲደራጁ የሚያስችላቸው ተግባራዊ እርምጃ መጀመሩመ ይታወቃል። ይህ ስራ እንግዲህ ምንም እንኳን በጥናትና በቅድመ ዝግጅት ደረጃ ቆየት ብሎ የተጀመረ እንደሆነ ይታወቃል። እንግዲህ በሀገራችን የህልውና አደጋ ተደቅኖ እደነበር ይታወቃል። ይህንን መቀልበስ አስፈላጊ ነበር። እንዲሁም በሌሎች አካባቢዎች ላይ የነበሩ ሰላም መደፍረሶች ዘላቂ መፍትሄ እስኪያመጡ ድረስ በጥናቱ ላይ የተመለከቱት የመፍትሄ አቅጣጫዎች ተግባራዊ እንዳይሆኑ አድርጎ ቆይቷል።

የመንግሥት ዋነና ኃላፊነት ዜጎችን ደህንነት ማስጠበቅ እና የሀገር ህልውና ማስከበር እንደመሆኑ፤ ሀገራዊ ሰላምን በተሟላ ሁኔታ ማስጠበቅ የተጣለበት መንግሥት፤ ይህንን ኃላፊነቱን እንዲወጣ በተለያዩ ደረጃ ያሉ የማህበረሰብ ክፍል በተለያየ መልኩ ጥያቄ ሲያቀርብ እና መልዕክት ለመንግሥት ሲያስተላልፍ ቆይቷል። ይህንን ለማሳካት ደግሞ በሥነምግባሩ፤ በሰው ኃይሉ፤ ጠንካራ የሆነ እንዲሁም በመሳርያ የተደራጀ አንድ ጠንካራ የተማከለ ሠራዊትን መገንባት አስፈላጊ እንደሆነም በተለያዩ አጋጣሚዎች ሲነሳ ቆይቷል።

አሁን ወደ ተግባር የገባው የክልል ልዩ ኃይሎችን መልሶ የማደራጀት ስራም በሁሉም ክልሎች ውስጥ በተመሳሳይ ወቅት የተጀመረ ነው። በሁሉም ክልሎች በየደረጃው ባሉ በሚመለከታቸው አካላት በጉዳዩ አስፈላጊነት ላይ ከመግባባት ላይ በመደረሱ እንዲሁም አሁን ሀገሪቱ ውስጥ ያለው የተሻለ የሰላም ሁኔታ ከዚህ ቀደሙ በጣም የተሻሻለ በመሆኑ እና ይህንን ትልቅ ተልኮ ለማስፈጸም የሚያስችል መሆኑን ከግምት ውስጥ በማስገባት፤ በሁሉም ክልሎች በየደረጃው ካሉ የሚመለከታቸው አካላት ጋር ጭምር ውይይቶችን በማድረግ ጭምር ነው ስራዎች የተጀመሩት።

በተለያዩ ወቅቶች ከብዙ አቅጣጫ ሲሰነዘሩ የነበሩ ሀገርን አደጋ ላይ የጣሉ ክስተቶችን ለመመለስ፤ እንደዚሁም የሀገርን ክብር ለማስጠበቅ በሁሉም ክልል የሚገኙ ልዩ ኃይሎች በጣም ከፍተኛ አስተዋጽኦ ማበርከታቸው የሚታወቅ ነው። ለዚህ ደግሞ መንግሥት ከፍ ያለ ዕውቅና ሲሰጥ ቆይቷል። ከፍተኛ መስዋዕትነትን በመክፈል ለሀገራቸው ብዙ አስተዋጽኦ ያበረከቱ የልዩ ኃይል አካላት አሉ። አሁን በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች የሚገኙ ልዩ ኃይሎች በመልሶ ማደራጀቱ ስራው ምርጫው ሙሉ በሙሉ ተጠበቆለት ፤ ፍላጎቱም እንዲሁ ተከብሮለት መንግሥት አማራጮችንም አስቀምጦለት ነው ይሄ የመልሶ ማደራጀቱ ስራ የሚከናወነው።

አንዱ፣ በየትኛውም ክልል የሚገኝ ልዩ ኃይል የኢትዮጵያ የህልውና ምሶሶ ወደ ሆነው፤ እንዲሁም ከራሱ አልፎ በአፍሪካ ብሎም በዓለም ጭምር ዕውቅና የተሰጠውን ጀግናው የመከላከያ ሠራዊታችንን መቀላቀል አንደኛው ነው። ይህ ደግሞ እንግዲህ ትልቅ ሀገራዊ ጥሪ መሆኑ ነው። በዚሁ አጋጣሚ አፅዕኖት መስጠት ያስፈልጋል። ሁለተኛው አማራጭ ደግሞ በዚያው ባለበት ክልል ያለውን የሰላምና የፀጥታ ሁኔታ ማስከበር ፤ የክልሉን ነዋሪዎች ጭምር ማገልገል የሚችልበትን እድል የሚሰጠውን የክልሉን የፖሊስ ሃይል መቀላቀል ደግሞ ሌላው ሁለተኛው የቀረበው አማራጭ ነው። በሁሉም ክልሎች ውስጥ ጠንካራ የፀጥታና የወንጀል መከላከል ስራን ለመጀመር የፖሊስ ሃይሎች፤ የፀጥታ መዋቅሩ በከፍተኛ ደረጃ መደራጀትም፤ መጠናከርም ስላለበት እንደዚሁም ብቁ ባለሙያዎችም ስለሚያስፈልጉት ይህንን ሃይል ማጠናከር ደግሞ ትልቅ አስተዋፅኦ የሚኖረው ርምጃ እንደሆነ ሊሰመርበት ይገባል።

ከእነዚህ አማራጮች ውጪ ደግሞ ወደመደበኛ ኑሮ መመለስ የሚፈልግም አካል ካለ ይህም ሙሉ መብቱ ተጠብቆለት የሚከናወን ይሆናል ማለት ነው፤ ሶስተኛው አማራጭ ይህ ነው። ወደ ሲቪል ሕይወት መመለስ የሚፈልግ ኃይልም ካለ የመቋቋሚያ አስፈላጊ ድጋፎችን ለማድረግ በመንግሥት በኩል ዝግጅት ተደርጓል። ይህንንም ለማስፈፀም ከሁሉም ክልሎች ጋር አስፈላጊ የሆነ ምክክሮች ሲደረጉ ቆይተዋል፤ አሁንም እነዚህ ምክክሮች እየተደረጉ ነው የሚገኙት። እነዚህ ሶስት አማራጮች በግልፅ ቀርበዋል። ይህንንም በመላው ሀገሪቱ በሚገኙ ክልሎች ውስጥ በፖለቲካ አመራሩ ዘንድ፣ የመከላከያ እና የፖሊስ አመራሮች እንደዚሁም ደግሞ የልዩ ሃይል አመራሮች እና አባላት መካከል ቀጣይነት ያላቸው ንግግሮች እየተደረጉ ነው የሚገኙት።

ምክንያቱም ይሄ ስራ እንደስፋቱ መጠን፣ እንደዚሁም ደግሞ በሚያካትታቸው አካላት በመግባባትና በመነጋገር ላይ ብቻ ተመስርቶ የሚከናወን መሆኑን በዚህ አጋጣሚ መንግሥት ለማስገንዘብ ይወዳል። ሆኖም በአንዳንድ አካባቢዎች ላይ በመረጃ እጦት እና የመርሃ ግብሩን ዋነኛ ዓላማ በተገቢው መልኩ ካለመገንዘብ የተነሳ አንዳንድ ያጋጠሙ ችግሮች እንደነበሩ ተመልክቷል። እነዚህ ችግሮች ሊፈቱ የሚችሉት ስለ ስራው ዓላማ እና በውስጡ ስለያዛቸው ቁም ነገሮች ትክክለኛ የሆነ መረጃ በመስጠትና መግባባት ላይ በመድረስ ጭምር እንደሆነ መንግሥት ያምናል። ለዚህም ነው በመላ ሀገሪቱ በሁሉም ክልሎች መርሃ ግብሩን አስመልክቶ በተለያዩ አካላት በኩል ውይይቶች እየተካሄዱ የሚገኙት። ምክንያቱም በመግባባት እና በመነጋገር የሚካሄድ ተግባር በመሆኑ ነው።

አንደኛ፣ የክልል ልዩ ሃይልን መልሶ የማደራጀቱ መርሃ ግብር በሁሉም ክልሎች እየተተገበረ የሚገኝ መሆኑን ሁሉም ሰው ሊገነዘበው የሚገባ ሀቅ ነው። በአንዳንድ አካላት እየተነዙ ያሉ መረጃዎች አሉ። እነዚህን መከላከል የሚቻለው ስለጉዳዩ ትክክለኛውን መረጃ በመስጠት ነው። የመርሃ ግብሩ ዓላማ ምን እንደሆነ በማስገንዘብ፤ ከዚህ ባሻገር ደግሞ ከዚህ በፊት ምን ያህል በህብረተሰቡ ጥያቄ እየተነሳበት የነበረ ጉዳይ እንደነበር በማስታወስም፣ ከዚያ በሻገር ደግሞ እንደ ሀገር የኢኮኖሚ ሁኔታችንን እንዲሁም ነባራዊ ሁኔታውንም ከግምት ውስጥ በማስገባት፣ እንደ ሀገር የምንፈልጋትን ትልቅ ኢትዮጵያ ለመመስረት በሚደረገው ጥረት ውስጥ ምን ያህል አስተዋጽኦ ሊያበረክት እንደሚችል ተገቢውን መረጃ በመስጠት ጭምር ነው። እነዚህን በአንዳንዶች የሚሰነዘሩትን የተሳሳቱ መረጃዎች መከላከል የሚቻለው ትክክለኛውን መረጃ ለተገቢው አካል በማድረስ ይሆናል። የክልል ልዩ ሃይልን መልሶ የማደራጀት ሂደት በሁሉም ክልሎች በተመሳሳይ እየተከናወነ መሆኑን በዚሁ አጋጣሚ ማንሳት ያስፈልጋል። ሂደቱን አስመልክቶ

ወደ 9ኛው ገጽ ዞሯል

ማህበራዊ

# እንዲህም ይኖራል

**ሕይወት ፈርጀ ብዙ ገጽታዎች አሏት፤ መውጣት እንዳለ ሁሉ መውረድም ይኖራል። ከመውረድ ውስጥም በትጋት መውጣት ይቻላል። አግኝቶ ማጣት እንዳለ ሁሉ አጥቶም ይገኛል። ይህ የሕይወት እውነታ ነው፤ በጥቂቶች የህይወት መውጣትና መውረዶች ውስጥ ብዙዎች ይማራሉ። የህይወትን ፈተናዎችም ያውቃሉ። በከፍታ ውስጥ የሚገኙት ‹‹እንዲህም ይኖራል እንዴ?›› ብለው ራሳቸውን ይጠይቃሉ። ለተቸገሩት ያዝናሉ፤ ካሳቸው ቀንሰው የሌሎችን ችግር ይካፈላሉ፤ በተጨማሪም ችግር ብልሃትን ያስተምራል እንዲሉ ከችግር ጋር ተላምዶ ከመኖር ይልቅ ለመፍትሄ የሚታትሩትንም ያበረታታሉ። በመሆኑም ‹‹እንዲህም ይኖራል›› ብለን በከፈትነው አምዳችን ህይወትን በየፈርጁ ታስተውሉበት፤ ^አስተውሳችሁም ትማሩበት ዘንድ ጋበዝናችሁ። ለአስተያየቶቻችሁ፤ ለመሰል ታሪኮች ጥቆማችሁ እንዲሁም ለድጋፋችሁ የዝግጅት ክፍላችን አድራሻ ትጠቀሙ ዘንድ ጋበዝናችሁ።**

## በቀና ልብ - በመልካም እጆች ስር

መልካምሥራ አፈወርቅ



ልጅነቷን በተወለደችበት ስፍራ አልገፋችም። እናቷን በህጻንነቷ ማጣቷ ተነግሯታል። ነፍስ እያወቀች፣ ዕድሜ ስትጨምር የአንድ እግሯን ችግር አወቀች። አንድ እግሯ እንደሌሎች አይደለም። እንዳሻት አይሆንላትም፣ በወጉ አይራመድም። ልጅ ብትሆንም የእግሯን ከሁሉም መለየት አውቃለች። ዝም አላለችም። በኮለተፈው አንደበቷ ምክንያቱን ጠየቀች። ለምን? እንዴት? አለች። ቤተሰቦቿ የእግሯን ጉዳት ሰበብ ነቅሰው እውነቱን ነገሯት።

### አጋጣሚው

ህጻን ነበረች። በወጉ ማትናገር፣ ፈጥና የማትሮጥ ጨቅላ። ገና በጠዋቱ ሞት በእናቷ ጨክኗል። ጡት አስጥሎ ከእሷ ነጥቆታል። ልጅ የእናት ፍቅሯን፣ ጠረን ሽታዋን አታውቅም። የዛኔ ስለእሷ ግድ የሚላቸው አባትና ወንድሞቿ ነበሩ። ስታለቅስ አባብለው ዕንቅልፍ ሲጥላት ከጠፍር አልጋው ያስተኟዋታል።

### እናት ስምን ትሙት

አንድ ቀን ትንሽዋ ልጅ ዕንቅልፍ ይዟት ሄደ። አዝላ ‹‹እሹሹ›› የምትል፣ ሲርባት ጡት የምታጎርስ፣ ተኝታ ስትነቃ አቅፋ የምትስም እናት የለችም። የተኛችው ከተለመደው የጠፍር አልጋ ነበር። ተኝታ ትወራጫለች፣ ትፈራገጣለች። ቤተሰቦቿ እሷን ትተው ከጉዳያቸው ውለዋል። የህጻኗ አንድ እግር ከጠፍር አልጋው ቀዳዳ ገብቶ ተቀርቅሯል። ልብ ያላት፣ያስተዋላት የለም።

ቆይታ ከዕንቅልፏ ነቃች። ቤተሰቦቿ እንደወትሮው ታቅፈው ካልጋው ላይ አነሷት። እግሯ እንደነበረው አልቆየም። እንዳሻት መንቀሳስ፣ መላወስ አቃታት። እግሯ ከጠፍሩ አልጋ ተቀርቅሮ መቆየቱ ለጉዳት ዳርጓታል። በሁኔታው የደነገጡ ዕለቱን ብዙ ሞከሩ። የጨቅላዋ ለስላሳ አካል አልተገራም። እግሯ ደንዝዞ መታዘዝ ፣ መላወስ አቁሟል።

ስፍራው ገጠር የሚባል ነው። በወቅቱ ቤተሰቦቿ ከህክምና አላደረሷትም። በአካባቢው ከሚገኝ ጸበል አመላልሰው አስጠመቋት። ለውጥ አልተገኘም። ከወዳጅ ዘመድ ተማክረው ከአዋቂ ቤት ወሰዷት። ከድካም በቀር መፍትሄ አልነበረም ። የትንሽዋ ልጅ ትንሽዬ እግር ከነህመሙ ዘለቀ።

የአድና አለባቸው ውልደት ዳንሻ ከተባለ ስፍራ ነው። በዕድሜ ከፍ ማለት ስትጀምር ጉዳቷ ለይቶ ታወቀ። የቀኝ እግሯ ከግራው እኩል አይራመድም። ከተለመደው አቋም ለይቶ ወደላይ ተሸማቋል፣ እሷን በእኩል ሆኖ አይከተላትም። ሁሌም የአድና ወንድሞች ከትምህርት ውለው ይመለሳሉ። እሷ ወደፊቷ አይታወቅም እንደነሱ ለዚህ ዕድል አትበቃ ይሆናል። ትንሽዋ አድና ከልጅነቷ ጥቂት ጊዜያትን ቆንጥራ በዳንሻ አሳለፈች።

### ከቀናት በአንዱ

አንድ ቀን የአድና አባት ወደ አዲስ አበባ ጉዞ ጀመሩ። ብቻቸውን አይደሉም። ትንሽዋ አድና ከጎናቸው አለች። የመንገዳቸው ምክንያት እሷን ለእህታቸው ሰጥቶ ለመመለስ ነው። አዲስ አበባ ከዳንሻ ይለያል። ከተማው ከገጠሩ ይበልጣል፣ የነዋሪው፣ ሕይወትና ኑሮው ካሉበት ዓለም አይመስለልም።

በተለይ ለአድና የዳንሻ ሕይወት ይከብዳል። አባት ልጃቸውን ለአክስቷ ሲሰጡ የወላጅ ልባቸው ባብቷል። አሁን ለእሷ ማንነት የሚሻለው አዲስ አበባ ሆኗል። ይህን ያመኑት ሰው እጇን በእጃቸው ይዘው ከአዲሱ ቤት አደርሷት። ከአክስቷ፣ ከእህታቸው ጎጆ።

### የእናት ምትክ

አክስት ትንሽዋን አድና በሙሉ ዓይን ቃኟት። በስስት ተቀብለው፣ በፍቅር አቅፈው ‹‹ልጄ›› ሲሉ ሳሟት። አባት ባስተዋሉት እውነት ደስ አላቸው። በአክስቷ ውስጥ የልጃቸውን የነገ ተስፋ አሻግረው እያዩ ፈጣሪን አመሰገኑ። ለቀናት በእንግድነት ዘልቀውም ወደ አገራቸው ገቡ። አድና አክስቷን እንደ እናት ተቀበለች። ጠዋት ማታ የምታየው ፈገግታ ተስፋዋን አለመለመ። ድካም ህመሟ ቀለላት። ቤቱን ቤተሰቡን ወደደች። ሕይወትን በአዲስ መልክ ልትኖረው ፈቅዳ ከራሷ ተስማማች።

### አዲስ ሕይወት

አሁን አድና የአዲስ አበባ ልጅ ነች። ከዚህ በኋላ ገጠር ይሉት ሕይወት የላትም። በዚህ ስፍራ ሁሉም መልካም እንደሆነ አውቃለች። ልበ ቀናዋ አክስት ከአንድ ልጃቸው አይለይዋትም። የሙት አደራን ተቀብለው ትርጉም ያለው ሕይወት ሊሰጧት ተዘጋጅተዋል።

አክስቷ እንደ እኩዮቿ ከመሆን አላገዷትም። ዕድሜዋ ሲደርስ ትምህርት ቤት አስገቧት። አገር ቤት ሳለች ሳትወድ በግድ ልታጣ የነበረውን ዕውቀት ማግኘቷ ተስፋዋን አበራው። ሳትሰለች ከሌሎች እኩል ለትምህርቷ ታገለች። የትምህርት ቤት ውሎዋ ፈታኝና አጓጊ ሆኖ ቀጠለ። በልጅነቷ ሀ ብላ በጀመረችው ትምህርት መሰረት ጣለች። ከቤት ስትደርስ የእናቷ ምትክ አክስቷ በፈገግታ ይቀበሏታል። በውሎዋ የሸመተችውን እውቀት በጥናት እንድትደግፍ ጊዜ አይነፍጓትም።

አድና ከአንደኛ ክፍል ትምህርቷ አንስቶ የአክስቷ ድጋፍ አልራቃትም። ከቤት ያለችው ትልቋ ልጅ እህትነቷን ተቀብላለች። ሁሌም ስለእሷ ብቻ የሚባል አድሎ የለም። በእነሱ ቤት ሕይወት አንድ አይነት ነው። ልጅነት የእኩል ነው። በአንድ በልተው፣ በእኩል ሰርተው፣ ኑሮን በእኩል ይጋራሉ። አድና አካል ጉዳተኛ ስለሆነች፣ የምታጣው፣ የማትሰራው አይኖርም። ሌሎችም ቢሆኑ እንዲሁ። ከቤት ሰራተኛ እኩል የመስራት፣ ቢያሻት ደግሞ የመተው መብት ከእሷው ነው።

### ትምህርት በፈተና

አድና ትምህርት ቤት ገብታ መማር ይዛለች። ከቤት አስከ ትምህርት ቤቷ ለመድረስ በእግሯ እየተጓዘች ነው። ከቀኑ ይልቅ የማታውን ትምህርት መርጣለች። ይህ መሆኑ ጥሩ ዓላማ ላላት ታዳጊ አልከበደም። እሷ ካለችበት የትምህርት ቀዬ ሰፊ የዕወቀት ገበታ እንዳለ ታውቃለች። ሁሌም በመንገዷ ድካም አትሸነፍም። ደስ እያላት ተምራ በፈገግታ ትገባለች።

አድና በዕድሜ ከፍታዋ የትምህርት ደረጃዋም አደገ። ይህ አጋጣሚ ግን ለምትወደው ትምህርት ፈተና መጋረጡ አልቀረም። ትምህርት ቤቱ ለእሷ መሰል ጉዳተኞች ታሳቢ አልሆነም። ለመማር፣ ዕውቀት ለመገብየት ከፍ ያለን ደረጃ መውጣትና መውረዱ የግድ ይላል። እኩዮቿ ሁሌም ይህን ማድረግ ከብዷቸው አያውቅም። ለእነሱ ደረጃ ማለት የሩጫ፣ የመፈንጫ ገጠመኝ ነው።

ባልንጀሮቿ ከደረጃው ቆመው የስሩን ያያሉ፣ ከስሩም ሆነው የላዩን ይቃኛሉ። ሲላቸው ፈጥነው፣ አልያም ተራምደው፣ ይወጡታል። አንዳንዴ ብረቱን ተደግፈው ይዝናኑበታል። ለአድና ይህ ሁሉ እውነት ከዓይኗ አልፎ አያውቅም። ለእሷ እንደመሰሎቿ በደረጃው መፍጠንና መሮጥ ቀልድ ይሆናል። ደረጃውን በወጉ አልፋው ለመውጣት የየዕለት ችግሯ ነው።

በየቀኑ ረጃጅም ደረጃዎችን በጭንቅ ማለፍ የማትወጣው ፈተና ሆኗል። ይህ ደረጃ በምትማርበት አራተኛ ፎቅ በየቀኑ በመሰናከል ደግፎ ያደርሳታል። ተመልሳ ስትወርድም የሚቀርላት የለም። ለእሷ ማር ለመቁረጥ ከንብ እንደሚታገል ሰው መሆኑ ግድ ይላታል። በየቀኑ በድጋፍ ክራንች ተደግፋ ሽቅብ መውጣት፣ ቁልቁል መውረድ መንገዷን የፍራቻና የስጋት አድርጎታል።

አድና ትምህርቷን በእጅጉ ወዳለች። በተለየ ፍቅር የምትደክምለት ዕውቀት አንድ ቀን እንደሚበጃት አልጠፋትም። አንዳንዴ ደረጃውን ወጥቶ ለመመለስ በእጅጉ ይደክማታል። እንዲህ ሲሆን የሚመለከታቸውን ‹‹እርዱኝ፣ተረዱኝ›› ስትል ትጠይቃለች። ምናልባት ከአራተኛ ወደ አንደኛ ፎቅ ቢቀይሩኝ ብላ።

ለአድና የሁሉም አተያይ አንድ አይደለም። አንዳንዱ እንደሆነች ሆና መማር ግዴታዋ መሆኑን ይነግሯታል። ሌላው በግዴለሽነት ሰምቶ ይተዋታል። ይህ ሁሉ እውነት የአድናን ልብ አልሰበረም። ጨለማውን ታግላ መንገዱን አቋርጣ የምትመጣለት የትምህርት ፍቅር በምክንያት መሆኑን ጠቆማት እንጂ።

አድና ትምህርቷን ከፈተናዎች እየታገለች ያዘችው። እንዳሰበችው አልሆነላትም። ድካሟ አየለ፣ ውጥረቷ በረታ። እንዲያም ሆኖ የምትወደውን ትምህርት አልተወችም። ያላትን መረጃ ይዛ የርቀት ትምህርት ቀጠለች።

### እንደገና

ትምህርትና አድና መልሰው በሌላ መንገድ ተገናኙ። ከጨለማ ለመውጣት በጨለማ የጀመረችውን ዕውቀት እጁን ይዛ ተጓዘች። ፈጽሞ አልከሰረችም። የዓመቱ ውጤት መልካም ሆኖ ለቀጣዩ ክፍል አዘጋጃት። ሀሳቧ አምና ወደነበረችበት ትምህርት ቤት አቀና። ዘንድሮን ተመልሳ ዕድሉን ልትጠቀም ፈለገች። ያሰበችው አልቀረም። ተመልሳ የሚመለከታቸውን አዋየች። መልካም ሰው ገጠማት። የማታ ትምህርቷን ባመቻት ክፍል መማር እንደምትችል ተነገራት።

አድና የምትወደውን ትምህርት እስከ ስምንተኛ ክፍል ገፋችበት። ከዚህ በኋላ ጉዞዋን የመቀጠል ዕድል አልገጠማትም። ትምህርቷን ትታ በሌላ አማራጭ ተጓዘች። አክስቷ አዲስ ዕቅዷን አጸደቁ። ሀሳቧን አክብረው በይሁንታ ደገፏት። እሷም በውሳኔዋ ገፋች። ራሷን ለአዲስ ሕይወት አዘጋጅታ ማንነቷን አበረታች።

ዛሬ አድና ጥሩ ወጣት ሆናለች። ዕድሜዋ ከፉ ደጉን ያሳያታል። አሁን ጣፋጭ፣ መራራውን አውቃለች። የሚጠቅማትን ከሚጎዳት ለይታለች። ይህ ዕድሜ ከትምህርት ይልቅ ራስን መቻል እንደሚበጅ እየነገራት ነው ። ውስጧን ማዳመጥ የጀመረችው አድና ያገኘችውን ስራ ማለፍ አልፈለገችም። አጋጣሚውን ተጠቅማ ውላ መግባቱን አምናለች።

### የእንጀራ ነገር

አድና ዛሬ ባለስራ ወጣት ነች። እንደእሷ አካል ጉዳት ካለባቸው ወገኖች ጋር ተደራጅታ የቆዳ ውጤቶችን እያመረተች ነው። አሁን ‹‹ክፍል ቀይሩኝ፣ እርዱኝ፣ ተረዱኝ›› የሚባል ተማጽኖ የለም። ያም ሆኖ ለስራ የምትመላለስበት መንገድ ምቹ አልሆነም። ታክሲ ለመሳፈር፣ ከአውቶቡስ ለመውጣት በየዕለቱ ትፈተናለች። እሷ ውጣውረድ ብርቋ አይደለም። ያለፈችበት የትምህርት ዓለም ትምህርት ሆኗት አልፏል።

ደምዝተኛዋ አድና በሰዓቱ ስራ ለመድረስ ማልዳ ትወጣለች። አንዳንዴ በለስ አይቀናትም። ፈጥና መውጣቷ ብቻውን መፍትሄ አይሆናትም። እንደማንም ታክሲ ለመሳፈር መንገዱ ቀና አይደለም። አንዳንዴ አንዳንድ የታክሲ ረዳቶች ወንበር ይዛ እንዳትጓዝ ከበር ይመልሷታል። ለምን ማለት አትችልም። አስቀድመው ‹‹ለአንቺ አይመችም›› ይሉትን ምላሽ ተክነዋል።

አድና ታክሲ ለመጠበቅ ሁሌም ክራንች ተደግፋ መቆም ግድ ይላታል። ያዘኑ፣ ስለእሷ የተጨነቁ ቅድሚያውን ይሰጧታል። የቸኮሉና ግድ የሌላቸው ደግሞ ሲላቸው፣ ቀድመው ሲመቻቸው ገፍተዋት ያልፋሉ። አድና በትራንስፖርት ግልጋሎት ለሸገር አውቶቡሶች ክብርና ምስጋና አላት። እነሱ ቅድሚያውን ሰጥተው፣ አመቺነትን ፈጥረው ያስተናግዷታል።

አንድ ቀን አድና ያላሰበችው ሆነ። በዕለቱ ወደቤት ለመግባት ትራንስፖርት እየጠበቀች ነበር። አጋጣሚ የሸገር አውቶቡስ ከፊቷ ደርሶ ቆመ። የአድና የሰለቸ ፊት በእፎይታ ፈካ። ወዲያው ሁለቱን ክራንቾች አንስታ በጥበቃ የዛሉ እግሮቿን አላወሰች። ወደ አውቶቡሱ መጠጋቷን ያየው ሾፌር እንደተለመደው የመግቢያ በሩን ዝቅ አድርጎ ወደውስጥ እንድትገባ ረዳት።

አድና በእርጋታ ወደበሩ ተጠግታ ወደ ውስጥ ማለፍ ያዘች። ወዲያው ለእሷ በተከፈተው በር መቅደም የፈለገች አንዲት ሴት ከኋላዋ ደርሳ ገፍትራ ጣለቻት። የሚደግፉት አጋዥ ክራንች ከእጇ ተፈናጥሮ ወደቀ። ሁኔታው አስደንጋጭና ድንገቴ ነበር።

### «እችላለሁ…»

አድና በስራና በቤተሰብ ሕይወቷ ደስተኛ ነች። ለእሷ ባይሆኑም በእጆቿ የሚመረቱ ጫማዎችን ለሚፈልጉ ተጠቃሚዎች ስታደርስ ትረካለች። ይህ ደስታ ደግሞ በሌሎች ተጋብቶ ብታየው ፍላጎቷ ነው። አንዳንዴ ግን ነገሮች ሁሉ በተቃራኒ ይሆናሉ። የእጇን ጥበብ የሚያዩ፣ በሁኔታው የሚገረሙ አንዳንዶች ከአድናቆት ይልቅ አለመቻሏን ሊነግሯት ይፈጥናሉ። ጫማዎቹን በእጃቸው ይዘው እሷ እንዳልሰራችው ደፍረው ይሞግቷታል። አድና ግን በንግግራቸው ታፍራለች እንጂ ፈጽሞ አታዝንም። ሁሌም ከከንቱ ሀሳባቸው ጀርባ ‹‹እችላለሁ›› የሚለውን እውነት በተግባር ታሳያቸዋለች።

አድና ከደጓ አክስቷ መዳፍ ማረፏ የቀን ውሎዋን እንድትረሳ የአካል ጉዳቷን እንዳታስብ ሰበብ ሆኗል። ቤት የሚቆያት ደማቅ ፈገግታ የሚያቅፏት መልካም እጆች ሕይወቷ ቀላል እንዲሆን፣ ነገን በተስፋ እንዳታደር አድርጓል። ይህ እውነት ብዙዎች ዘንድ የማይኖር ሀቅ ነው።

### እንዲህም ይኖራል

አድና ስለ አክስቷ ቅንነት ስታስብ የነገው ሕይወቷ ጭምር መልካም ሆኖ ይታያታል። አክስቷ ከእናት በላይ ማንነቷን ገንብተዋል። አይምሮዋን አንፀዋል። ከአንድ ልጃቸው እኩል የልጅነት ማዕረግ ሰጥተው ‹‹ልጄ›› ሲሉ እናት ሆናዋል። አድና ስለዚህች ሴት ያላት ክብር ቃላት ገልጾት፣ ንግግር ተሸክሞት አያውቅም።

እሷን መሰል አካል ጉዳተኞች በማንነታቸው ያለባቸውን ጫና አሳምራ ታውቃለች። ቤት ተከራይተው፣ ሩቅ መንገድ አልፈው፣ በቤተሰብ ተጽዕኖ አንገት ደፍተው የሚኖሩትን ታውቃለች ። እሷ ግን ለአንድም ቀን ይህ አይነቱ ስሜት ውስጧ ዘልቆ አላደረም።

አድና ሁሌም ከ‹‹እችላለሁ›› ጀርባ ‹‹አያቅተኝም›› ይሉት ስሜት አብሯት አለ። ይህ ጥንካሬ በውስጧ እንዲኖር ያደረጉ ቤተሰቦቿ ነገ የተሻለ እንዲሆን ከጎኗ ናቸው። አድና ማለት በቤት ውስጥ ከሁሉም እኩል ነች። ስራ የምትታዘዘው፣ እንግዳ የምትቀበለው፣ እንደ አቅሟ እየተባለች አይደለም። ሌሎች የሚሰሩትን ሁሉ ታደርጋለች ። የምታደርገው ከሌሎች አያንስም። እንደ ሴት ልጅ ሙያውን፣ ቤት አያያዙን፣ የማወቅ ግዴታና ውዴታው ተጥሎባታል። ይህ መሆኑ ደስታዋን ጨምሯል። ተስፋዋን አብርቷል።

### ስለነገ

አድና ዛሬ ላይ ቆማ ስለነገ ብዙ ታልማለች። አሁን ባለችበት ሙያ በተሻለ መንገድ ብታድግ፣ ብትለወጥ ምኞቷ ነው። ህብረተሰቡ አካል ጉዳተኞች ‹‹አይችሉም›› ከሚለው ስሜት ተላቆ ጥንካሬቸውን እንዲያደንቅ የሚያስችል እውነት ቢፈጠር ትሻለች። ለዚህ ደግሞ እሷን መሰል ወገኖች ከልመና ይልቅ በስራ አምነው፣ በዓይምሯቸው ጥበብ እንዲኖሩ፣ ሰርተው እንዲለወጡ ትመክራለች።

ከምንም በላይ ግን አድና ነገን በትዳር ዓለም ጎጆ ቀልሳ፣ ልጆች ወልዳ ብትኖር ምኞቷ ነው። ለዚህ ሀሳቧ ከፍላጎትና ምኞት በላይ የሁልጊዜው የ‹‹እችላለሁ›› ጥንካሬዋ ከእሷ ጋር ነው። አድና በመልካም እጆች ውስጥ አድጋ፣ በፍቅር ዓለም የምትኖር፣ ነገን በበጎ የምታልም ጠንካራ ወጣት ነች። ይህ ለአብዛኞቹ አካል ጉዳተኞች የማይቸር ዕድል በተቃራኒው የእሷን ሕይወት አቅንቶ ‹‹እንዲህም ይኖራል›› ያስብል ዘንድ ግድ ብሏል።

ኢኮኖሚ

# ስኬት

# “ነውር ነው”ን ወደ ስኬት የቀየረ የባልትና ዝግጅትና ንግድ

**ፍሬሕይወት አወቀ**

ዘመናዊ የአኗኗር ዘይቤን በመከተል ሂደት ውስጥ ኑሮን ቀለል ማድረግ የሚያስችሉ አሰራሮች ያስፈልጋሉ። ለእዚህ ደግሞ ጊዜ ወስደን የምናገኛቸውን ወይም የምናዘጋጃቸውን ማናቸውንም ነገሮች በቀላሉ ማግኘት እንፈልጋለን። ዘመናዊ አኗኗር አዳዲስ የአሰራር መንገዶችን ከማምጣቱ በተጨማሪ፣ ቀደም ሲል ማህበረሰቡ እንደ ነውር የሚቆጥራቸውን በርካታ አሰራሮች ወደ ስራ አስገብቷቸዋል፡፡ ዛሬ ላይ ዘመናዊነት ባመጣው ውጤት ነውር ይባሉ የነበሩ አሰራሮች ነውርነታቸው አክትሞ አዋጭ መሆን ችለዋል፡፡

ማህበረሰቡ ነውር አድርጎ ካቆያቸው በርካታ ጉዳዮች መካከል ሽሮ፣ በርበሬ፣ እንጀራ ወዘተ... ከገበያ ገዝቶ መጠቀም አንዱ ነበር፡፡ በዚህም ምክንያት ለበርካታ ዓመታት እንጀራን ጨምሮ የባልትና ውጤቶችን በማጀት ማዘጋጀት እንጂ ከገበያ መግዛት እንደነውር ሲታይ መኖሩ ይታወሳል፡፡ በተለይም ሴቶች እንጀራና ሽሮ በርበሬ የሚገዙ ከሆነ ደግሞ ከነውርም በላይ ነውር ሆኖ ይታይ ነበር፡፡

ይህ ሁኔታ ከተቀየረ ዓመታት ተቆጥረዋል። እንጀራም ይሁን ሌሎች ማንኛቸውም የበሰሉና የተዘጋጁ ምግቦችን ከገበያ ገዝቶ መጠቀም፣ እነዚህን ምግቦች በቤት ውስጥ ለማዘጋጀት የሚውሰደውን ጊዜና ድካም ይቀንሳል፤ ምግቦቹን ለማዘጋጀት በቂ ቦታ እና ቁሳቁስ ለማይኖራቸው ደግሞ ገዝቶ መጠቀሙ ፋይዳው ከፍተኛ ነው፡፡ ምግቦቹን ለማዘጋጀት የሚያስፈልገው እውቀትና ክህሎት ለሌላቸውና እጥረቱ ላለባቸው ደግሞ ሌላው የተዘጋጁ ምግቦች ፋይዳ ነው፡፡

የዛሬው የስኬት ገጻችንም የባልትና ውጤት ምርቶችን ወደ ገበያ ይዞ በመውጣት ፈር ቀዳጅ የሆነ አንድ ቤተሰብን ሊያስተዋውቃችሁ ይወዳል፡፡ ይህ ቤተሰብ ሽሮ በርበሬ መግዛት ነውር በሆነበት ወቅት የባልትና ውጤቶችን ወደ ገበያ ይዞ በመውጣት ቀዳሚው ነው፡፡ ይህ ቤተሰብ የባልትና ውጤቶችን በቤት ውስጥ አዘጋጅቶ ገበያውን ለማግኘት በብዙ ችግር ውስጥ አልፏል፡፡ ሊገዛ የመጣውም ቢሆን ምርቱ እንዳይታይ በጥቁር ፌስታል፣ በጋዜጣና በሌላ መሸፈኛ እንዲጠቀለልለት ይወተውት እንደነበርም የባልትና ውጤት አዘጋጆቹ ያስታውሳሉ፡፡

ዛሬ ግን ያ ሁሉ አልፎ ድካማቸው ፍሬያማ መሆን ችሏል፡፡ የትኛውም ሰው የባልትና ውጤቶችን ያለሀፍረት በኩራት የሚገዛበት ወቅት ላይ ተደርሷል። ትናንት በቤት ውስጥ ለሁለት የተጀመረው የባልትና ውጤት የማዘጋጀት ሥራ ዛሬ ሙሉ ቤተሰቡን ማሳተፍ ተችሏል፡፡ በወቅቱ በአካባቢያቸው መስፋት ያልቻለው ገበያም ዛሬ ላይ ከአገር ውስጥ አልፎ በተለያዩ ውጭ አገራት በተለይም በአውሮፓ በስፋት ተደራሽ በመሆን ለሀገር ኢኮኖሚም የውጭ ምንዛሬ በማስገኘት አስተዋጽኦ እያበረከተ ይገኛል፡፡

ለዚህ ነው የዕለቱ የስኬት ገጻችን በተለያዩ መጠሪያዎች ከምናውቃቸው ቅመማ ቅመምና የባልትና ውጤት አምራች ላኪዎች መካከል አንዱ የሆነውን “ፋሲካ ቅመማ ቅመምና የባልትና ውጤት አምራች ድርጅትን” የስኬት ጉዞ ሊያስቃኛችሁ የወደደው፡፡

ድርጅቱ ጅማሮውን ያደረገው በ1980 ዓ.ም እንደሆነ የፋሲካ ቅመማ ቅመምና ባልትና ሥራ አስኪያጅ ወይዘሮ ኤልሳ ሃብቴ ትናገራለች። እሷ እንዳለችው፤ በወቅቱ ኢትዮጵያን ሴቶች የባልትና ውጤት ምርቶችን በባህላዊ መንገድ በቤት ውስጥ እንደሚያዘጋጁ ሁሉ ወላጅ እናቷ ወይዘሮ ወለተኪዳን ገብረመድህን ከወላጅ አባቷ አቶ ሃብቴ ገብረማርያም ጋር ሥራውን በቤት ውስጥ ጀመሩት። ጥንዶቹ በባህላዊ መንገድ የጀመሩትን የባልትና ሥራ በአሁኑ ወቅት ልጆቻቸው ተረክበው ዘመናዊ በሆነ መንገድ ማስቀጠል ችለዋል፡፡

ሥራውን ከቤተሰብ ተረክቦ ዘመናዊ በሆነ መንገድ በማስቀጠል ሂደት ኤልሳ የቤቱ የመጀመሪያ ልጅ እንደመሆኗ ከልጅነት እስከ ዕውቀት ቤተሰቦቿን በማገዝ ሙያውን ቀስማለች፡፡ ለዚህም ነው ቅመማ ቅመምና የባልትና ውጤት የሆኑ ምርቶችን ዘመናዊ በሆነ መንገድ ማዘጋጀት ብዙም ያልከበዳት። ለሥራው ቅርብ እንደመሆኗ ትምህርቷን ከ12ኛ ክፍል ገታ አድርጋ ቤተሰቦቿ የጀመሩትን የባልትና ሥራ የተቀላቀለችው ኤልሳ፤ አሁን ላይ ወንድሞቿን ጨምራ ሥራውን ማስፋት ችላለች፡፡ ገበያውም ቢሆን ከአገር ውስጥ ባለፈ ለውጭ ገበያ መድረስ ችሏል፡፡



ፎቶ ፀሐይ ንጉሴ

ወይዘሮ ኤልሳ ሃብቴ

በወቅቱ በቤት ውስጥ የተዘጋጀው ሽሮና በርበሬ ወፍጮ ቤት ወስዶ በማስፈጨት፤ በነጭ ላስቲክ በሻማ እንባ ታሽጎ ለገበያ ይቀርብ እንደነበር ያስታወሰችው ኤልሳ፤ ያን ጊዜ ታዲያ ሽሮ፣ በርበሬና ሌሎች ምርቶችን መግዛት እንደ ነውር ይቆጠር እንደነበር ትናገራለች። በወቅቱ ሥራውን የጀመሩት ወላጆቿ ቴክኖሎጂውና ዕውቀቱ ባይኖራቸውም ከአገር ውስጥ ገበያ በተጨማሪ ኤክስፖርትን ታሳቢ አድርገው ወደ ሥራው እንደገቡ ነው ያስረዳችው፡፡

የወላጆቻቸውን ውጥን ለማሳካት ያለሙት ልጆች ፋሲካ ቅመማ ቅመምና ባልትና የሚለውን ድርጅት በማቋቋም ኤክስፖርቱን በቀላሉ ተቀላቅለዋል፡፡ በአሁኑ ወቅትም ድርጅቱ የተለያዩ ቅመማ ቅመሞችን እና የባልትና ውጤት የሆኑ ምርቶችን ዘመናዊ በሆነ መንገድ አዘጋጅቶ ለአገር ውስጥና ለውጭ ገበያ ተደራሽ እያደረገ ይገኛል፡፡ የፋሲካ ቅመማ ቅመምና ባልትና ምርቶች 70 በመቶ ያህሉ ወደ ውጭ ገበያ የሚላኩ ሲሆን 30 በመቶ ያህሉ ብቻ ለአገር ውስጥ ገበያ ይቀርባል፡፡

እናትና አባት ሁለት ሆነው በልጆች አጋዥነት የጀመሩት ሥራ ተስፋፍቶ በአሁኑ ወቅት 60 ለሚደርሱ ዜጎች በቋሚነት፤ እንዲሁም ከ100 እስከ 150 ለሚደርሱ ሠራተኞች ደግሞ ጊዜያዊ የሥራ ዕድል መፍጠር ችሏል፡፡

ከዛሬ 35 ዓመት በፊት ወደ ባልትና ሥራ በመግባት ለዘርፉ ፈር ቀዳጅ መሆን የቻለው ፋሲካ ቅመማ ቅመምና ባልትና አሁን ኤክስፖርት ላይ ትኩረት አድርጎ የሚሠራ ድርጅት ነው፡፡ ሳሪስ አካባቢ በቤት ውስጥ የተጀመረው የባልትና ሥራ ወደ ፋብሪካ አድጓል፤ በተጨማሪም ቃሊቲና ጀሞ ላይ ተጨማሪ ማምረቻዎች ተከፍተዋል። በእነዚህ ሶስት ማምረቻዎችም ዘመናዊ የሆኑ ማሽኖች ሲኖሩ፤ ማሽኖቹ መቁላት፣ መከካት፣ መፍጨት፣ ማሸግና ሌሎች ተግባራትንም ማከናወን የሚችሉ ናቸው። መሸጫ ቦታን በተመለከተም በከተማዋ የተለያዩ አካባቢዎች ባሉት የመሸጫ ሱቆች ምርቶቹን ለአገር ውስጥ ገበያ ያቀርባሉ፡፡

ፋሲካ ቅመማ ቅመምና ባልትና ድርቆሽን ጨምሮ በርበሬ፣ ሽሮ፣ ቡላና ሌሎች ኢትዮጵያዊ የሆኑ ማናቸውንም የባልትና ውጤት ምርቶችን ያዘጋጃል። ‹‹በባልትናው ዘርፍ በአገሪቱ ፈር ቀዳጆች ነን›› የምትለው ኤልሳ፤ ሥራውን ከልብ ወዳውና አምናበት እንደምትሠራው ትናገራለች፡፡

በአጼ ኃይለስላሴ ዘመን የኢትዮጵያ ቅመማ ቅመም ፋብሪካ የሚባል ድርጅት ተቋቁሞ እንደነበር ታስታውሳለች፡፡ ከዛ በኋላ ግን በግለሰብ ደረጃ በዘመነ ደርግ የባልትና ውጤቶችን ማምረት የጀመሩት ወላጆቿ እንደሆኑ ትናገራለች፡፡ በወቅቱ ሥራው ነውር እንደነበርና በብርቱ ትግል ዛሬ ላይ መድረሱን አጫውታናለች፡፡

ትናንት እንደነውር ይታይ የነበረው የባልትና ውጤቶችን መግዛት ዛሬ ላይ በማህበረሰቡ የተለመደና የዘመናዊነት መገለጫ ሆኗል፡፡ ጊዜያቸውን አትርፈው ድካም መቀነስ እንደቻሉ የሚናገሩ በርካታ ደንበኞች አሉን ስትል ኤልሳ ትገልጻለች፡፡ በቅመማ ቅመም ምርቶች በኩል አብዛኞቹ ደንበኞች በውጭ አገር ያሉ እንደመሆናቸው በዘርፉ በስፋት አልተሠራም ትላለች፡፡ መንግሥት ለዘርፉ ልክ እንደ ቡና ሁሉ ትልቅ ትኩረት ሰጥቶ መሥራት ቢቻል ለአገር ኢኮኖሚያዊ ዕድገት የሚያበረክተው አስተዋጽኦ እጅግ የጎላ መሆኑን ታነሳለች፡፡

“በቁጥር 20 የሚደርሱ የቅመማ ቅመም አይነቶች ኢትዮጵያ ውስጥ አሉ” የምትለው ኤልሳ፤ እነዚህን ቅመማ ቅመም በጥራትና በብዛት ማምረት ቢቻል የሚያስገቡት ገቢ ቀላል ግምት የሚሰጠው እንዳልሆነ ትናገራለች፡፡ ከእያንዳንዱ ቅመማ ቅመም የሚገኝ ገቢም ኢኮኖሚያዊ አበርክቶው የጎላ ይሆናል፡፡ የኢትዮጵያ ቅመማ ቅመም ደግሞ በውጭው ዓለም እጅግ ተፈላጊ ነው የምትለው ኤልሳ፣ ይህን ዕድል መጠቀም አስፈላጊ መሆኑን ትገልጻለች፡፡ ኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ የቅመማ ቅመም አይነቶች በሙሉ በውጭው ዓለም ስለመኖራቸው በማንሳት፣ የቅመሞቹ ቃና ከኢትዮጵያ ቅመም በእጅጉ እንደሚለይ ነው የምትናገረው፡፡ የኢትዮጵያ ቅመማ ቅመሞች ቃናና ጣዕም እጅግ ተፈላጊና ተመራጭ መሆኑን ጠቅሳለች፡፡

በውጭው ዓለም ተመራጭና ተወዳጅ በሆነው የኢትዮጵያ ቅመማ ቅመምና ባልትና ላይ እሴት በመጨመር ለአገር ውስጥና ለውጭ ገበያ ማቅረብ ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታዎች አሉት የምትለው ኤልሳ፤ ምርቱን አዘጋጅተው ለውጭ ገበያ የሚያቀርቡትን ጨምሮ አገርም ከዘርፉ ተጠቃሚ መሆን እንደምትችል በማመላከት ዘርፉ ላይ ሰፊ ሥራ መሠራት እንዳለበት አስገንዛባለች። በተለይም በጥራት በኩል ተወዳዳሪ ለመሆን እንደ በርበሬና ዝንጅብል በመሳሰሉ ምርቶች ላይ የሚፈጠሩ ፈንገሶችን በማስወገድ ጥራት ያለው ምርት በማምረት ከተቻለ የቅመማ ቅመም ዘርፍ ከቡና ያልተናነሰ ገቢ ማምጣት እንደሚችል ጠቁማለች፡፡

ኤልሳ እንደምትለው፤ የፋሲካ ቅመማ ቅመምና የባልትና ውጤቶች በአውሮፓ ሰፊ ገበያ አላቸው። የኢትዮጵያ በርበሬም በውጭው ዓለም እጅግ ይፈለጋል። ከተወሰነ ጊዜ ወዲህ ግን በበርበሬ ላይ አፍላቶክሲን የተባለ ፈንገስ ተከስቷል መባሉን ተከትሎ ችግሩ ለገበያው እንቅፋት እንደሆነም ጠቁማለች፡፡ በዚህ ምክንያትም በውጭው ዓለም እጅግ ተፈላጊ የሆነው የኢትዮጵያ በርበሬ በአሁኑ ወቅት ገበያው መቀዛቀዙንና ይህም በእጅጉ እንደሚያስቆጫት ትናገራለች፡፡ ይሁንና በርበሬን ተክቶ ሽሮና የተለያዩ የባልትና ውጤቶች እንዲሁም በቁጥር 20 የሚደርሱ ቅመማ ቅመሞችን ጭምር ኤክስፖርት በማድረግ አገሪቷ ከዘርፉ ተጠቃሚ መሆን እንደቻለች ነው ያመላከተችው፡፡

ፋብሪካቸው በጥሬው ወደ ገበያ የሚያወጣው ምንም አይነት ምርት እንደሌለም አስረድታለች። ማንኛውም ቅመማ ቅመም እሴት ተጨምሮበት ለምግብነት ተዘጋጅቶ ለገበያ እንደሚቀርብ ነው የገለጸችው፡፡

ማህበራዊ ኃላፊነትን በመወጣት ረገድም የተለያዩ አስተዋጽኦዎች ያሉት ፋሲካ ቅመማ ቅመምና ባልትና መነሻ በሆነው ሳሪስ አካባቢ ለሚገኙ ወጣት የእግር ኳስ ቡድን ድጋፍ ያደርጋል። ወጣቶቹም የተደረገላቸውን ድጋፉ ተጠቅመው አልባሌ ቦታ ላይ ከመዋል ይልቅ በኳስ ጨዋታ ጊዜያቸውን እያሳለፉ እንደሆነ አስረድታለች። ክብር ለአረጋውያን ለተባለ ድርጅትም እንዲሁ በየወሩ ሽሮና በርበሬን ጨምሮ አስፈላጊ የሆኑ አስቤዛ ይቀርብላቸዋል፡፡ ይህም ካለፉት አራት ዓመታት ጀምሮ ተግባራዊ ሲደረግ የቆየ በጎ ተግባር ሲሆን፤ በተጨማሪም በተለያዩ አጋጣሚዎች በአካባቢው ለሚገኙ አቅመ ደካሞች ድጋፍ ያደርጋል፡፡ አገራዊ ለሆኑ ማንኛውም ጥሪዎችም አቅም በፈቀደ መጠን ፈጣን ምላሽ በመስጠት ማህበራዊ ኃላፊነታቸውን እየተወጡ ይገኛሉ፡፡

ረጅም ጊዜ ያስቆጠረው ፋሲካ ቅመማ ቅመምና ባልትና በአሁኑ ወቅት ዘመናዊ ማሽኖችን እንደሚጠቀም የተናገረችው ኤልሳ፤ ለአብነትም ሽሮን ቆልቶ፣ ከክቶ፣ አበጥሮና ፈጭቶ የሚያሽግ ማሽን በመጠቀም በቀላሉ ምርቱ እንደሚመረት ገልጻለች። ሌሎችም መታመስ የሚፈልጉ ቅመሞችንም እንዲሁ ማመስ የሚችሉ ማሽኖች ስለመኖራቸው አጫውታናለች፡፡

በባህላዊ መንገድ የተጀመረው ፋሲካ ቅመማ ቅመምና ባልትና በዘመናዊ መንገድ ጥራቱን አስጠብቆ በማስቀጠል ከሶስት አስርት ዓመታት በላይ መቆየት በመቻሉ በተለያየ ጊዜ ሽልማቶችም ተበርክተውለታል፡፡ በቅርቡም ለረጅም ጊዜ ገበያ ውስጥ በመቆየቱ፣ በጥራቱና በማኔጅመንቱ ከአቢሲኒያ አዋርድ ሽልማት የተበረከተለት መሆኑን ጠቅሳ፣ ሽልማቶቹም የወርቅ፣ የዋንጫና የዲፕሎማ መሆናቸውን ነው ኤልሳ የጠቀሰችው፡፡

ድርጅቱ ሰፊ የማምረቻ ቦታ ማግኘት ባለመቻሉ በተለያየ ቦታ እያመረተ መሆኑን ጠቅሳም፤ ተጨማሪ ሰፊ የማምረቻ ቦታ ከመንግሥት እንዲሰጣው ጥያቄ ማቅረቡን ትናገራለች፤ ጥያቄው ምላሽ ሲያገኝም ትልቅ ፋብሪካ የማቋቋም ዕቅድ እንዳለውም የጠቆመችው፡፡ ፋብሪካው ሲገነባም ሰፊ የሥራ ዕድል እንደሚፈጠር ጠቁማ፣ ዘርፉን ለትውልድ በማስተላለፍ ፋሲካ ቅመማ ቅመምና ባልትናን የማስቀጠል ኃላፊነታቸውን እንደሚወጡ አስረድታለች። ከዚህም ባለፈ የኢትዮጵያን ቅመማ ቅመምና የባልትና ውጤቶችን በዓለም አቀፍ ደረጃ በስፋት በማስተዋወቅ አገሪቷ ከዘርፉ የሚገባትን የኢኮኖሚ ተጠቃሚነት እንድታረጋግጥ ፋሲካ ቅመማ ቅመምና ባልትና ተግቶ እንደሚሠራ አጫውታናለች፡፡

# ስፖርት



# ስስፖርተኞች ተስፋ የሰነቁ የድሬዳዋ ማዘውተሪያ ስፍራዎች

**ጌትነት ምህረቴ**

በውስጡ ደረጃውን የጠበቀ የእግር ኳስ ሜዳ፤ የመለማመጃና የመወዳዳሪያ የመዋኛ ገንዳዎችን፣ ጅምላዚሞችን፣ የስፖርተኞች መኖሪያ ህንጻዎችን፣የግራውንድ ቴኒስ ሜዳንና የአስተዳደር ህንጻዎችን አካቶ መያዙን ተመልክተናል፡፡እንዲሁም ከ2000 በላይ ሰዎችን የሚያስተናግድ የስብሰባ አዳራሽ፣ ቤተ መጻህፍት፣ የመማሪያ ክፍሎችን፣ ካፍቴሪያና ሌሎች የስፖርት መሰረተ ልማቶችን በውስጡ ይዟል፡፡ ይህ ዘመናዊ የድሬዳዋ ሁለገብ የወጣቶች የስፖርት አካዳሚ በአሁኑ ጊዜ ግንባታው በመጠናቀቅ ላይ ይገኛል፡፡

307 ሚሊዮን ብር እየተገነባ የሚገኘው የወጣቶች ስፖርት አካዳሚ ቀሪ ስራዎቹን ዘንድሮ ሙሉ ለሙሉ ተጠናቆ በመጪው ዓመት አገልግሎት እንደሚሰጥ የሚናገሩት በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ወጣቶችና ስፖርት ኮሚሽን የፋሲሊቲ ቡድን መሪና የግንባታው ክትትል ባለሙያ አቶ ምህረቱ ዘላለም፤ ማዕከሉ ለወጣቶች የስፖርት ማዘውተሪያና በተለያዩ የስፖርት አይነቶች የሚሰለጥኑበት አካዳሚ መሆኑን ነግረውናል፡፡

የአካዳሚው ግንባታው የተጀመረው ግንቦት ወር በ2011 ዓ.ም ሲሆን በአሁኑ ጊዜም ግንባታ አፈጻጸም 97 ነጥብ 7 በመቶ መድረሱን ነው የገለጹት፡፡

አዲሱ አካዳሚ በከተማዋ የተቀዛቀዘውንና የቀነሰውን የስፖርት እንቅስቃሴ ይመልሳል ተብሎ ተስፋ ተጥሎበታል የሚሉት አቶ ምህረቱ፤ በዚህ አካዳሚ ሁሉም ስፖርተኞች እንደየፍላጎታቸው ስልጠናቸውን በመከታተል ለተለያዩ የስፖርት ክለቦች የሚሆኑ ብቁ ስፖርተኞች የሚፈሩበት ይሆናል ነው ያሉት፡፡

በተለይ ከተገነቡት ሁለት የመዋኛው ገንዳዎች አንዱ መለማመጃ ሲሆን ሁለተኛው ዓለም አቀፍ መስፈርት



ከተገነቡት ሁለት የመዋኛው ገንዳዎች አንዱ ዓለም አቀፍ መስፈርት ያሟላና በኢትዮጵያ የመጀመሪያው መሆኑ ተጠቁሟል፣

ያሟላና በአገራችን ደረጃ የመጀመሪያው መሆኑን ጠቅሰው፤ እንደ አገር በውሃ ዋና በዓለም አቀፍ ደረጃ ብቁ ስፖርተኞችን ለመፍራት የሚያስችል መሆኑን ይገልጻሉ።

120 ሰልጣኖች የሚሰለጡንበት የተሟላ የአካዳሚ አገልግሎት የሚሰጡ የስፖርትና የመዝናኛ መሰረተ ልማቶች ያሉት አካዳሚ ነው፡፡ አካዳሚው በግንባታው ወቅትም ለበርካታ የከተማው ነዋሪዎች የስራ ዕድል መፍጠር ችሏል። በቀጣይም ብቁ፣ ስነ ምግባር የተላበሱና ጤናማ ስፖርተኞችን ያፈራል ተብሎም ተስፋ ተጥሎበታል፡፡

አካዳሚው በውስጡ አንፊ ቲያትር የተገነባለት ሲሆን ለወጣቶችና ለህጻናት ለስፖርታዊ እንቅስቃሴና መዝናኛ ቦታ ሆኖ የሚያገለግል ግዙፍ ፕሮጀክት መሆኑን አቶ ምህረቱ ገልጸዋል፡፡

በሌላ በኩል የ10ኛውን የአፍሪካ ዋንጫ ያስተናገደው የድሬዳዋ ስታዲየም የማሻሻያ ግንባታ 448 ሚሊዮን ብር ወጪ እየተካሄደ ይገኛል፡፡በ1968 ዓ.ም ለአገልግሎት የበቃውና ከአዲስ አበባ ስታዲየም ቀጥሎ ዓለም አቀፍ ወድድሮችን ሲያስተናግድ የቆየው ይህን ታሪካዊ ስታዲየም ዓለም አቀፍ ደረጃውን በጠበቀ መልኩ የማሻሻያ ግንባታዎችን እየተካሄዱለት መሆኑን አቶ ምህረቱ ይናገራሉ፡፡

የማሻሻያ ግንባታው ዓለም አቀፍ ስታዲየሞች ማሟላት ያሉባቸውን መሰረተ ልማቶችን ያካተተ ነው፡ ፡ ስታዲየሙ 25ሺህ ሰዎችን የሚይዝ ሲሆን በፊፋ ደረጃ መሰረት ልብስ መቀየሪያና መልበሻ ክፍሎች፣ የማሳጅ፣ የሚዲያና መሰል አስፈላጊ ክፍሎችን ያሟላ ነው፡፡

በአሁኑ ጊዜ የማጠናቀቂያ ስራዎች እየተሰሩ ሲሆኑ በዚህ ዓመት ሙሉ ለሙሉ እንደሚጠናቀቅና በመጪው ዓመትም ዓለም፣ አህጉርና አገር አቀፍ ውድድሮችን ማስተናገድ እንደሚችል ነው ያብራሩልን፡፡

በከተማዋ የሙቀቱ መጠንና የውሃው ጨዋማነት ከፍተኛ በመሆኑ በስታዲየሙ የመጫዋቻ ሳሩ ችግር ይፈጥር እንደነበር አቶ ምህረቱ አስታውሰው፤ ችግሩን በዘላቂነት ለመፍታትም የከተማ አስተዳደሩ የፊፋን ደረጃ ያሟላ አርቲፊሻል ሳር እንዲገዛና እንዲነጠፍ ውሳኔ አሳልፎል፡፡ ይህ አርቲፊሻል ሳር ለ10 ዓመታት የሚያገለግልና የፊፋን መስፈርት ያሟላ ነው፡፡

በቅርብ ጊዜ የማንጠፍ ስራው ተከናውኖ ዓለም አቀፍ ውድድሮችን ወደ ድሬዳዋ ለማምጣት ዝግጁ እንደሚሆን ገልጸዋል፡፡

የማሻሻያ ግንባታው እየተካሄደ የሚገኘው የድሬዳዋ ታሪካዊ ስታዲየም ሲጠናቀቅም በአሁኑ ጊዜ ኢትዮጵያ ውስጥ የፊፋን ስታዳርድ የሚያሟላ ዓለም አቀፍ ስታዲየም ባለመኖሩ ምክንያት ውጭ አገር በመሄድ የሚጫወተውን የኢትዮጵያ ብሄራዊ ቡድን እዚህ አገሩ ላይ ጨዋታዎችን እንዲያደርግ የሚያስችልም ነው፡፡

በመጪው ዓመት አህጉራዊና ዓለም አቀፍ ጨዋታዎችን በድሬዳዋ ስታዲየም ለማስተናገድ ነው እየሰራን ያለነው የሚሉት አቶ ምህረቱ፤ ካፍ በሰጠን አስተያየት መሰረት ግንባታው የተካሄደ የሚገኘው፡፡ የካፍ ተወካዮችም ይህን የማሻሻያ ግንባታ ተመልክተው ዓለም አቀፍ ፍቃድ ይሰጡናል ብለን እንጠብቃለን ነው ያሉት፡፡

ከተማዋ ዘመናዊ የወጣቶች ስፖርት አካዳሚና ታሪካዊውን የድሬዳዋ ከተማ ስታዲየም የማሻሻያ ግንባታ ከፍተኛ ገንዘብ በመመደብ እያካሄደች መሆኑን የሚገልጹት፤ የድሬዳዋ ከተማ አስተዳድር ከንቲባ አቶ ከድር ጁሃር፤ ይህም የከተማ አስታደድሩን ስፖርታዊ ውድድሮች በማሳደግ ከተማዋን ብሎም ሀገርን የሚያስጠሩ ተተኪ ስፖርተኞች ለማፍራት ትልቅ ድርሻ ይኖራቸዋል ነው ያሉት፡፡

እየተገነቡ ያሉ መዝናኛዎችና የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች ወጣቶችን ከደባል ሱስ በማላቀቅ አምራች ትውልድ መፍጠር የሚያስችሉ መሆናቸውን ጠቅሰው፤ ፕሮጀክቶቹ ትውልድን በመቅረጽና ብቁ ተወዳዳሪ ስፖርተኞችን በማፍራት ረገድ የጎላ ሚና እንደሚኖራቸው ተናግረዋል።

የከተማ አስተዳደሩ ለህፃናትና ወጣቶች ትኩረት ሰጥቶ የሚሰራቸው የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች ብቁ ዜጋ ለመፍራት ዓላማ ያላቸው መሆኑን አመልክተው፤ የወጣቶችና የስፖርት ቤተሰቡ የረጅም ጊዜ ጥያቄዎችን መፍትሔ ለመስጠት የስፖርት ልማት ፕሮጀክቶችን ጀምሮ በፍጥነት ማጠናቀቅ መቻሉን ትልቅ ስኬት ነው ብለዋል፡፡

የድሬዳዋ ከተማ ወጣት በእነዚህ የስፖርትና የመዝናኛ ቦታዎችን በመጠቀም ለአገሩና ለከተማዋ የሚያስጠራ ስፖርተኛ መሆን እንደሚኖርበት ጥሪ አቅርበዋል፡፡


## የደረሰኝ መጥፋት ማስታወቂያ

በአዲስ አበባ ከተማ አቃቂ ቃሊቲ ክ/ከ ወረዳ 04 የቤት ቁጥር አዲስ ግብር ከፋይ መለያ ቁጥር (TIN) 0074608982 ጌጤነሽ አበራ በቀለ ከተመዘገብኩበት አቃቂ ቃሊቲ ክ/ከ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ፅ/ቤት የህትመት ፍቃድ በማግኘት ካሳተምኩት ደረሰኝ ውስጥ የተጨማሪ እሴት ታክስ (ቫት) የእጅ በእጅ ሽያጭ ከቁጥር 051 እስከ 250 ያልተሰራበት የጠፋ ስለሆነ በማንኛውም አካል እጅ ውስጥ ገብቶ ወንጀል እንዳይሰራባቸው እና የጠፋ መሆኑን የ3ኛ ወገን እንዲያውቀው ይህ ማስታወቂያ እንዲተላለፍ ተደርጓል፡፡ ነገር ግን ከደረሰኙ ውስጥ ተሰርቶበት ያገኘ ወይም ከድርጅቱ ግዥ በማከናወን ክፍያ ለመፈፀም በማስረጃነት የተቀበለ ማንኛውም ሰው ከላይ ለተጠቀሰው በግብር/ታክስ ከፋይነት ከተመዘገብኩበት አቃቂ ቃሊቲ ክ/ከ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ፅ/ቤት ወይም በአቅራቢያው ለሚገኝ ገቢ ሰብሳቢ መ/ቤት በማሳወቅ በግብር/ታክስ አሰባሰብ ላይ ትብብር እንዲያደርግ አስታውቃለሁ፡፡

**ግብር ከፋይ ስም ጌጤነሽ አበራ በቀለ**

## አዲስ አበባ አስተዳደር

የባለንብረት ስም አለምፀሀይ ሰለሞን ዘለቀ የሰሌዳ ቁጥር አአ 02-01-B61840 የተሽከርካሪው አይነት አውቶሞቢል የሻንሲ ቁጥር NZE120-3002578 ሞዴል TA-NZE120-AEPNK-A የሞተር ቁጥር 2NZ-1646997 የሊብሬ ቁጥር 231150/231650/232079/528508 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሰሌዳ ጠፋብኝ ብለው 22/7/2015 አመልክተዋል፡፡ ሠሌዳው ወድቆ፣ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ፣ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን የቂርቆስ ቅ/ጽ/ቤት**

የባለንብረት ስም ልኡል ደለለኝ ዘለቀ የተሽከርካሪው አይነት ደረቅ ጭነት ከ11 ኩንታል ያነሰ የሰሌዳ ቁጥር አአ 03-01-A35625 የሻንሲ ቁጥር JT132LNF000003018 ሞዴል LN150L-CRMDSW የሞተር ቁጥር 2L-4684304 የሊብሬ ቁጥር 419462 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሰሌዳ ጠፋብኝ ብለው 15/7/2015 አመልክተዋል፡፡ ሠሌዳው ወድቆ፣ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ፣ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፍቃድና ቁጥትር ባለሥልጣን የቃሊቲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

ከሳሽ አቶ ሳሙኤል ብዙነህ ሽፈራው እና ተከሳሽ አቶ ዮናስ ደጀኔ ዳባ መካከል ፍ/ብሔር ስላለው ክስ ጉዳይ ተከሳሽ በ20/8/2015 ዓ.ም ለሆነው ቀጠሮ በ5፡00 ሰዓት ለመ/ደ/ፍ/ቤት የካ ምድብ 4ኛ ፍ/ብሔር ችሎት እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡

**ፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት**

በከሳሽ ኢትዮ ቴሌኮም በተከሳሽ፡- ታጁዲን አጠቃላይ መካከል በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ልደታ ምድብ 9ኛ ችሎት ባለው ክርክር ጉዳይ ተከሳሽ/ተጠሪ በ17/8/2015 ዓ.ም ከቀኑ ሰዓት ላለው ቀጠሮ በችሎት እንዲቀርቡ ፍርድ ቤቱ አዟል፡፡

**ፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት**

## የደረሰኝ መጥፋት ማስታወቂያ

በአዲስ አበባ ከተማ የካ ክ/ከ ወረዳ 06 የቤት ቁጥር አዲስ ግብር ከፋይ መለያ ቁጥር (TIN) 0081220132 ታዬ ደጀን አልጣህ በግብር/ታክስ ከፋይነት ከተመዘገብኩበት የካ ከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ፅ/ቤት የህትመት ፍቃድ በማግኘት ካሳተምኩት የእጅ በእጅ ሽያጭ ተጨማሪ እሴት ታክስ /ቫት/ ደረሰኝ ከቁጥር 0001 እስከ 0100 ያልተሰራበት ስለጠፋብኝ በማንኛውም አካል እጅ ውስጥ ገብቶ ወንጀል እንዳይሰራባቸው እና የጠፋ መሆኑን የ3ኛ ወገን እንዲያውቀው ይህ ማስታወቂያ እንዲተላለፍ ተደርጓል፡፡ነገር ግን ከደረሰኙ ውስጥ ተሰርቶበት ያገኘ ወይም ከድርጅቱ ግዥ በማከናወን ክፍያ በመፈፀም በማስረጃነት የተቀበለ ማንኛውም ሰው ከላይ ለተጠቀሰው በግብር/ታክስ ከፋይነት ለተመዘገብኩበት የካ ከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ፅ/ቤት ወይም በአቅራቢያ ለሚገኝ ገቢ ሰብሳቢ መ/ቤት በማሳወቅ በግብር/ታክስ አሰባሰብ ላይ ትብብር እንዲያደርግ አስታውቃለሁ፡፡

**የግብር ከፋይ ስም ታዬ ደጀን አልጣህ**

በአመልካች ወ/ሮ አማን ደዬሳ ቃበታ እና በተጠሪ አቶ አየለ ጌታቸው ታደሰ መካከል ስላለው የፍ/ብሔር ክርክር ጉዳይ አመልካች ወ/ሮ አማን ደዬሳ ቃበታ ለ16/08/2015 ዓ.ም ለሆነው ቀጠሮ ከጠዋቱ 3፡20 ሰዓት ፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት አራዳ ምድብ 6ኛ ቤተሰብ ችሎት እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡

**የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት**

አመልካች ወ/ሮ ባንቺጊዜ ደመም ማዘንጊያ እና ተጠሪ አቶ አበባው ካሳሁን ይግዛው ላይ የመጥፋት ውሳኔ እነዲሰጣቸው አቤቱታ አቅርበዋል፡፡ ስለሆነም ተጠሪ ወይም ያሉበትን የሚያውቅ ሰው ካለ ለ1/9/2015 ዓ.ም በ4፡00 ሰዓት በአ/አበባ ከተማ የመጀ/ደ/ፍ/ቤት አራዳ ምድብ ችሎት እንዲቀርቡ ታዟል፡፡

**በአ/አበባ ከተማ የመጀ/ደ/ፍ/ቤት አራዳ ምድብ ችሎት**